# የክብር ዘበኛ ቀጣይ ዝግጅት (ረቡዕ ታኅሣሥ ፭)

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ኋላ ለፍርድ ቤት በሰጡት ቃል በልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ተሰብስቦ በነበረው በዘውድ ጠባቂዎች ስብሰባ የተወሰነውን በልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ተገልጾላቸው በሐሳቡ ተስማምተው፤ ከሌሊቱ ፱ ሰዓት ገደማ ከወጡ በኋላ ከቆዩበት ቆይተው መንገዳቸውን ያቀኑት ወደ ደብረ ብርሃን ሳይሆን፤ ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ነበር። ማክሰኞ ለረቡዕ አጥቢያ ከጠዋቱ ፲፩ ሰዓት ሲሆንም ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ደርሰው ጄኔራል መንግሥቱን አገኙ። ጄኔራል መንግሥቱም በመገረም፤ "እንዴት በዚህ ሰዓት እዚህ መጡ?" ሲሏቸው፤ እሳቸውም፣ «ወታደሩ ግርግር አድርጓል ሲሉ ሰማሁ። ሰዎችም ተይዘዋል ይባላል። ምንድነው ነገሩ?» አሉና መልሰው ጠየቁ።



ደጃዝማች ከበደ ተሰማ

ከዚህ በኋላ ጄኔራል መንግሥቱ «አዎ! የጦር ሠራዊት አድሞ የጃንሆይን መንግሥት ለመገልበጥ ተነሥቷል» አሉ። ደጃዝማችም፣ «ለመሆኑ ያደመው ወታደሩ ወይስ ሹማምንቱ ናቸው?» አሉ። ጄኔራል መንግሥቱም «ምንም የለየ ነገር የለም፤ ሁለቱም ናቸው። ለማንኛውም ጉዳይ ጄኔራል መርዕድን ፈልጌው ነበር፤ አጣሁት። ከሱ ጋር ብንገናኝ ነገሩ ምናልባት ወደ ደህና ሊያመራ ይችል ይሆናል» አሏቸው። ደጃዝማች ከበደም «ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ፣ ደም መፋሰስ እንዳይደርስ ከጄኔራል መርዕድና ከጄኔራል ከበደ ገብሬ ጋር ብትነጋገሩ ይሻላል» ሲሉ፤ ጄኔራል መንግሥቱም የሽምግልና ተግባር እንዲጀመር በማሰብ «ይርዱኝ! እኛ ተገናኝተን ከተነጋገርን ደም መፋሰስ ላይደርስ ይችላል» አሏቸው። ደጃዝማች ከበደም «ግርማዊት እቴጌ በድንጋጤ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ጥንቃቄ እንዲደረግላቸው፤ የልዑል አልጋወራሽ ቤተሰቦችም ሥጋት ላይ ስለሆኑ፤ የጤንነታቸው ሁኔታ እንዲገለጽላቸው» በማለት አሳሰቡ።

ጄኔራል መንግሥቱም ስለግርማዊት የሚያሳስብ ነገር እንደሌለ፤ ከአባ ሐና ጋርም በጉዳዩ መነጋገራቸውን ሐኪምም እንዳይለያቸው ማድረጋቸውን፣ የአልጋ ወራሽን ደህንነትም ካፒቴን ኃይሉ መጥተው ካዩዋቸው በኋላ ተመልሰው ለልዕልት ባለቤታቸው ሁኔታውን እንዲገልጹላቸው ማድረግ የሚቻል መሆኑን፤ በረጋ መንፈስ



*ደጃዝማች ከበደ ተሰማ*

ተነሥቷል» አሉ። ደጃዝማቹም፣ «ለመሆኑ

አስረዷቸው፡፡ ነገሩ የከነከናቸው ደጃዝማች ከበደ፣[30] «በፊት ሰምቼ የነበረው ጦር ሠራዊትም ክብር ዘበኛም ሁለታችሁም ዐምፃችኋል» የሚል ወሬ ነበር፡፡ አሁን ግን ያመፀው ጦር ሠራዊት ብቻ መሆኑን ነገርከኝ፡፡ ለማንኛውም መገናኛ ስጠኝና ብሔራዊ ጦርን ለማዘጋጀት መንገዴን ልቀጥል» አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጄኔራል መንግሥቱ ኮስተር ብለው «መጀመሪያ እነጄኔራል መርዕድ ዘንድ ሔደው እኛ እንድንገናኝ ቢያደርጉ ይመረጣል» አሏቸውና ደጃዝማች ከበደ መንገዳቸውን ወደዚያው አቀኑ[31]፡፡

በዚህ መሐል ማክሰኞ በክብር ዘበኛ መኮንኖች ሠፈር ከሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ መኖሪያ ቤት አጠገብ የሚኖር፣ አቶ ወሰንየለህ ብጡል የተባለ የትምህርት ሚኒስቴር ባልደረባ ጓደኛዬ «እህትህ ደክማለችና ቶሎ ድረስ» ተብሎ ወደ ጐንደር ለመሔድ ይዘጋጅ ስለነበር፤ ከሌሎች ጓደኞቼ ጋር ሆነን እርሱ ጋር አምሽተን ነበር፡፡ በመጨረሻም ጉዞው በነጋታው ስለነበር፤ ከነበርነው ሦስት ጓደኞቼ (አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ (በኋላ አምባሳደር)፣ አቶ ታደሰ ዘለቀ (በወቅቱ የሺመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር) እና እኔ (የዚህ ታሪክ ጸሐፊ)) መካከል ረቡዕ ጠዋት በ፲፪ ሰዓት ከአቶ ወሰን የለህ ቤት ቀድሞ የደረሰ አውሮፕላን ማረፊያ ያድርሰው ተባብለን ከጄኔራል ሙሉጌታ መኖርያ ቤት አጠገብ ከነበረው ከአቶ ወሰን የለህ ቤት ተነስተን ወጣን፡፡ ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ገደማ ራስ ደስታ ሆስፒታል ጀርባ ወደነበረው ቤቴ ስመለስ፤ በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያና በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት አካባቢ ያየሁት አዲስ ነገር አልነበረም፡፡

ማክሰኞ በተነጋገርነው መሠረት፣ ረቡዕ ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት ከጉለሌ በአፍንጮ በር አድርጌ፣ የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ልዩ ኤታ ማጀር ቢሮ ከሚገኝበትና ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ግቢ ለጃንሆይና ለከፍተኛ ባለሥልጣኖቹ መግለጫ እሰጥበትና ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ የሥራ እገዛ ለማድረግ ቀደም ብሎ ጠዋትም ሆነ ማታ እወጣ እገባበት የነበረው የቤተ መንግሥት መግቢያ (በቀድሞው ጽሕፈት ሚኒስቴር አሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አምስተኛ በር የሚባለው) በር ስደርስ፤ አንድ ታንክ ቆሞ አየሁ፡፡ እርሱን በችኮላ አልፌ ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ፣ ወደ አንበሶች ቤትና ወደምኒሊክ ሆስፒታል ከሚወስደው መስቀለኛ መንገድ ስደርስ፤ ሌላ ታንክ ቆሞ አየሁ፡፡ ከዚያም የመ/አለቃ ሙላቱ ነጋሽ (በኋላ ሜጀር ጄኔራል) ከታንኩ ወርዶ አስቁሞ መታወቂያዬን ስለጠየቀኝ፤ ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት፡፡ ከዚያ ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ወስዶ ፎቅ መውጫ ደረጃው ላይ አድረሶኝ ተመለሰ፡፡

---

[30] እዚህ ላይ የደጃዝማች ከበደን ጥያቄና ጥቆማ ልብ ይሏል፡፡ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት የመፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ መኖሩን ቀደም ብለው ያውቁ እንደነበር ነው፡፡ ቅር ያላቸውም ያደመው ጦር ሠራዊት ብቻ ነው መባሉንና መለያየቱን ነው እንጂ ሙሉ እንቅስቀሴውን መጥላታቸውን አላሳዩም፡፡ አዝማሚያቸውም ተገናኝታችሁ ተስማሙበት የሚል ነበር፡፡

[31] ጄኔራል መንግሥቱም ደጃዝማች ከበደ ተሰማም ለፍርድ ቤት የሰጡት ቃል ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ጄኔራል መንግሥቱ ከፎቅ ወደ ምድር ሲወርዱ ያዩኝና «ብርሃኑ! ብርሃኑ! ና» ብለው፣ ወደ ፎቅ ተመልሰው እየመሩኝ ሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ያለበትን ክፍል አሳይተውኝ እንደገና ወረዱ። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ካለበት ክፍል ልገባ ስል እሱ ወደበሩ መጥቶ ተጨባበጥን። አጨባበጡ ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ ሲሆን፣ ሰላምታ ሳይሆን በእጁ ወደኋላ እንደመግፋት ነበር። «ተመልሰህ ሒድ፣» ማለቱ እንደሆነ ቀርቀብ አደረግሁ። ጥንስሱን ቀደም ብዬ ባውቅም፣ በዚያን ጊዜ የተገነዘብኩት ስሜቱ ግን ነገሩ ጥሩ እንዳልነበረ ነው። እሱ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ትቶ መሔድ ደግሞ ኅሊናዬን ከበደው። እኔ በዚህ ስሜት ላይ ሁኜ እዚያው እንደቆምኩ፣ ገርማሜ መጣ። እርሱም ያሳየኝ ፊት እንደድሮው አልነበረም፣ የደስታ ስሜት አይነበብበትም። በዚህ ሁኔታ ላይ እንደነበርን የ፱ አለቃ ታከለ (የጄኔራል መንግሥቱ ሹፌር) ቢሮ ቁጥር ፳፬ አስገባኝ። የአካባቢውን ሁኔታ እያየሁ ትንሽ ቆይቼ፣ ይገቡ ይወጡ ከነበሩ ሌሎች ሰዎች ጋር ተደባልቄ ተመልሼ በመውጣት መተላለፊያው ላይ ቆሜ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን መጠበቅ ያዝኩ። በመኸሉ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከክፍሉ ብቅ ሲል አየኝና ትቸው መሔድ እንዳልፈልግሁ ተገንዝቦ መሰለኝ፣ «ሒድና እነ ከተማን እርዳቸው» በማለት ያሉበትን ክፍል አመላከተኝ። ወደዚያው ሔድኩ።

ክፍሉ ውስጥ አቶ ከተማ ይፍሩ የዐዋጁን ቃል ይጽፋል። አቶ ማሞ ታደሰ ሁለት እጃቸውን ከኪሳቸው አድርገው በመስኮት ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ያያሉ። አቶ ጌታቸው በቀለ ከመደርደሪያ ላይ ያለ ወረቀት እያገላበጠ ያያል። የሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ልዩ ጸሐፊ አቶ ሞገስ ሀብተ ማርያም (በኋላ አምባሳደር) አልጋ ወራሽ ያነበቡትን ዐዋጅ በታይፕ ይጽፋል። እኔን ያናገረኝ ሰው ስላልነበረ፣ ከክፍሉ ወጥቼ ወደ ምድር ቤት ወርጄ አደባባዩ ላይ እንደቆምኩ፣ ሻለቃ ተሰማ ዋቅጅራ ከውጭ ሲመጣ አገኘሁት። «ከየት እየመጣህ ነው?» ስለው «ጄኔራል መንግሥቱ ልዑል ራስ እምሩን ጥራ ብለው ልከውኝ ጠርቼ መምጣቴ ነው» አለኝ። በመቀጠልም «ወርቅነህን አግኝተኸዋል?» ሲለኝ፣ እንዳገኘሁት ገለጽኩለትና «ታዲያ ራስ እምሩ የታሉ?» ብለው፣ «እኔ ራሴ እመጣለሁ ሒድ» ብለውኛልና አሁን ይመጣሉ» አለኝ። እንዳለውም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እኛ እዚያው እንደቆምን መጡ።

እንግዲህ ነገሮች ሁሉ በእንዲህ እንዳሉ፣ ሌ/ኰሎኔል ወርቅነህ ምንም መሣሪያ አልያዘም ነበር። እኔ በአካባቢው ያለውንና የሚደረገውን እየተመለከትኩና እያሰላሰልኩ እንዳለሁ፣ ሦስት ሰዓት ሲሆን የሥራ ባልደረባዬ የሆነው አቶ ኤፍሬም ፀሐይ መጥቶ ተገናኘን። ሁኔታውን ሁሉ አጫወትኩት፣ ከዚያም ተመካክረን ወደ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቤት አመራን። ከቤቱ እንደደረስን ከድር የተባለውን የቤት ኃላፊ ‹‹ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ባዶ እጁን ስለሆነ፣ ከሰነድ መያዣ ቦርሳው ውስጥ የሚይዛትን «ኡዚ» ስጠን፣ እንውሰድለት›› ብለን አናገርነው። እርሱም በቅርብ ስለሚያውቀን «እሺ»› ብሎ አስፈርሞ ሰጠንና ወስደን ስንሰጠው፣ «ምን ያደርጋል? አያስፈልግም" ብሎ

ተከላከለን:: የዚህን ጊዜ እኔ ግድየለም ያዘው ብዬ አጠበኩኝ:: በመጨረሻ እየተገረመ ተቀብሎ ያዘው:: ከዚያ በኋላ እስከ መጨረሻው ድረስ ከጄ አልለያትም::

መሣሪያውን ከሰጠነው በኋላ፣ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጠን:: «አቶ ኤፍሬም ፀሐይ እስቲ ዞርዞር ብለህ የከተማውን ሁኔታ አይተህ ናና ግለጽልኝ:: አንተ (እኔን) የኤምባሲዎችና ቆንሲላ ጽሕፈት ቤቶች አገናኝ መኮንን (ሌይዘን) ስለሆንክ፤ የአሜሪካን ኤምባሲ የፖለቲካ ክፍል ኃላፊውን ሚስተር ማጊን፣ የእሥራኤል (ዲፋክቶ) ቆንሲላ ጄኔራሉን ሚስተር ባሮንን በመገናኘት ሐሳባቸውን ተቀብለህ መጥተህ ግለጽልኝ" ብሎ ላከን:: እኔም በአዘዘኝ ቦታዎች ተገኝቼ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ዲፕሎማቶች ሳነጋግር፤ ሚስተር ማጊ እንደበፊቱ ተቀብለው ወደቢሯቸው ወስደው ሳይሆን ወደ አጥሩ በር መጥተው በሩን ገርበብ አድርገው ይዘው «ወርቅነህ በዚህ ዐድማ ውስጥ መግባቱ በጣም ደንቆናል፤ ማመንም ቸግሮናል» ካሉኝ በኂላ፤ ‹የሚሳካ ይመስልሃል?» ሲሉ ጠየቁኝ:: የእሥራኤል ቆንስላው በተለይ «ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እንዲህ ያለ ሐሳብ ከነበረው፣ እንዴት ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደ ገብሬን እንዲሁ ይለቃቸዋል? ከጦር ሠራዊቱና ከአየር ኃይሉ ጋር ግንኙነት አድርገዋል ወይ? የሁለቱ ክፍሎች ኃይል ቢቻል ሁሉን ካልሆነም እንዲከፋፈል ያልተደረገ ከሆነ፤ የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በዚህ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ላይ መገኘት፣ በፈቃዱ ነው ለማለት ያስቸግራል:: ወርቅነህን እናውቀዋለን:: እንደዚህ ያለ ሥራ አይሠራም" አሉ:: ቀጥሎም «ጄኔራል መንግሥቱ የፖለቲካ ፍላጐት ያላቸው ናቸው ብለን እንገምታቸውም ነበር:: እንዲህ ማድረጋቸው በጣም ገርሞናል» በማለት እራሳቸውን እየነቀነቁ አግራሞታቸውን ገለጹልኝ::

በዚህ መሐል፤ ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከጧቱ ፪ ሰዓት ገደማ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ እንደደረሱ፤ ጄኔራል መንግሥቱ ተቀብለው ስለሰውጡና ስለሚታዩት ችግሮች ከገለጹላቸው በኋላ፤ በማንኛውም ነገር ለልዑል አልጋወራሽ ምክራቸውን እንዲለግሡ በመጠየቅ ከአልጋወራሽ ጋር አገናኟቸው:: በዚያኑ ወቅት ጄኔራል መንግሥቱ ደጃዝማች ከበደ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔደው ሜጀር ጄኔራል መርዕድን እንዲያነጋግሩ አግባብተው ከሸኟቸዉ በኋላ፤ በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሰብሳቢነት ገርማሜና ሌሎችን ለሥራው ዕውቀት አላቸው የሚሏቸውን ሰዎች ጨምረው፣ ለአዲሱ መንግሥት ማቋቋሚያ ዐዋጅ እንዲያረቁ ማዘዛቸውን ሰማሁ:: በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሰብሳቢነት ዐዋጁን ለማርቀቅ ተመድበው የነበሩት ሰዎችም አቶ ከተማ ይፍሩ፣ አቶ ማሞ ታደሰና አቶ ገርማሜ ንዋይ ነበሩ:: እነዚህ ሰዎች ዐዋጁን አርቅቀው ይዘቱን ለጄኔራል መንግሥቱ ማቅረባቸውን ሰማሁና ሌ/ኮሌኔል ወርቅነህ ወደ ክፍሉ እስቲመለስ ከሌሎቹ ተሰብሣቢ መኮንኖች ጋር ቁጥር ፳፬ ክፍል ሆኜ ስጠብቅ ቆየሁ::

እዚያው እያለሁ ትንሽ ቆይቶ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ መጥቶ ተገናኝንና በትእዛዙ መሠረት ሁለቱን ዲኘሎማቶች አነጋግሬ ያገኘሁትን አስተያየት ለወርቅነህ ሳቀርብለት፤

በብስጭትና በቁጭት አንዱን እጁን በሌላኛው እጁ በጥፊ በመምታት አስጮኸው:: ከዚያም ፊቱን እኔ ካለሁበት ከበሩ ወደ መስኮቱ በማዞር ሔደ:: ጥቂት ከቆየ በኋላ በድጋሚ «ሒድና አቶ ከተማ ይፍሩንና አቶ ማሞ ታደሰን እርዳቸው» ሲል ቆጣ ብሎ ትእዛዝ ሰጠኝ:: ሒድ ወደዚህ አትምጣ ማለት እንደሆነ ገባኝ:: "ነብር በወጥመድ" ምን ላድርግ? እሱ እኔን ከጉዳት ለማዳን ሒድ የሚል ምልክት ሲሰጠኝ፤ እኔ እርሱን እንዲያ ባለ ሁኔታ ትቶ መሔድን ኅሊናዬ የማይቀበለው ስለሆነ፤ በተቻለ ከሱ ብዙ ሳልርቅ ቆየሁ:: እምነቱ በጥንስሱም አብሮ መነሳት ወይም አብሮ መውደቅ ነበርና::

ከዚያም፣ ታኅሣሥ ፬ ቀን በዘብ ሥራ ውሎ ጃንሜዳ ያደረው እና በማግሥቱ ታኅሣሥ ፭ ቀን ለሥራ የገባው የክብር ዘበኛ ጦር፣ ጃንሜዳ እንዲሰበሰብ ከጄኔራል መንግሥቱ ትእዛዝ ተሰጠ:: በተላለፈው ትእዛዝ መሠረት ሠራዊቱ ሲሰባሰብም፤ በክብር ዘበኛ ውስጥ የሚገኙ መኮንኖች፣ ወታደሮችና ሲቪል ሠራተኞች ሁሉ መሣሪያ እንዲይዙ፤ የውጊያ ልብሳቸውን እንዲለብሱ ታዘዙ:: ሠራዊቱ በጃንሜዳ እንዲሰበሰብ የተደረገበትን ምክንያት ለማወቅ በጉጉት መጠየቁ አልቀረም ነበር:: የተሰጠው መልስም "ጦር ሠራዊት በጃንሆይ መንግሥት ላይ በማመፁ የክብር ዘበኛ ይህን ዐመፅ ለማክሸፍ ለግዳጅ ለማዘጋጀት ነው" ከሚል ከሹክሹክታ በቀር፤ ስለ ትክክለኛው ሁኔታ በግልጽ የተነገረ ነገር አልነበረም:: የክብር ዘበኛ ሠራዊትና ሲቪል ሠራተኞች በሙሉ ጠዋት ወደ ሥራ ከተተው ገቡ::

ከማለዳው ሁለት ሰዓት ሲሆን የክፍለ ጦሩ የመምሪያ መኮንኖች፣ የብርጌድ አዛዦች፣ የመድፈኛ ሻለቃ፣ የታንከኛና ፈረሰኛ፣ የመሐንዲስ፣ የመገናኛ፣ የትራንስፖርት፣ የሕክምና፣ ሙዚቀኛ፣ የተተኪ ሻለቃና ሌሎችም የጦር አዛዦች ሁሉ በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ተሰብስበው፤ "የጦር ሠራዊት ስላመፀ፤ ቀድመን ማጥቃት አለብን" በማለት ጄኔራል መንግሥቱ ዝርዝር ውስጥ ሳይገቡ በጥቅሉ ገለጹ:: ቀጥሎም፣ ቀደም ብሎ በተነደፈው ዕቅድ መሠረት የአሰላለፍ ዝግጅት ተደርጎ የቀንና የሌሊት መሰብሰቢያና መከላከያ ቦታ እንዲይዙ አዘዙ:: በመሆኑም ፩ኛ ብርጌድ በአፍንጮ በር በኩል የውስጥ ለውስጡን መንገድ ይዞ ቀን ጥበቃ እንዲያደርግና ማታ በቃፊሮች መረጃና ቅኝት እያደረገ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አካባቢና ዙሪያ መከላከያ ቦታ ይዞ፤ ሲታዘዝ ለመወርወር እንዲዘጋጅ፤ ፪ኛ ብርጌድ ቅድስት ሥላሴ፣ ሺህ ሰማኒያና አዋሬ መታጠፊያ መንገድ ድረስ ያለውን መከላከያ ቦታ ማታ እንዲይዝና፤ ቀን በሩሲያ መንገድ እስከ ምኒልክ ሆስፒታል ባለው መሥመር ቦታ ይዞ ቃፊር እያወጣ ቅኝት እንዲያደርግ፤ ፫ኛ ታንከኛ ስኳድሮን በ፩ኛና ፪ኛ ብርጌድ መሐል ፬ ኪሎ ፊት በር መንገድና የቸርቸል ጎዳናን እየተዘዋወረ ቅኝት እንዲያደርግ፤ መድፈኛ ሻለቃ በመድፈኛ ግቢና በአካባቢው መከላከያ ቦታ እንዲይዝ፤ ቁልፍ ቦታ ጥበቃ ላይ ያሉት ክፍሎች ጥበቃውን እንደቀጠሉ፤ ሌሎች ረዳት ክፍሎች በየሰፈራቸው ትእዛዝ እንዲጠባበቁ በጠቅላላው ቦታ ቦታቸውን ይዘው አካባቢያቸውን እየቃኙ ለተጨማሪ ግዳጅ እንዲዘጋጁ ትእዛዝ በግምባር ተሰጠና መመሪያውን መፈፀም ጀመሩ::

ከዚህ በኋላ፣ ጄኔራል መንግሥቱና ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ተገናኝተው በተጀመረው የለውጥ ሁኔታ ሳቢያ የአዲስ አበባ ከተማ ፀጥታ እንዳይታወክ፣ ሀብት እንዳይዘረፍ፣ በትራፊክ በኩልም ጉዳትና ችግር እንዳይፈጠር፣ የገንዘብ ተቋሞችንም ለመጠበቅ ስለሚቻልበት የሥምሪት ምክክር አደረጉ። ለዚህ ጉዳይም፤ የአዲስ አበባ ከተማ የፖሊስ አዛዥ የነበሩት ሌ/ኮሎኔል ጋሻው ከበደ (በኋላ ብ/ጄኔራል) ተጠሩ። በመሆኑም ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በፖሊስ እንዲጠበቁ እንዲመደብላቸው ሲደረግ፤ ጠቅላይ ገዥዎችም በያሉበት በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲያስጠብቁ ጄኔራል መንግሥቱ የፈረሙበት የቴሌግራም መልእክት ተላለፈ።

ጄኔራል መንግሥቱ ወንድማቸውን ገርማሜን እና ራስ እምሩን ጨምረው ልዑል አልጋወራሽ ወዳሉበት ክፍል ገብተው አልጋወራሹን አጅበው በማውጣት፤ የተዘጋጀውን የዐዋጅ ጽሑፍ ክብር ዘበኛ ሬዲዮ ጣቢያ ክፍል ገብተው አልጋ ወራሽ እያነበቡ ድምፃቸው በቴፕ ከተቀረጸ በኋላ፤ ታጅበው በሔዱበት ሁኔታ ወደነበሩበት ክፍል እንዲመለሱ አደረጉ። ልዑል አልጋወራሽ ድምፃቸው በቴፕ ከተቀረጸ በኋላ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እና ገርማሜ የድምፅ ማጉያ የያዙ በርካታ ጅፖች በአዲስ አበባ ከተማ ዋና ዋና መንገዶች በመዘዋወር ከቀኑ በ፯ ሰዓት ዐዋጅ የሚነገር መሆኑን ሲገልጹ እንዲያረፍዱ ትእዛዝ ሰጥተው በዚያው መሠረት ተለፈፈ። ጄኔራል መንግሥቱ ከጠዋቱ ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን፤ በቴፕ የተቀዳው የልዑል አልጋወራሽ የዐዋጅ ቃል በኢትዮጵያ ሬዲዮ ለሕዝብ እንዲተላለፍ፤ ለጋዜጣና ለፕሮፖጋንዳ መሥሪያ ቤት (በኋላ ማስታወቂያ ሚኒስቴር) ምክትል ሚኒስትር፣ ለአቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ የስቱዲዮ ሠራተኞችን እንዲያዙ፤ በሻምበል አሥራት ደፈረሱ በኩል መልእክት አስተላለፉ።

አቶ አምደ ሚካኤል "ይህ ዐዋጅ የመንግሥት ለውጥን የሚገልጽ ከሆነ ይህንን ኃላፊነት እንዴት ውስድ ይሉኛል?" በማለት እሳቸው ከመታዘዝ እንዲታለፉ ተማፀኑ። ግዴታ ከሆነ ደግሞ በልዑል አልጋወራሽ ትእዛዝ እንዲሰጣቸው ጠየቁ። ጄኔራል መንግሥቱ የሰውየው ሁኔታ አሳዘናቸውና «ፈራሁና ጠገብኩ የሚልን ማስገደድ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አትፍራ አይዞህ! እንዳልከው ከአልጋወራሽ ዘንድ ላቅርብህና እሳቸው ይዘዙህ»፤ አሉና ልዑል አልጋወራሽ ዘንድ አቀረቧቸው። አልጋወራሽም «የሚልህን አድርግ፤ ዐዋጁ ይነገር»፤ ሲሉ አዘዙዋቸው። በድንጋጤ ተውጠው የነበሩት፤ አቶ አምደ ሚካኤል ልባቸው መለስ ብሎ «ይሁን፣ ይሻላል» አሉ። ጄኔራል መንግሥቱም ግድ የለም ሌላ ነገር መጨመር እንችላለን። የትእዛዝ ደብዳቤ እጽፍልሀለሁ፤ አንተው እራስህ ቃሉ እንደሚስማማህ አድርገህ ጻፈው። እፈርምበታለሁ ብለው በማደፋፈር ሸኟቸው። መግባባት እንደተደረሰ ወዲያው የሻምበል አሥራት ደፈረሱና አቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝ ወደ ኢትዮጵያ ሬድዮ ጣቢያ አብረው ሔደው ዐዋጁ በሬዲዮ እንዲሰራጭ አዘው ተመለሱ።

ከዚያም በኢትዮጵያ ለሚገኙ ኤምባሲዎች፣ ቆንስላዎች፣ ለውጭ መንግሥታት ተወካዮችና ለመሳሰሉት በኢትዮጵያ አዲስ መንግሥት የተቋቋመ መሆኑን የሚያሳውቅ በየአድራሻቸው የሚሠራጭ ደብዳቤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እንዲዘጋጅ አዘዙ:: ይህ ደብዳቤ በአቶ ጎይቶም ጴጥሮስ (የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር) ተዘጋጅቶ፤ በአቶ ዳዊት እቁባ እግዚ (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ) ተፈርሞ የተሠራጨው ጽሑፍ፤ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት» የሚል አርማ ባለው ወረቀት ሳይሆን «የኢትዮጵያ መንግሥት» በሚል ነበር::

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ደጀዝማች ከበደ በሽምግልናው ሥራ ለመግፋት በአንደኛ ክፍለ ጦር ካሉት የዘውድ ጠባቂዎች ጋር ተነጋግረው የደረሱበትን ለመፈንቅለ መንግሥቱ አራማጆች ለመግለጽ ከጄኔራል ኢሣይያስ ገብረ ሥላሴ ጋር ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ደርሰው፤ መልሱን በጉጉት ይጠብቁ ከነበሩት ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ተገናኙ:: ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ «የሔዱበት ጉዳይ እንዴት ሆነ?» የሚል ጥያቄ እንዳቀረቡላቸው፤ «ሜጀር ጄኔራል መርዕድ አልመጣም ብሏል:: ጄኔራል ኢሣይያስን ግን ይዤው መጥቻለሁ» አሉና መልስ ሰጡዋቸው:: ወዲያው የመጡበትን ጉዳይ ለመፈጸም ጄኔራል ኢሣይያስ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ሐሳብ መለዋወጥ ሲጀምሩ፤ «ምንድን ነው ምክንያቱ ነገሩስ እምን ደረጃ ደርሷል?» ብለው ጄኔራል መንግሥቱን ጠየቋቸው:: እሳቸውም ወታደሮቹና መኮንኖቹ በደሞዝ በጣም የተቸገሩ መሆናቸውን መግለጽ ሲጀምሩ፤ ጄኔራል ኢሣይያስም «የደመወዙን ነገር በምክር ማሻሻል ይቻላል:: ስለምን በደመወዝ ምክንያት ይህን ያህል ግርግር ይደረጋል?» ብለው በድጋሚ ጠየቁ:: ጄኔራል መንግሥቱም «አንተ አልገባህም፤ ለብቻህ ላነጋግርህ» ብለው ወደ አንድ ክፍል አስገብተው፣ «ልዑል አልጋ ወራሽ ሜጀር ጄኔራል መርዕድንና ሜጀር ጄኔራል ከበደን ለማነጋገር ስለሚፈልጓቸው ሒድና ነግረህ አምጣቸው» ብለው ነገሯቸው:: ጄኔራል ኢሣይያስም «ልዑል አልጋ ወራሽ ሳይነግሩኝ የእርሳቸው ትእዛዝ ነው ብዬ አልናገርም" በማለታቸው፤ ጄኔራል መንግሥቱ ልዑል አልጋ ወራሽ ወደሚገኙበት ክፍል ይዘዋቸው ገቡ:: ከዚያም፣ «ግርግሩ ምንድን ነው? በቀለብና በመሳሰለው ነገር ከሆነ፣ ከአማካይ ቦታ ተገናኝቶ በርጋታ ተነጋግሮ መንገድ መክፈት ይቻላል» ብለው ጄኔራል ኢሣይያስ ሐሳብ ሰነዘሩ:: ይሄኔ ጄኔራል መንግሥቱ ችግሩ እንደተገለጸው አለመሆኑን በመጥቀስ፤ ለብቻ ወስደው መውደቅ ስለሚገባው ብልሹ አስተዳደር፣ መተካት ስለሚኖርበት የተሻለ አስተዳደር ለውጥ፣ በጦሩ፣ በተማረው ክፍል፣ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና ከሕዝብ በተውጣጣ ኮሚቴ ለውጡ የሚመራ መሆኑን፤ ስለእንቅስቃሴው ዐላማና ፍላጐት በግልጽ አስረዷቸው:: ጄኔራል ኢሣይያስም፣ የእንቅስቃሴውን ዐላማ ከተረዱ በኋላ ነገሩን በሽምግልና ዓይቶ መፍታት አስፈላጊ መሆኑን አምነው የሽምግልናው ሁኔታ ፍፃሜ ሳያገኝ የችኮላ ነገር እንዳይከሰት አሳስበው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ለመሔድ ወጡ::

ጄኔራል ኢሣይያስ በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ከጄኔራል መንግሥቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር ተገናኝተው ስለሁኔታው ከተረዱ በኋላ፤ ጄኔራል መርዕድና



ብ/ጄኔራል ኢሣይያስ ገብረ ሥላሴ

ጄኔራል ከበደ ገብሬ በአልጋ ወራሽ የተጠሩበትን መልእክት ይዘው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔዱ። እዚያ እንደደረሱ ሁለቱ ጄኔራሎች በጄኔራል ኢሣይያስ የመጣውን መልእክት ከሰሙ በኋላ፤ በግንባር ተገናኝቶ መነጋገሩን እንደሚደግፉት በመግለጽ፤ የመንፈስ አባቶች በጉዳዩ እንዲገቡበት በቅደሚያ ከፓትሪያርኩ ጋር እንዲነጋገሩ መንገዱን ጠርገው ሐሳብና ትእዛዝ አጣምረው ሰጥተው መልሰው ላኩዋቸው። ጄኔራል ኢሣይያስ በትእዛዙ መሠረት ፓትሪያርኩን አነጋግረው፤ ሽምግልና የሚያውቁ አምስት ጳጳሳት ተመርጠው ስለተሰጣቸው፤ የማስታረቅ ሥራ እንዲጀመር ጳጳሳቱን ይዘው ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ሔዱ።

ጳጳሳቱ ከፓትሪያሪኩ ግቢ ወጥተው ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ የሚሔዱበት ተልዕኮ፣ ከጄኔራል መንግሥቱና ከልዑል አልጋወራሽ ጋር በመገናኘት እነሜጀር ጄኔራል መርዕድ በሽምግልናው ለመግፋት መፈለጋቸውን አስታውቀው፤ ለማሸማገል የቀጠሮ ቀን ለመያዝና ቦታ ለመወሰን፤ እንዲሁም በውይይቱ የክብር ዘበኛን የሚወክሉ ሰዎች ተመርጠው እንዲሰጡዋቸው ለመጠየቅ ነበር። ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ እንደደረሱ ጄኔራል መንግሥቱን ከፎቅ መውጫው ደረጃ ላይ ስላገኟቸው፤ የመጡበትን ጉዳይ አስረዱ። ይኸውም፣ «ደም መፋሰስ እንዳይኖርና ሁከት እንዳይፈጠር በክብር ዘበኛና በጦር ሠራዊት መካከል ስምምነት እንዲደረስ ሽምግልና ለማካሔድ ከአቡነ ባስልዮስ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ) ተልከው መምጣታቸውንና ቀጠሮውም ለሐሙስ ታኅሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. በ፱ ሰዓት በፓትሪያርኩ መኖሪያ ግቢ ውስጥ እንዲሆን በእነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ በኩል በግንባር ተገናኝቶ የመነጋገሩን አስፈላጊነት ያመኑበት መሆኑን ጳጳሳቱ ገልጸው፤ «በእናንተስ በኩል ምን ትላላችሁ?» አሏቸው። ጄኔራል መንግሥቱም ሐሳቡን በመቀበል፤ ሕዝብ የገጠመውን ችግር ለጳጳሳቱ ገልጸውና ችግሩ እየተባባሰ በሔደ ቁጥር ኃላፊነት የሚሰማው ሰው እያወቀ እንዳላወቀ፤ እያየ እንዳላየ፤ በዝምታ መኖሩ ከባድ የኅሊና ሸክምና ፈታኝ ጥያቄ መሆኑን አስረዱ። አባቶችንም

> እናንተም ሳትቀሩ የቤተክርስትያን በር ስለዘጋችሁ፤ ቀድሞ በቤተክርስትያን ጥግ ያድሩ የነበሩ ድሆች መጠጊያ በማጣት አውሬ ይበላቸዋል። ይኸን ሁሉ ችግር ምን አገባኝ? ለምን እንደፈለገ አይሆንም? ብለን፤ የራሳችንን ምቾትና ድሎት እያበጀን፤ በጊዜው መታረም



ብ/ጄኔራል ኢሣይያስ ገብረ ሥላሴ

የሚገባውን በቸልታ ብንተው፤ እራሱ ሁለተኛ ችግር ይሆናል። በቅንነት የጀመርነው ነገር ስለሆነ፤ ሁላችንንም ያገባናል። ጥያቄያችሁን እቀበላለሁ።

አሉ።

ጳጳሳቱ «ቤተክርስትያን በሯን ስለዘጋች ድሆች መጠጊያ አጥተው አውሬ ይበላቸዋል» ብለው ጄኔራል መንግሥቱ በተናገሩት ቃል ቅር ተሰኙ። ይህ የቅሬታ መንፈስ በሁሉም ልቦና ቢሰነቀርም፤ ቅሬታቸውን ዋጥ አድርገው «ከእናንተ ዘንድ ሰዎች እንዲሰናዱ» ብለው ሐሳብ አቀረቡ። ጄኔራል መንግሥቱም የሚሰናዱት ሰዎች ምን የሚያደርጉ እንደሆኑ ጳጳሳቱን ሲጠይቁ፤ ጳጳሳቱም «በጦር ሠራዊቱና በእናንተ መካከል እርቅ እንዲወርድ ፓትርያርኩ ግቢ ሔደው ደም እንዳይፋሰስ እርቁን የሚደራደሩ ናቸው» አሏቸው። እሳቸውም በበኩላቸው፣ «እንኳንስ የሰው ደም የእንስሳ ደም ቢፈስ አልወድም። ጥሩ ነው» አሉ። በነጋታው ሐሙስ በ፬ ሰዓት ከአቡነ ባስልዮስ መኖሪያ ግቢ እነዚሁ በክብር ዘበኛ በኩል የሚመረጡትን ሰዎች ጄኔራል ኢሣይያስ መጥተው ይወስዷቸዋል ብለው ጳጳሳቱ ተሰናብተው ሔዱ።

ጄኔራል መንግሥቱ ወዲያው ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህን ጠርተው፤ በክብር ዘበኛ በኩል እርቁን የሚደራድሩ እነማን ቢሆኑ እንደሚሻል ሲነጋገሩ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እኛ እንመርጣለን አሉ። ይሑን እንጂ ጄኔራል መንግሥቱ ከክፍሉ ከመውጣታቸው በፊት ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እርቁ ይሳካል ተብሎ ተስፋ የማያስጥሉ በርካታ መረጃዎች መኖራቸውን ቁርጥ ባለ ቃል ገለጸላቸው። ምክንያቱም እኔ የዚህ ታሪክ ጸሐፊም እዚያው ሁኜ እንዳየሁት፤ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ጦር ሠራዊቱ ከየጠቅላይ ግዛቱ ወደ አዲስ አበባ በፍጥነት እንዲመጣ ጠዋት ያስተላለፏቸውን የሬዲዮ መልእክቶች ከራሱ መሥሪያ ቤት የመቶ አለቃ ተድላ (በኋላ ጄኔራል) እና ከጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ዓለም አቀፍ የሬድዮ መገናኛ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የተጠለፈውን መልእክት ደግሞ የመቶ አለቃ ታምሩ የማነ ብርሃን አምጥተው ሰጥተውት ተመልክቶታል። ስለዚህ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከዘውድ ጠባቂው ወገን ምን እንደታቀደና ምን እየተዘጋጀ እንደሆነ በተጨባጭ ማስረጃ እየታወቀ እያለ፤ በዚህ ወገን ትኩረት ተሰጥቶ መከናወን ያለበት የሽምግልናው ድርድር እንዳልሆነ፤ ለጄኔራል መንግሥቱ አጠናክሮ አስረዳቸው። ምን አልባት መግባባት ላይ ተደርሶ የማይፈለገውን ደም መፋሰስ ለማስቀረት በመፈለግ እንጂ፣ ጄኔራሉም የሁኔታውን አሳሳቢነት ሳይረዱት ቀርተው አልነበረም። ሆኖም "እናመጣቸዋለን" በማለት ይነጋገሩ ከነበሩበት ክፍል ወጥተው ሔዱ።

በመቀጠልም፣ ሲዘጋጅ ያረፈደውና በልዑል አልጋ ወራሽ ድምፅ የተቀረፀው ዐዋጅ ቀስቃሽ በሆነ ወታደራዊ ማርሽ ታጅቦ ከቀኑ ፯ ሰዓት ሲሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሬዲዮ ይተላለፍ ጀመረ። በመጀመሪያ ሙዚቃ ጣልቃ እየገባ ይደመጥና በመደጋገም፤ «ይህ ዛሬ የማሰማችሁ ድምፅ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ የልዑል መርዕድ

አዝማች አስፋወሰን ድምፅ ነው። ዐዋጅ!» እያለ ለጥቂት ደቂቃዎች ሲነገር ቆይቶ፤ የልዑል አልጋ ወራሽን የዐዋጅ ቃል ማሰማት ይቀጥላል። የዐዋጁ ሙሉ ቃልም፦

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ፫ ሺህ ዓመታት በላይ የሆነ የሚታወቅ ታሪክ አለው። ነገር ግን፣ በዚህ ረጅም ዘመን ውስጥ ገበሬው ከቀንበር፣ ከሞፈር፣ ከድግር የእርሻ መሣሪያው፤ ነጋዴው ከችርቻሮ፣ ሌላው በልዩ ልዩ ሙያ የሚተዳደረው አባቶች ካቆዩለት የአሠራር ዘዴ ያልወጣ፣ በጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድህነትና ከድንቁርና የኑሮ ደረጃ እስከዛሬ ሊወጣ አልቻለም። የአስተዳደሩ ዐላማም ሕግንና ሥርዓትን መሠረት አድርጐ የሕዝብ መብት መጠበቂያ መሆን ሲገባው፣ የጥቂቶች የግል ጥቅም ማበልፀጊያ የወገን መጥቀሚያ የሕዝብ መበደያና መጨቆኛ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ቀረ።

ታጋሹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከጭቆና፣ ከድህነትና ከድንቁርና ያልወጣበት "ከዛሬ ነገ በር ይከፈትልኛል" በማለት፣ ያለፉት ዘመናት ሁሉ ያልሻሩትን በማንም የሌላ አገር ሕዝብ ታሪክ የማይገኘውን በተስፋ የመቆየት ችሎታውን አሳየ። ነገር ግን፣ ድንቁርናን ከመካከላቸው አጥፍተው በአእምሮአቸው መራቀቅና በኑሮ ደረጃቸው እየገፉ ከሚሔዱት የዓለም ሕዝቦች የኑሮ ደረጃ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያደርሰው የሚችል የማይፈፀም የቃል ተስፋ መስማት ሳይሆን እውነተኛ ተግባር ላይ የዋለ የሕዝብ የአእምሮና የኑሮ ዕድገት የአገር ልማት ፕሮግራም እስከዛሬ ተዘርግቶ ካለማየቱ በላይ፤ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ነፃነታቸውን ያገኙ የአፍሪካ አገሮች እንኳን ሳይቀሩ በሚፈፅሙት የሥልጣኔ እርምጃዎች ሳይቀር የኢትዮጵያን ሕዝብ እየቀደሙና ወደኋላቸው እየጣሉ ወደፊት የሚገሰግሱ መሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕለት በዕለት ግልጽ እየሆነለት ሔደ። ይህም ሁኔታ ከአለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያን ሕዝብ የረጅም ዘመን ተስፋ መጨረሻ ደረጃ ላይ አደረሰው። በገበሬው፣ በነጋዴው፣ በሙያተኛውና በልዩ ልዩ ተግባር በሚተዳደሩ ሠራተኞች፣ በጦር ክፍሎች፣ በፖሊሶችና በተማሩ ወጣቶች በአጭሩ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል እጅግ ከፍ ያለና የተስፋፋ እንቅስቃሴ ተፈጠረ።

ይህን የሕዝብ መነሣሣት ለማፍረስ ብዙ ሙከራ ተደርጐ ነበር። ነገር ግን፣ ቀፎው ተነክቶበት የተሸበረ ንብና ተስፋውን ጨርሶ የተነሣ ሕዝብ ተመሳሳይ በመሆኑ፣ የተፈፀመው ሙከራ ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ድሮው የተገዥነት ቦታው ለመመለስ አልቻለም። ይህም ከመሆኑ የተነሣ፣ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ የተጀመረው የሕዝብ እንቅስቃሴ፣ እነሆ ዛሬ ሥልጣንን ጥሶ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገሪቱም መድኅን ከመሆን ደረጃ ላይ መድረሱን ልገልጥላችሁ ዕድል በማግኘቴ ደስታዬ ፍጹም ነው።

እስከዛሬ ድረስ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገት እንቅፋት ሆነው የኖሩት የጥቂት ሰዎች፣ ለሀብት ያላቸው ፍላጐት መቻውንም ቢሆን ሊረካ የማይችል ጥሪትና ትውልድን ብቻ መከታ በማድረግ ሥልጣንን በመሻማት፣ ሕዝብን መከፋፈል፤ እነዚህ ሁለቱ የእትዮጵያ ሕዝብ የኑሮ ነቀርሳ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ ከዛሬ ጀምሮ በሀብት በኩል እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ሆኜ በሚቀረጥልኝ ደመወዝ ብቻ የምተዳደር፣ በሥልጣን

በኩል እውነተኛውን ሕገ መንግሥት መመሪያ በማድረግ አገሬንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማገልገል ፍጹም በሆነ ቅን ልቦና ወስኛለሁ።

የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት፣ በእኔ በራሴ፣ በጦር ክፍሎች፣ በፖሊስ ሠራዊት፣ በተማሩ ወጣቶችና እንደዚሁም በኢትዮጵያ ሕዝብ የተደገፈ ስለሆነ፤ የሚደረገው ሹምሽርና ሌላው ማንኛውም ዓይነት ውሳኔ የፀና ይሆናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ በዓለም ፊት ተገቢ የሆነውን ግርማ ሞገስ የሚያጐናጽፈውን ክብር የሚያስገኝልህ እውነተኛ ታሪክህ የተጀመረው ዛሬ መሆኑን ዕወቅ፤ ኀብረትህ ክብረት የጠነከረ ይሁን!

የሚል ሲሆን፤ ከልዑል አልጋ ወራሽ ድምፅ ቀጥሎ የዐዋጁን ሙሉ ቃል የያዘው ወረቀት በመቶ አለቃ በቀለ ሠጉ፣ በሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌና በመቶ አለቃ አበበ ካሣ በከተማው ተበተነ። ሕዝቡም መፈንቅለ መንግሥት መካሔዱን በማያጠራጥር ሁኔታ ተረዳ።

የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያም፣ የአቶ ዳምጤ አሰማኸኝን «አለ...ቀ! ደቀ...ቀ.ቀ.ቀ! የባርነት ቀንበር ወደ...ቀ!» የሚለውን መግለጫ በመደጋገም በወታደራዊ ማርሽና በሙዚቃ እየታጀበ ቀኑን ሙሉ እየደጋገመ ሲያስደምጥ ዋለ። በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብን ስሜት በተለያየ መንፈስ ለውጦ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆነ። ግማሹ ድጋፉን በደስታ ሲገልጥ፤ ቀሪው ጥርጣሬ በተሞላበት መንፈስ «ልዑል አልጋ ወራሽ ዐዋጁን የተናገሩት ተገደው ሳይሆን አይቀርም» የሚል አስተያየት ይሰጥ ጀመረ። አንዳንዶቹ ታዛቢዎች ደግሞ፣ ዐዋጁን ሲናገሩ እንደተደመጠው «የአነጋገር ቃና ቅላፄያቸው ሥልታቸውና የትንፋሽ አወራረዳቸው ግዳጅ ያለበት አይመስልም"፣ "ንጉሡ ለጉብኝት በሔዱበት ልጃቸው አልጋ ወረሱ»፣ «ክብር ዘበኛ ዝም ብሎ ማየት አልነበረበትም» «ጦር ሠራዊቱም ‹ያለነው እኛ የሞትነውም እኛ› እንደሚባለው ጦርነት ቢነሣና ሰው ቢያልቅ ጉዳቱ የሕዝብ ነው የሚሆነው አለ» የሚሉ አስተያየቶች ነበሩ። ሌላው ደግሞ «ንጉሡ ለአገራቸው ብዙ ደክመዋል። ድርጊቱ ክዳት ነው» የሚሉም ነበሩ።

በአገር ውስጥ ሁኔታው ይህንን ሲመስል፤ በውጪ፣ በልጅ እንዳልካቸው መኮንን የሚመራው ለንደን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ የዐፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመደገፍ አቋሙን ሲያሳውቅ፤ በአምባሳደር ተፈሪ ሻረውና በአንደኛው ጸሐፊ በአቶ አባተ አግዴ የሚመራው፣ በስዊድን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ደግሞ አዲስ የተቋቋመውን ሕዝባዊ መንግሥት በመደገፍ አቋሙን ገልጾአል። ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች፣ በተለይ አምባሳደር ተፈሪ ሻረው መግለጫ ለመቀበል የመጡትን ጋዜጠኞች ሲቀበሉ፤ እጆቻቸውን በደስታ ወደ ላይ ከፍ አድርገው በማንሳት "ነፃነት! ዲሞክራሲ!" በማለት መፈክር አሰምተዋል። «አዲስ የተቋቋመው መንግሥት የኮሚኒስት ዝንባሌ አለው?» ተብለው ሲጠየቁም፤ «የለውም» በማለት አስተባብለዋል፤ ተብሎ ተነግሯል። የዕለቱ የስዊድን ጋዜጦችም «ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በእንግሊዝ፣ በስዊድንና በአሜሪካ ባንኮች ከፍ ያለ ገንዘብ አካብተዋል» ብለው አምባሳደሩ ከሰዋል ሲሉ ጽፈዋል።

የዐዋጁ ዜና ወደ ተለያዩ አገሮችም መዳረሱ አልቀረም:: ለምሳሌ ግሪን ፊልድ በጻፈው መጽሐፍ[32] በለንደን አውሮፕላን ጣቢያ አካባቢ ለአንድ ሬዲዮ ተነጋጋሪዎች ክበብ አባል የጥሪ ምልክት ET 3 XY Addis Ababa፤ የልዑል ሣኅለ ሥላሴ መልእክት የሚል የአማተር ሬዲዮ ተነጋጋሪዎች ክበብ አባል፣ «የ፷፰ ዓመቱ የኢትዮጵያው ንጉሥ (በመፈንቅለ መንግሥት) ተገለበጡ» የሚል መልዕክት ለመጀመሪያ ጊዜ ደረሰ:: የተቀበለውም የ፶፫ ዓመቱ የክለቡ ጋዜጠኛ ጆሴፍ ታይረል የተባለ ሰው ነበር:: ይህ ሰው ተቀብሎ ያስተላለፈው የወሬ ብልጭታ፣ በእንግሊዝና ከዚያም ወደ ተለያዩ አገሮች እየተጠናከረ ተሠራጭቷል:: ልዑል ሣኅለ ሥላሴ ያስተላለፉት መልእክት በዲፕሎማሲው በኩልም የዕውቅናውን ጥያቄ መንግሥታት እንዲያስላስሉትና በየአገሩ የሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችን ማብራሪያ እንዲጠይቁ ገፋፍቷቸው ነበር:: ማክሰኞ ለረቡዕ አጥቢያ በአዲስ አበባ መፈንቅለ መንግሥት እየተካሔደ መሆኑን፤ የአውሮፕላን ማረፊያው አካባቢ በወታደር የሚጠበቅ መሆኑን፤ ወደ ቤተ መንግሥት የሚያመሩ መንገዶች መዘጋታቸውን፤ እንዲሁም የመገናኛ መሥመሮች ሥራ ማቆማቸውን፤ ለመንግሥቱ አስታውቆ የነበረው የአሜሪካ ኢምባሲም ዐዋጅ ከተነገረ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ ጥሩ መሪ ይሆናሉ" የሚል እምነት ባይኖረውም፣ ለሚፈለገው የፖለቲካ ለውጥ እንቅፋት አይሆኑም የሚል ግምት እንዳለው ለመንግሥቱ አስታውቆ ነበር::

በአጠቃላይ ዐዋጁ የለውጥ መንፈሱን አማሙቆት እንዳለ፤ በወቅቱ በቦታው ተገኝቼ እንዳስተዋልኩት ከተለያዩ አስተያየት አቅራቢዎች ልዑል አልጋወራሽ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ሆነው ዐዋጅ እንዲናገሩ መደረጉ፤ የዐዋጁን ታማኝነት ጥርጣሬ ላይ ይጥለዋል እያሉ መምከር ብቻም ሳይሆን፤ የተያዙት ባለሥልጣኖችን የለውጡ ተቃዋሚዎች ይለቀቁ እያሉ ስለሆነ፤ ለሽምግልናው ጥረት እንቅፋት እንዳይሆን እየተባለ ግፊት ይደረግ ነበር:: ደጃዝማች ከበደም «ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ቤታቸው ወይም ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት እንዲገቡ ቢደረግ ይሻላል» ብለው ስላሳሰቡ፤ ጄኔራል መንግሥቱ በሐሳቡ በመስማማት ልዑል አልጋ ወራሽን ከክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት መውሰጃ መኪና እንዲቀርብ ለኮሎኔል ሉሉ እንግሪዳ የቤተ መንግሥቱ የተሽከርካሪና ሠረገላ ክፍል ምክትል ኃላፊ ትእዛዝ ተሰጥቶ፤ ሮልስ ሮይ መኪና ይዘው ሲመጡ፤ ሰንደቅ ዐላማ ባለመያዛቸው ቶሎ ሔደው እንዲያመጡ ታዘው በማምጣት፤ ልዑል አልጋ ወራሽ በአገር መሪ ደረጃ ሰንደቅ ዐላማ እያውለበለቡ ከልዑል ራስ እምሩ ጋር ወደ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት እንዲገቡ ተደረገ:: በዚህ የጥድፊያ ጊዜ የፖሊስ ሞተረኞችን ማሰባሰቡ ጊዜ የሚወስድ ስለነበረ፤ ልዑሉ የታጀቡት በክብር ዘበኛ ሞተረኞች ነው::

ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ገነተ ልዑል ከመሔዳቸው በፊት፣ ጄኔራል መንግሥቱ ለልዑል አልጋ ወራሽ ‹‹ደም እንዳይፈስ ማድረግ የሁላችን ኃላፊነት ነውና እነ ጄኔራል መርዕድ ሊመጡ ተነጋግረናል:: እንዲመጡ ቢደረግ መልካም ነው››

---

[32] *Greenfield, R.* ***Ethiopia A New political History*** *ገጽ ፩፻፩ - ፩፻፫*

ስላሉዋቸው፤ ልዑሉም «ደግ ነው ደጃዝማች ከበደ ሒድና የእኛንም ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት መግባት ነግረህ ይዘሃቸው ና» በማለት ትእዛዝ ሰጡ። ልዑል ራስ እምሩ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ እዚህ እንዲመጡ ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ቅሬታቸውን ለጄኔራል መንግሥቱ አቅርበው እንደ ነበር፤ ደጃዝማች ከበደ ለፍርድ ቤቱ በሰጡት ቃል እንዲህ በማለት ገልጸዋል።

> ልዑል አልጋ ወራሽ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድን እዚህ እንዳመጣ አዘውኝ ልሔድ ስል ልዑል እራስ እምሩ፣ ምን አምነው ነው ወደዚህ የሚመጡት። ላይ ላዩን ለምን እንነጋገራለን። ለዚህ ጉዳይ ዋናዎቹ እነማን ናቸው?። አንነጋገርም ወይ? እዚህ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትም ሆነ የእናንተ ቢሮ ጥበቃ የሚደረገው በእናንተ ሰዎች ነው። ምን አምነው ነው የሚመጡት? ነገሩን ገልጠን ብንነጋገርና ደም እንዳይፋሰስ ራሳችንም መሥዋዕት መሆን አለብን

በዚህ ጊዜ ጄኔራል መንግሥቱም "እንዴት! እነ ጄኔራል መርዕድ እዚህ ቢመጡ ምን እንዳይሆኑ ነው እኔ አልታመንም?" በማለት በቁጣ ተናገሩ። ልዑል ራስ እምሩም፣ «ይኸንን እኔ አላውቅም» አሉና ዝም አሉ።

ደጃዝማች ከበደ ጣልቃ ገብተው «እሺ ሲሉ ይመጣሉ፤ እምቢ ቢሉ መልሱን ይዤ እመጣለሁ» ስላሉ፤ ሁሉም በዚሁ ተስማሙ። ደጃዝማች ከበደም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ለመሔድ ሲነሡ ግን፤ ጥቂት ወታደሮች ከበብ ከበብ አድርገዋቸው ቆሙ። ይሄኔ ራስ እምሩ ያደረባቸው ጥርጣሬ ደጃዝማች ከበደንም ተሰማቸው። ስለዚህ ነው ከበብ ከበብ መደረጋቸውን ተከትሎ ደጃዝማች ከበደ «ያችን የአሰፋ ገ/ማርያምን መጽሐፍ አንብበሃል?» ሲሉ ጄኔራል መንግሥቱን የጠየቁት። ጄኔራሉም «የትኛዋን?» «ስሟ ለዚህ ይጠቅማል» ሲሏቸው፤ «ያች እንደወጣች ቀረች የምትለዋን» ብለው መለሱላቸው። ጄኔራል መንግሥቱም «የለም! ደጃዝማች እንዲህ ያለው ነውር አይታሰብም። አይሥጉ» ብለው እምነታቸውን ስለሰጧቸው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር መሔዳቸውን ይገልጻሉ።[33]

በዚህ መኻል ልዑል አልጋ ወራሽ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ገቡ። ደጃዝማች ከበደም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔደው እዚያ እንደደረሱ መኳንንቱ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ነበሩና፣ መጀመሪያ ከልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ጋር ሲገናኙ «እንደምን መጡ?» ይሏቸዋል። ደጃዝማችም «እነ ሜጀር ጄነራል መርዕድን ልወስድ ነው። ልዑል አልጋ ወራሽም ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ገብተዋል። ደህና ናቸው። ይዘሃቸው ና ብለውኝ ይህንን ነገሬ ልወስዳቸው ነው የመጣሁት» የሚል መልስ ሰጡ። ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣም፤ «አይሆንም! የጃንሆይን መንግሥት ገልብጠናል እያሉ ዐዋጅ እያወጁ

---

[33] የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ለህትመት በተዘጋጀ የታሪክ ማስታወሻ ገጽ ፲፩። ከዚህ ማስታወሻ ላይ ልጃቸው ዶ/ር ካሣ ከበደ ለእኔ ጉዳይ እንዲጠቅመኝ መርጦ የላከልኝን ሦስት ገጽና የራሱ ደብዳቤን በአባሪነት አያይዤአለሁ።

እንደምን ተብሎ ነው እነሜጀር ጄኔራል መርዕድ ወደዚያ የሚሔዱት?» በማለት ቆጣ ብለው ሲናገሩ፤ ሁሉም በትዝብትና በመገረም እንዳዩዋቸው ይገልጻሉ። በመቀጠልም

> መልእክቱን ስናገር፤ እኔ በፊት ያልሰማሁትና ያላወኩት በኋላ እቤቴ በደረስኩ ጊዜ የሰዓት ሬድዮ ዜና፤ የአልጋ መገልበጥ ጉዳይ ተነሣና ንግግር ተደረገ። የዐዋጁን ቃል አሁን ወደዚህ ስመጣ ነው እንጂ ከዚያ በፊት አልሰማሁም ብዬ የነገሩን ሁኔታ አነሣሁና ንግግር ስጀምር፤ ጄኔራል መርዕድ በንግግሬ መሐል ጣልቃ ገባና፣ አሁን ከሰሙና ካወቁት በኋላ ምን ማድረግ ይቻላል?» ሲል ጠየቀኝ። «ምክር የምሰጠው እንደሁኔታው ነው» አልኩትና «የጦራችሁ ኃይል እንዴት ነው» ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ፤ አሁን ባለንበት ሁኔታ የነርሱ ድርጅት ብልጫ ያለው ነው። ነገር ግን እነርሱ የሌላቸው እኛ ታንክ አለን። ያለውም ናዝሬት ስለሆነ እንዲመጣ አዘናል። እንደደረሰ የኛ ኃይል ይበልጣል። አየር ኃይልም ከኛ ጋር ነው"። ብሎ መለሰልኝ። እኔ እንደገባኝ «አሁን የተሰለፈው የክብር ዘበኛ የአልጋ መገልበጥ መሆኑን ያወቀ አይመስለኝም እና የፓትርያርኩን ምክርና ውግዘት ቃል የያዘ መልእክት ተጽፎ ቢበተን ይሻላል ስል ሐሳብ ስላቀረብኩ፤ ሻለቃ አሰፋ ለማ (በኋላ አምባሳደር) እና እኔ እንድናዘጋጅ ተወሰነና አዘጋጅተን ወረቀቱ በአቡነ ባስልዮስ ማኅተም ታትሞ ተበተነ"።[34]

በማለት ደጃዝማች ከበደ ይተርካሉ። ይህ ግን የሻለቃ ጠለለ ቸርነት ወረቀቱ አሥመራ ታትሞ በአውሮፕላን ተበተነ ካለው ጋር ይጣረሳል።

ከዚህ በመቀጠል የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት እስከ ንጋቱ ፲፪ ሰዓት የሰዓት እላፊ ዐዋጅ አወጡ። ጊዜው እየመሸ ሁሉም በመዳከም ላይ እንዳለ፤ አቶ ከተማ ይፍሩ ይዞት በነበረው ትንሽ የባትሪ ሬዲዮ ቢ.ቢ.ሲ. በአንድ ሰዓት በሰጠው ዜና፤ ንጉሡ በአገራቸው መፈንቅለ መንግሥት መካሔዱን መስማታቸውንና ወደአገራቸው ለመመለስ መቁረጣቸው ተሰማ። ልዑል ራስ እምሩም ተመሳሳይ ሬዲዮ ይዘው ስለነበር፤ ዜናውን ሰምተው ለጄኔራል መንግሥቱ ገለጹላቸው። ጄኔራል መንግሥቱ ልዑል ራስ እምሩን «እውነት ይመጡ ይመስሎዎታል?» ሲሉ ጠየቋቸው። ልዑል ራስ እምሩም «አዎ ይመጣሉ» ሲሉ መለሱ። ጄኔራል መንግሥቱም "አዎ ደፋር ናቸው። አውቃለሁ ሲሉ መለሱ።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ከምሽቱ አንድ ስዓት ተኩል ላይ፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እኔን ለሁለተኛ ጊዜ «አሜሪካን ኤምባሲና እሥራኤል ቆንስላ ጽሕፈት ቤት ሔደህ አስተያየታቸውን ሰምተህ መጥተህ ንገረኝ» ብሎ አዘዘኝ። እኔም እሥራኤል ቆንሲላ ጽሕፈት ቤት ለክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ በጣም ቅርብ ስለነበር (ኤምባሲ አልተከፈተም ነበር) ሚስተር ባሮን ቤት ሔድኩ። ቤቱና ቢሮው አንድ ላይ ነበር። ቆንስላው መምጣቴን ከዘበኛው ሰምተው ከግቢው መግቢያ በር ድረስ መጥተው

---

[34] ዝኒ ከማሁ

በመቀበል ወደ ቤት ካስገቡኝ በኋላ በመደነቅ እያዩ፤ እንድቀመጥ ጋበዙኝ። አሁንም በመጀመሪያው ግንኙነታችን ያሉትን አስፍተውና አጥብቀው እንዲህ ሲሉ ደገሙልኝ። ብርሃኑ! እኔ ነገሩ ሁሉ አልገባኝ ብሏል! ጄኔራል መንግሥቱን የምንገምተው በዓለማዊነት ነበር። የፖለቲካ ፍላጐት አላቸው ብለን አንገምትም ነበር። ይገርማል!» አሉኝ። ስለ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህም «እውነት ወርቅነህ በዚህ ነገር አለበት?» ሲሉ ደግመው ጠየቁኝ። እኔም፤ አዎ! አለበት አልኳቸው። «እኔ አልመሰለኝም። ወርቅነህ ካለበት እንዲህ ያለ ሥራ ይሠራል ብዬ አላምንም፤ ወርቅነህን በሚገባ አውቀዋለሁ» አሉኝ። እኔም ምኑን ነው የሚያውቁት? አልኳቸው። እሳቸው ግን ለጥያቄዬ ቀጥተኛ መልስ ሳይሰጡ

"እእ...እ...እ" ብለው ንግግራቸውን በመቀጠል "ስማ ብርሃኑ! አየር ኃይሉንና ጦር ሠራዊቱን ሲሆን በሙሉ ከእናንተ ጋር እንዲሆን ካልሆነም እንዲከፋፈል ሳይደረግ፤ ከሁሉም የሚደንቀው እንዲህ ያለ ነገር ሲደረግ ፓትርያርኩን አለመያዝ እንዴት ያለ ሥራ ነው? የኢትዮጵያን የአገራችሁን ነገር አታውቁም ማለት ነው? ሌላው ደግሞ ሊቃነ ጳጳሳቱ መምሪያችሁ ድረስ ሲመጡ አለመያዝ፣ ወይም የናንተ ተባባሪ እንዲሆኑ አለማሳመን በግድ የለሽነት መልቀቅ ምን ማለት ነው? ምንድን ነው የሚሠራው ሥራ? እውነት በዚህ ነገር ወርቅነህ አለ! ወይም በፈቃዱ እየሠራ ነው ብዬ አላምንም! ሰውዬውን ጠንቅቄ ስለማውቀው ይህን ሁሉ እሱ እያወቀው ነው፤ የሱ ሥራ ነው ብዬ አላምንም። በል አሁንም ቢሆን ጅምሩ ውጤት እንዲያገኝ ከተፈለገ ሁለቱ ጄኔራሎች ዛሬም ቢሆን ሳይያዙ ማደር የለባቸውም።

# የጦር ሠራዊት ቀጣይ የተቃርኖ ዝግጅት

ሜጀር ጄኔራል መርዕድና ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ በተቃርኖ ለመቀጠል ያለውን በቁጥር ጥቂት የሆነውን ጦር ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ፣ በአንደኛ ክፍለ ጦር ዙሪያና በባቡር ጣቢያ አጠገብ ያለውን አደባባይ እንዲይዝ በማድረግ ላይ እንዳሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ ከቤታቸው ተነስተው ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ ሔደው ከልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅና ከሌሎችም ባለሥልጣኖች ጋር ተገናኝተው ሌሊቱን ተመካክረው ጠዋት አንደኛ ክፍለ ጦር በመሔድ ከሜጀር ጄኔራል መርዕድ ጋር እየተደረገ ስለነበረው ሁኔታ ተነጋገሩ። የንግግሩ ፍሬ ነገርም ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ለጊዜው ባለው ኃይል የክፍለ ጦሩን ዙሪያ እያስጠበቁ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ላይ የተነሣውን ሤራ ለማክሸፍ ቀጣይ ዝግጅት እያደረጉ መሆናቸውን ያስረዷቸው ሲሆን፤ ልዑል ደጃዝማች ዐሥራተ ካሣም በበኩላቸው ዐመፅ በአዲስ አበባ ስለመደረጉ በዙሪያው የሚገኙ የአውራጃ ገዥዎች ሁሉ እንዲያውቁት፣ በተለይም ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በለሊት ወደ ደብረ ብርሃን ወጥተው ሕዝብ እንዲቀሰቅሱና




ራስ አሥራተ ካሣ

እንዲያነሣሱ ስለመንገራቸውና የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ሕልውና ለመጠበቅ ሤራውን ለማክሸፍ ወደ ኋላ ሳይባል ታማኝነትን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ማሳሰባቸው ነበር።



*ራስ አሥራተ ካሣ*

ኮሎኔል (በኋላ ሌፍቴናንት ጄኔራል) ጃገማ ኬሎ ስለ ውጊያው ለበላይ አለቆቻቸው ባቀረቡት ሪፖርት ላይ፣ የአየር ኃይሉ አቋም ከላይ በተገለጸው አኳኋን የመንግሥት ግልበጣውን ወገን የሚቃወም ሆኖ ስለተገኘ፤ የዘውድ ጠባቂው ወገን ይዞት ከተነሳው ኃይል ጋር ሲደመር የኃይል ሚዛኑ አስተማማኝ ባይሆንም፣ የሌሎችን መተባበር ያስገኛል የሚል ተስፋ እንደሰጠ ገልጸዋል። የአየር ኃይሉ በተፃራሪነት መቀጠል ለጄኔራል መርዕድና ለጄኔራል ከበደ ገብሬ መልካም የተስፋ ጮራ ፈንጥቆ የተቃውሞ ዝግጅቱ ቀጠለ። ንቅናቄው ሲጀመር በአዲስ አበባ የነበረው የጦር ሠራዊቱ አባል ቁጥር ከአንድ ሻለቃ የሚበልጥ አልነበረም። ሁለቱ ባለሥልጣኖች ማለትም ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ በየክፍሉ መከናወን ስለሚኖርበት ዝግጅት ሐሳብ ተለዋውጠው እንደተለያዩ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ በሬዲዮ ግንኙነት በማድረግ፣ በናዝሬት የሚገኘው የታንከኛ ጦር፣ የሐረር፣ የጅማ፣ የጐንደር፣ የደብረ ብርሃንና የነገሌ ቦረናም ጦር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ትእዛዝ አስተላለፉ።



*ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ*



ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ

## የአየር ኃይል አቋምና ክንውኖች

በዚህ ወቅት የአየር ኃይሉ አቋምና እንቅስቃሴን ምን እንደሚመስል በአየር ኃይል መገናኛ ክፍል ኃላፊው ሻምበል ጠለለ ቸርነት (በኋላ ሻለቃና) ምክትሉ ሻምበል (በኋላ ኮሎኔል) ሽፈራው ወርቁ በቦታው ስለነበሩ የሰጡኝ ምስክርነት ላይ ተመሥርቼ አቀርባለሁ::[35]

> *ረቡዕ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጠዋት ሥራ እንደገባን፣ ኮሎኔል በኋላ (ሌፍተናንት ጄኔራል) አሰፋ አየነ መኮንኖቹን በይበልጥ ፓይለቶቹን ሰብስበው፣ "ማክሰኞ ሌሊት ለረቡዕ አጥቢያ ከጄኔራል መርዕድ መንገሻ ዘንድ አንድ ሰው በትንሽ ወረቀት የተጻፈች አጭር መልዕክት ይዞልኝ መጣ:: ማስታወሻው የያዘው መልእክትም ክብር ዘበኞች ከነአዛዣቸው በመንግሥት ላይ ዐመፅ ጀምረዋልና ሁኔታውን እያጣራን ስለሆነ፤ አየር ኃይል ሔደህ ሬዲዮ ከፍተህ የሚሰጥህን ትእዛዝ እንድትጠባበቅ:: ጃንሆይም ከአገር ውጭ ብራዚልን በመጎብኘት ላይ ናቸው" ይላል ሲሉ ገለጹ:: በመቀጠልም ከጄኔራል መርዕድ ጋር ተገናኝተው መልእክቱ በእርግጥ ከእርሳቸው መምጣቱን ከዚያም እስከዚህ ሰዓት ድረስ ያለውን ለውጥ ለመጠየቅ ከአዲስ አበባ ጋር የስልክ ግንኙነት ስለተቋረጠ ማወቅ እንዳልቻሉ አስረዱ:: ሆኖም "ክብር ዘበኛም ዐመፀ ጦር ሠራዊት፣ እኛ እጃችንን አጣጥፈን ልንቀመጥ አንችልም:: ድርጅታችን (አየር ኃይል) ተቋቁሞ እዚህ እስኪደርስ ብዙ የአገሪቷ ገንዘብ ወጥቶበታል:: የብዙ ወንድሞቻችን ደምም የፈሰሰበት ስለሆነ ለአገሪቷ ባለዕዳ ነውና፤ የሕዝብ ደም በከንቱ እንዳይፈስ ለማድረግ ተዘጋጅተን በመጠባበቅ ሁኔታውን ማየት አለብን" አሉ::*
>
> የወቅቱ የአየር ኃይል አዛዥ ስዊድናዊው ጄኔራል ሊንድሐል ነበሩ:: ሆኖም፣ ነገሩ የአገር ጉዳይና ፖለቲካ ነክም ስለነበር፣ በመንግሥት ግልበጣው ሙከራ ወቅት አየር ኃይሉ ከጦር ሠራዊቱ ጋር ተካፋይ የሆነበትን ሥራ ያስተባበሩትና የመሩት፣ በጊዜው ምክትል አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል አሰፋ አየነ ነበሩ:: ስዊድናዊው ጄኔራል ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ባይሆንም፣ በአዛዥነታቸው ለመርዳት ሞክረዋል፤ ፈቅደዋልም:: በመሆኑም የተሰበሰቡትን መኮንኖች፣ "የኃይለ ሥላሴ ታማኝ የሆናችሁ ተነሡና በእግራችንም ቢሆን ወደ አዲስ አበባ ተጉዘን፣ የንጉሡን መንግሥት በመደገፍ ጦርነት እንዳይነሣ ሰላማዊ ሰልፍ እናድርግ" የሚል ሐሳብ አቅርበው ነበር:: ያቀረቡት ሐሳብ አየር ኃይሉ ከተሰለፈበት የጦር መስክ ውጭ ከመሆኑም ሌላ ከአዲስ አበባ ርቀት አኳያ ሲታይ ውጤታማ ሊሆን አይችልም የሚል ሐሳብ መጣ:: በተለይ በወጣት መኮንኖችና በበታች ሹማምንት ዘንድ ለውጡን የመደገፍ አዝማሚያ

---

[35] *ይህንን መረጃ የሰጡኝ፣ የሻምበል ጠለለ ቸርነት (በኋላ ሻለቃ) በአየር ኃይል የመገናኛ ክፍል ኃላፊ እና የሻምበል ሽፈራው ወርቁ (በኋላ ኮሎኔል) የአየር ኃይል የመገናኛ ክፍል ም/ኃላፊ የነበሩት መኮንኖች ናቸው:: በተለይ ሻለቃ ጠለለ ቸርነት ትውስታውን በጽሁፍ ሰጥቶኛል:: ሁለቱም አሁን አሜሪካ በሎስ አንጀለስ ከተማ ይኖራሉ:: አሜሪካ ስሔድ አልፎ አልፎ እንገናኛለን::*

ታየ። በዚህ ጊዜ በስብሰባው ተሳታፊ የነበረው ኮሎኔል ብርሃነ ክርስቶስ አንዳርጌ "እኔ የማውቀው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ነው። ሌላ አላውቅም።" ብሎ የስብሰባውን አዳራሽ በር በኃይል ከፍቶ ወጣ። ተሰብስበው ከነበሩት መኮንኖችም ጥቂቶቹ ተከትለውት ወጡ። በዚህ ምክንያት ስብሰባው ፈረሰና ንጉሡ ነገሥቱን የሚደግፉት ከኮሎኔል አሰፋ አየነ ጋር ወግነው ዝግጅቱ በየክፍሉ ቀጠለ። በተለይ የሬዲዮ ግንኙነት ብቸኛው መገናኛ ስለነበር፣ አዲስ አበባ ከሚገኘው የጦር ሠራዊትና የመከላከያ ሬዲዮ ጣቢያ ጋር ግንኙነት እንዲመሠረት እኔ ራሴ (ሻለቃ ጠለለ ቸርነት) ታዘዝኩ። ከዚህ በፊት የጦር ሠራዊትና የአየር ኃይሉ በሬዲዮ የመገናኘት ልምድ አልነበረውም። በዚያን ዕለት ግን፣ መገናኘቱ ወሳኝ ስለነበረ እንደምንም ግንኙነት ተመሠረተ።

ቀጥሎም ኮሎኔል አሰፋና ጄኔራል መርዕድ በሬዲዮ እንዲገናኙ ተደርጐ ኮሎኔል አሰፋ አየነ ለንጉሡ ፍጹም ታማኝነታቸውን ለጄኔራል መርዕድ ገለጹ። በመቀጠልም አየር ኃይል ከጦር ሠራዊት ጎን እንደሚሰለፍና የአየር ኃይል አውሮፕላኖችን በመጠቀም ጦር ሠራዊቱን ከያለበት ለማጓጓዝ እንደሚቻል፣ በሬዲዮ ጣቢያው ግንኙነት ማድረግም ሆነ ፕሮፓጋንዳ ማሠራጨት የሚቻል መሆኑን አክለው ለሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ አረጋገጡ።

እንግዲህ በዚህ መልኩ ነው የአየር ኃይሉ ተሳታፊነት በዘውድ ጠባቂው ወገን የተረጋገጠው። ይህም የዘውድ ጠባቂውን ወገን ዕቅም ያጐላ ሆኗል።[36]

የዘውድ ጠባቂው ማዕከል በሆነው በክፍለ ጦሩ በኩል ደግሞ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ፣ በጥሪም ይሁን በተባራሪ ወሬ የሰሙና በሲቪል ሥራ ተመድበው ያገለግሉ የነበሩ የጦር ሠራዊት መኮንኖች ሁሉ፣ የጦር ልብሳቸውን እየለበሱ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር በመምጣት፤ ጄኔራል መርዕድ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ " ጋን በጠጠር ይደገፋል" እንዲሉ፣ ከመደበኛው ጦር ጋር ተደባልቀው ጐራውን አጠናከሩት። ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬም በበኩላቸው የመጣውን ሁሉ በአዳራሽ ውስጥ ሰብስበው ክብር ዘበኛ የጃንሆይን መንግሥት ለመገልበጥ ልዑል አልጋ ወራሽን፣ ሚኒስትሮችንና መኳንንቱን ማሠሩን ገልጸው፤ ጦር ሠራዊት በኩል ደግሞ ሤራውን ለማክሸፍ ፈጣን እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ለተሰብሳቢዎቹ አስረዱ። ቀጥሎ ጄኔራል መርዕድ በየጠቅላይ ግዛቱ የሚገኘው ጦር ሠራዊት ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ የጥሪ መልእክት በሬዲዮ ያስተላለፉ መሆኑን ገለጹ። ከዛም የወኔ መቀስቀሻና የመንፈስ ማበረታቻ ቅስቀሳም ተደረገ።

---

[36] ኮሎኔል አሰፋ ብርቱ አንበሳና ተመራማሪ እንደነበሩና ‹‹የኢትዮጵያን ሕዝብ መንፈሳዊ አቋምና ስነልቦናዊ ባሕርይ ጠንቅቀው ያውቃሉ›› እየተባሉ የሚነገርላቸው ናቸው። በወቅቱ የነበረው የክብር ዘበኛ ሠራዊት አብዛኛው አጥባቂ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን እምነት ተከታይ ስለነበረ፤ በፓትርያርኩ ስም የውግዘት ቃል የያዘ በራሪ ወረቀት ታትሞ ቢበተን ጦሩን ከአንድ ሥነ ልቦናዊ ቀውስ ውስጥ ከቶ ይፈታዋል። ካልሆነም የውጊያ ስሜቱን ያቀዘቅዛል ብለው በማመን፣ የውግዘት ቃል ስለመበተን የመጀመሪያውን ሐሳብ ያመነጩት እሳቸው እንደሆኑ የሚጠቁሙ አሉ።

ይህ በእንዲህ እያለ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ከረፋዱ አራት ሰዓት ሲሆን ነው አንደኛ ክፍለ ጦር ወጥተው ከዘውድ ጠባቂ ክፍል ኃላፊዎች ጋር የተገናኙት:: ጄኔራል መርዕድ ስለደጃዝማች ከበደ ከልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ መጀመሪያ ሰምተው የነበረው በለሊት ወደ ደብረ ብርሃን ሔደዋል የሚል ነበር:: ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ይህን ይበሉ እንጂ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ግን በተመካከሩት መሠረት ወደ ደብረ ብርሃን መሔዱን ትተው በንጋት ያመሩት ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ መሆኑን ቀደም ተገልጿል:: ከላይ እንደገለጽኩት ደጃዝማች ከበደ በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ተገናኝተው አልጋወራሽን እጅ ነስተው የሽምግልና ሥራ ለመጀመር ሐሳብ እንዳላቸው ተናግረው ያቀረቡት ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ፣ ሜጀር ጄኔራል መርዕድን ለማግኘት ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር የተሸኙት ንጋት ላይ ነበር:: ይሑን እንጂ፣ ደጃዝማች ከበደ አንደኛ ክፍለ ጦር የደረሱት እንደቸኮላቸው አልነበረም:: ይህም ምክንያት ሊኖረው ይችላል::

ደጃዝማች ከበደ በቤተ መንግሥት ያደጉ፣ በፖለቲካና በአስተዳደር የበሰሉ ሰው ስለሆኑ፣ ለሊቱን ዞር ካለ ቦታ ሆነው ነገሩ ምን እንደሆነና ምን ማድረግ እንደሚሻል በአዕምሮአቸው ሲያወጡ ሲያወርዱ አድረው፣ ወደ ደብረ ብርሃን ከመሔድ ይልቅ በክብር ዘበኛ በኩል ያለውን ሁኔታ በቅድሚያ አጣርቶ ማወቅ እንደሚያስፈልግ በማመን፣ ከቆዩበት ቆይተው ወገግ ሲል እዚያ እንደደረሱ ሁሉ፤ አሁንም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ቸኩለው ዘው ከማለት ሁኔታውን እየመረመሩና እያጣሩ መሔድን መርጠው ወይም የመፈንቅለ መንግሥቱን ጥንስስ ቀደም ብለው ደርሰውበት ኑሮ፣ ለውጡን ደግፈው ሊሆን ይችላል::

ያም ሆነ ይህ «ወደ ደብረ ብርሃን ሔደዋል» ስለመባሉ ወሬ ደርሷቸው የነበሩት ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ደጃዝማች ከበደ ሳይታሰብ በድንገት መጥተው ሲያገኙዋቸው በመገረም የተነጋገሩትን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደሚከተለው አስቀምጦታል::

> በመደራጀት ላይ እንዳለን ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ወደ አራት ሰዓት ገደማ መጡ:: እንደገቡም ‹ደጃዝማች ከየት መጡ? እኛ ወደ ደብረ ብርሃን ሔደዋል መባልዎን ሰምተን ነበር::› ብዬ ብጠይቃቸው፣ ‹እርግጥ ነው፣ ወደዚያ አምርቼ ነበር:: ነገር ግን ሁኔታውን ሳላጣራ ሔጄ አገር ማሸበር እንዳይሆን ብዬ አጣርቶ መሔድ ይሻላል በማለት በቅድሚያ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ግንኙነት አድርጌ በተለዋወጥኩት ቃል አንድ ያለመግባባት ነገር የተፈጠረ ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: ስለዚህ፣ ተገናኝታችሁ ብትወያዩ አልኩት::› አሉኝ:: "የት ነው የምንገናኘው?" አልኳቸው:: "አሁን ያሉት ክብር ዘበኛ ቢሮ ነው:: እዚያ ነው የምትገናኙት" አሉኝ:: "እርሱ ቢሮ! አልሔድም! እውነት ከሆነ አማካይ ቦታ ወይም ከእርሶ ቤት ቢሆን ይመረጣል አልኳቸው::

ይሉናል::

ደጃዝማች ከበደ ተሰማም ከጄኔራል መርዕድ ጋር ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሞካሪዎች ጋር የጦር ሠራዊቱ ኃላፊዎች እንዲነጋገሩ ለማግባባት ያደረጉትን ጥረት እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> እኛ በመገናኘታችን ምንም የምናተርፈው ነገር ስለሌለ፣ እኔም ሆንኩ ጄኔራል ከበደ አንሔድም» አለኝ፡፡ እኔም «የለም በጉዳዩ አስቡበት፡፡» «እናንተ የክብር ዘበኛ ዐምፆአል ስትሉ፤ እነሱ የጦር ሠራዊት ዐምፆአል ሲሉ፤ ባለመግባባት ምክንያት ነገሩ ከርሮ ደም መፋሰስ እንዳይደርስ ለማድረግና ሰላም ማውረድ ይቻል እንደሆነ በሁለታችሁ መካከል እንደመሸጋገሪያ ድልድይ ለመሆን ለመሞከር ነው፡፡ ስለዚህ ምን አለ ግንኙነት አድርጋችሁ ያልተግባባችሁበት ነገር ታርሞ አዲስ አበባንም ከጥፋት የብዙውንም ሰው ደም ከመፍሰስ እንዲተርፍ ብታደርጉ» አልኩት፡፡ እሱም እርስዎ የሚሉት ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ በድንገት የተከሰተ አይመስለኝም፡፡ እንዲያው በጥንቃቄ ታቅዶና ታልሞ በፕሮግራም የተሠራ ነገር መሆኑን መንፈሴ ስለተገነዘበው የምስማማበት አይደለም፡፡

ይህንን የደጃዝማች ከበደ ንግግር ጄኔራል መርዕድም እንደሚከተለው ያስረግጣሉ፡፡

> እኔ እንድሔድና ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር እንድነጋገር፤ ጄኔራል ከበደ ገብሬም አብሮኝ የንግግሩ ተካፋይ መሆን ይፈቅድ እንደሆነ ምክር አካፍለው ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ይህ ነገር ሊሆን አይችልም፡፡ ጄኔራል መንግሥቱ ወደዚህ መጥቶ ከኔ ጋር ለመነጋገር ይፈቅድ እንደሆነ፣ እዚሁ መጥቶ ያለ ሥጋት ተነጋግሮ ሊሔድ ይችላል፡፡ በበኩሌ ይዤ ላስቀረው አልፈልግም፡፡ እኔ ግን ወደዚያ ለመሔድ አልፈቅድም" በማለት እንደገና ቁርጥ ሐሳቤን ለደጃዝማች አስረዳኋቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አብረው የነበሩ መኮንኖች ባይሆን አንድ ሰው ቢሔድ ስለተባለ፣ "በጄኔራል ኢሣይያስ ላይ እንፍረድበትና ይሒድ፣ በዚያውም፣ በወታደሩ በኩል ያለውን አይቶ እንዲመጣ" ብለን ተስማምተን ላክነው፡፡[37]

ደጃዝማች ከበደ ግራ ቀኙን አቀራርቦ ለማስማማት ምን ዘዴ መጠቀም እንዳለባቸው ለ፬ ሰዓት ያህል ጊዜ ወስደው፣ አስበውበትና በዚያም በዚህም አቅጣጫ ምን ሁኔታ እንዳለ መዝነው ለመሸምገል ከሞከሩ በኋላ፣ ከተቃራኒው ወገን ጄኔራል ኢሣይያስ አብረው በመሔድ እንዲያነጋግሩ ሐሳብ ሲቀርብ፤ ጄኔራል ኢሣይያስም ተገናኝቶ መነጋገሩ ደም መፋሰስን የሚያስቀር ከሆነ እኔ ሔጄ እጠይቃለሁ ብለው ስለተስማሙ ሁለቱ ተያይዘው ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ አመሩ፡፡ ጄኔራል ኢሣይያስ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ደርሰው፣ ከጄኔራል መንግሥቱና ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋር ተገናኝተው ሐሳብ ለሐሳብ ከተለዋወጡ በኋላ፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደ ገብሬን አግኝተው ማነጋገር እንደሚፈልጉ፣

[37] አዲስ ዘመን፣ ታኅሣስ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.

የመንፈስ አባቶችም በሽምግልና ሥራ መግባት እንዳለባቸው ገልጸው ጄኔራል ኢሣይያስን መልሰው ወደ እነጄነራል መርዕድ ላኳቸው።

ጄኔራል ኢሣይያስ ክቡር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ሔደው ጄኔራል መንግሥቱን አነጋግረው ሲመለሱ እነሜጀር ጄኔራል መርዕድ ጄኔራል ኢሣይያስን ሲቀበሉ በነበረው ንግግር ጄኔራል መርዕድ ተገናኝቶ በግንባር መነጋገሩን እንደሚደግፉት በመግለጽ፤ በቅድሚያ አቡነ ባስልዮስን እንዲያገኙ ከዚያም ቀጥለው ወደ ብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ዘንድ ቢሔዱ እንደሚሻልና ለሽምግልናው ዝግጁ መሆናቸውን ለልዑል አልጋ ወራሽ እንዲገልጹ መንገዱን ሁሉ እየጠረጉ አመላከቷቸው። ጄኔራል ኢሣይያስም ይህን ካዳመጡ በኋላ፣ ወዲያው ወደአቡነ ባስልዮስ ሔደው በሽምግልናው ሥራ ምን ማድረግ እንደሚሻል ጠየቋቸው። ፓትሪያርኩም ለሽምግልና ጄኔራል መንግሥቱ ዘንድ አብረው መሔድ እንደሚፈልጉ መልስ ሰጡ። ጄኔራል ኢሣይያስም እርስዎ አሁን አያስፈልጉም። አምስት የሽምግልና ነገር የሚያውቁ ጳጳሳትን ይስጡኝ ብለው ስለጠየቁ፤ ለሽምግልና የሚሔዱ ጳጳሳት ተመረጡ። ከጳጳሳቱ መካከል የበአታ ገዳም መምህር፣ የዝቋላ ገዳም መምህር፣ የደብረ ሊባኖስ ጸባቴና ሌሎች ሁለት ጳጳሳት የሚገኙበትን የሽምጋይ አባቶች ቡድን ይዘው ወደ ክብር ዘበኛ ሔዱ።

በዚህ መኻል፣ ልዑል አልጋ ወራሽ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ገቡ። ደጃዝማች ከበደም ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሒደው እዚያ እንደደረሱ፣ መኳንንቱ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ስለነበር፤ መጀመሪያ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ "እንደምን መጡ?" አሉዋቸው። ደጃዝማችም፣ "እነሜጀር ጄኔራል መርዕድን ልወስድ ነው። ልዑል አልጋ ወራሽም ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ገብተዋል። ደህና ናቸው። ይዘሃቸው ና ብለውኝ ይህንን ነግሬ ልወስዳቸው ነው የመጣሁት" የሚል መልስ ሰጡ። አሥራተ ካሣም፣ "አይሆንም! የጃንሆይን መንግሥት ገልብጠናል እያሉ ዐዋጅ እያወጁ እንደምን ተብሎ ነው እነሜጀር ጄኔራል መርዕድ ወደዚያ የሚሔዱት?" በማለት ተናገሩ። ይሄኔም በሥፍራው የነበሩት ሁሉም ደጃዝማች ከበደን በትዝብትና በመገረም ዓዩዋቸው።

ደጃዝማች ከበደ የመጡበትን ጉዳይ ከሜጀር ጄኔራል መርዕድ ጋር ቢነጋገሩበትም፤ ጄኔራል መርዕድ ከረፋዱ ጀምሮ በየአቅጣጫው በሬዲዮ ጥሪ የተደረገለት የጦር ሠራዊት ከሐረር፣ ከነጌሌ ቦረና፣ ከድሬዳዋ፣ ከደብረ ብርሃንና ከሌሎችም ሥፍራዎች በባቡርና በአየር ኃይል አውሮፕላን መጓጓዝ መጀመሩን ሲያረጋግጡ ነበር የቆዩት። ከዚሁም ጋር የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች፣ የወጡት የለውጥ እንቅስቃሴ በተቻለ መጠን ያለ ምንም ደም መፋሰስ እንዲጠናቀቅ ከፍ ያለ ፍላጐትና ምኞት ያላቸው መሆኑን፣ ከላይ ከታች በሚመላለሱት ሽማግሌዎች የመረጃ ምንጭነት ተረድተዋል። የጦር ሠራዊት በክብር ዘበኞች ላይ አድሮበት ከኖረው ቅናት የመነጨ ቆየት ያለ ቅራኔ መኖሩም፤ እንዲህ ላለው አጋጣሚ አስተዋፅኦ ሊያደርግ እንደሚችል ተገንዝበዋል። ሌላው ቀርቶ፣ ክብር ዘበኛ የሕዝቡን ልብ በሙዚቃ በመብላት ተወዳጅነት

አለው፡፡ እኛን ግን የሚያስታውሰን የለም በሚል ስሜት ጦር ሠራዊቱ ይቀናና ክፋት ያስብ ስለነበር፣ በምንም ጉዳይ መጣጣም አልነበረም፡፡

በጦር ሠራዊትና በክብር ዘበኛ መካከል ቅራኔ የተፈጠረው ንጉሡ ሁለቱን የሠራዊት ክፍል እኩል ባለማየታቸው ነው፡፡ ለክብር ዘበኛ ከደመወዝ ሌላ የስንዴ ድርጎ (ራሽን) ይሰጠው ነበር፡፡ የክብር ዘበኛ ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚለብሰው ረጅም በላሌ ሱሪ ሲሆን፣ የጦር ሠራዊት ደግሞ ቁምጣ ነው፡፡ ክብር ዘበኛ የሚጫማው ሽፍን ጫማ ሲሆን፣ ጦር ሠራዊት ደግሞ የካርቱም ጫማ የሚባል ግማሹ ክፍት የሆነ ነበር፡፡ ጦር ሠራዊት ከደሞዙ በተጨማሪ የሚሰጥ ሌላ ዳረጐት አልነበረውም፡፡ ይህን የመሳሰለው ማበላለጥ በጦር ሠራዊቱ ላይ ቅናት ፈጥሮ ቆይቶ ነበር፡፡ ይህን በክብር ዘበኛና በጦር ሠራዊት መካከል የነበረ ልዩነት እነሜጀር ጄኔራል መርዕድ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ተረድተዋል፡፡

ወደ አየር ኃይል ጉዳይ ስመለስ፣ ሁኔታው በአየር ኃይሉ በኩል እየጠራ በሔደበት ወቅት፣ አልጋ ወራሽ የአባታቸው መንግሥት ፈርሶ እሳቸው የተተኩበት ዐዋጅ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ተነግሮ፣ ክብር ዘበኛ በመንግሥት ላይ ማመፁ ግልጽ ሆኗል፡፡ ኮሎኔል አሰፋ አየነ ፓይለቶችን ሰብስበው ይህንኑ ዜና ካሰሙ በኋላ፣ ‹‹ዐመፁን ለማቆም ከጦር ሠራዊቱ ጋር መተባበርና በኤታማዦር ሹሙ መሪነት ተሳታፊ መሆን አለብን፡፡ ይህንንም ስናደርግ ለጊዜው ያመፀውን የክብር ዘበኛ ጦርን እልቂት ሳናበዛ ጦርነቱን ለማቆም መሆን አለበት፡፡ በጦርነቱ የሚያልቁት ወንድሞቻችን መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም›› ብለው ቀሰቀሱ፡፡ ለዚህ አባባላቸውም አንድ የሰጡት ምሳሌ "ከተዋጊ ፓይለቶቹ አንዱ መቶ አለቃ ደብሩ ድምበሩ ከላይ ተኩሶ መሬት ላይ ሊገድል የሚችለው ታላቅ ወንድሙን የክብር ዘበኛ ሻለቃ ክፍሌ ድምበሩን ነው" ብለው የጦሩን መንፈስ ሰበሰቡ፡፡

በዚህ ጊዜ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ መንገሻ በተደጋጋሚ በሬዲዮ ጥሪ ኮሎኔል አሰፋን፣ "አዲስ አበባ ናና ስለማንኛውም ተመካክረን የዐመፁን ማክሸፊያ ሥልት ካወጣን በኋላ ትመለሳለህ" ይሏቸው ነበር፡፡ ኮሎኔሉም "እሺ እመጣለሁ፣ መጀመሪያ እዚህ ያለውን ሥራ ላጠናቅቅ" የሚል መልስ ይሰጡ ነበር፡፡ ሜጀር ጄኔራል መርዕድም እየደጋገሙ አዲስ አበባ ና እያሉ መወትወታቸውን አላቋረጡም፡፡ ስለዚህ «የአዲስ አበባ መግቢያ በር በክብር ዘበኞች ስለተዘጋ ማለፍ አንችልምና እዚሁ ቆይቼ የሚሰጠኝን ትእዛዝ ልፈጽም» በማለት ኮሎኔል አሰፋ እግራቸውን ይጎትቱ ነበር፡፡ የአየር ኃይሉ መገናኛ ኃላፊ ሻለቃ ጠለለ የጄኔራል መርዕድ ተደጋጋሚ ጥያቄ፣ ኮሎኔል አሰፋን የመጠርጠር ነገር እንዳለው በአከባቢው ለነበርነው መኮንኖች ግልጥ ነበር ሲል ሁኔታውን ያስረዳል፡፡

ደጀዝማች አሉላ በቀለና ልጅ ዳንኤል አበበ (በኋላ ደጃዝማች) በአየር ኃይሉ ግቢ ሆነው፣ የኮሎኔል አሰፋን አቋም ይከታተሉ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የኮሎኔል አሰፋን ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር ተባብሮ የመንግሥት ለውጡን ማክሸፍ የሚቃወሙ

ጥቂት ወጣት መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ነበሩ። ይህንንም፣ ኮሎኔል አሰፋ ስላወቁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርገው ነበር። በመጨረሻ ከጄኔራል መርዕድ ወደ አዲስ አበባ ና የሚለው ጥያቄ ስለበዛባቸውና፤ እምቢ ብዬ እዚህ መቅረቱ ያስጠረጥረኛል ብለው በመሥጋት በመኪና ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ወሰኑ። የሳቸውን ማርቸዲስ አንድ ሌላ መኮንንና መቶ አለቃ ተስፋዬ ለገሠ (እርሳቸውን) ከሹፌራቸው ጋር አስቀምጠው ፊት ፊት እንዲሔዱ አድርገው እሳቸው በርቀት በሻለቃ ጋዲሳ ጉማ መኪና ሻለቃ ጋዲሳ እየነዱ መንገድ ጀመሩ።[38]

ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ዘይት በሚወስደው መንገድ ላይ ያገኙትን የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ሁሉ እያስቆሙ ስለ መንገዱ በተለይ ስለ አዲስ አበባ መግቢያ ሲጠይቁ፤ የታጠቁ የክብር ዘበኛ ወታደሮች ሁሉንም የመግቢያ በር ዘግተው ይዘውታል ይሏቸው ነበር። በመጨረሻ ቃሊቲን እንዳለፉም አንድ መኪና አስቁመው ሲጠየቁ የአድአ ወረዳ ገዥ የነበሩትን፣ ልጅ ኃይለ ማርያም መንገሻን አገኟቸውና ስሁኔታው ጠየቋቸው። እሳቸውም፣ «እንዲያው እጃችሁን ለመስጠት ወይም ከእነሱ ጋር ለመቀላቀል ካልሆነ በስተቀር፤ ከንፋስ ስልክ ማለፍ አትችሉም» አሏቸው። በዚህ ጊዜ ኮሎኔል አሰፋ፣ «እንዲህ እየተባልኩ ሔጄ እጄን አልሰጥም። ከአገሬ ገገርዬም አልለይም። አዙር እንመለስ ብለው፤ ልጅ ኃይለ ማርያምንም በመያዝ መመለስ እንደጀመሩ በመንገድ ላይ ሬድዮ መገናኛ የያዙ ክብር ዘበኛ ወታደሮችን ያገኙና በመገናኛቸው ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር እንዲያገናኟቸው ጠይቀው አገናኟቸው። ኮሎኔል አሰፋ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ሲነጋገሩ የሰሟቸው ኃይለ ማርያም *ምትአምባ ደርሶ መልስ* በተባለ መጽሐፋቸው እንዳስቀመጡት[39] ጄኔራል መንግሥቱ "አሰፋ ከዳኸኝ? ከዳኸኝ?" ሲሉ ኮሎኔሉ ደግሞ «ቆይ መንጌ» ሲሉ ይሰማ ነበር። ኮሎኔል አሰፋ ከእነሱ መለየታቸውን ጄኔራል መንግሥቱ በማወቃቸው ስልኩን በጆሯቸው ላይ እንደዘጉባቸውም በመጽሐፉ ተጠቅሷል።

ከዚህ በኋላ ኮሎኔል አሰፋ የአዲስ አበባን መግቢያ ችግር ለጄኔራል መርዕድ ነገሯቸው። የዚህን ጊዜ «እንግዲያውስ በአውሮፕላን ና» አሏቸው። ኮሎኔል አሰፋም «እሺ» ብለው አውሮፕላን ውስጥ እንደገቡ ጄኔራል ሊንድ ሐልን ጠርተው «ካልተመለስኩ ቤተሰቤን አደራ» እንዳሏቸው፣ የሻምበል ጠለለ ያስታውሳል። ኮሎኔል አሰፋ ከጄኔራል መርዕድ ጋር በተነጋገሩት መሠረት በአውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ አውሮፕላን ሚዳው ጫፍ ሆነው ለመነሣት ሲዘጋጁ፤ ጄኔራል መርዕድ በሬዲዮ «የአዲስ አበባው አውሮፕላን ማረፊያ ባሁኑ ጊዜ በክብር ዘበኛ ጦር ስለተያዘ መምጣትህ ቀርቶ እዚያው ሆነህ የምንሰጥህን ትእዛዝና መመሪያ ተከተል» በማለት ስላዘዟቸው፤ እዚያው አየር ኃይል ግቢ ሆነው ቀጣይ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ዋሉ።

---

[38] መረጃውን የሰጠኝ ሻምበል ጠለለም ስለመገናኛ እንነጋገራለን ብለውት እዚያው ኮሎኔል አሰፋ የነበሩበት መኪና ውስጥ ነበር።

[39] ኃይለማርያም መንገሻ ምትአምባ ደርሶ መልስ ገጽ ፻፷፭፤

ማምሻውን ደግሞ፣ በኮሎኔል አሰፋ ብቸኛ አነሣሽነት የአየር ኃይሉን የመገናኛ ሬዲዮ በመጠቀም የአዲስ አበባ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሬዲዮ ጣቢያ በማስመሰል፣ የዐመፅ አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ሲያሰራጩ አመሹ:: ስለዚህ ረቡዕ ዕለት የግራ ቀኙ ወገኖች የታያቸውን ሁሉ ሲያከናውኑ ውለውና አምሽተው፣ በነጋታው መከናወን ስላለበት ሥራ እያውጠነጠኑ ነጋ::

# ምዕራፍ ፮

# የመፈንቅለ መንግሥቱ እንቅስቃሴ

## ኮተቤ ላይ የታገደው ጦር (ሐሙስ ታኅሣሥ ፮ ቀን)

የረቡዕ ለሊት እንዳይነጋ የለምና ለሁለቱም ወገን ነጋ። ከዚያ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ከደብረ ብርሃን እንዲመጣ ያዘዙት ጦር ታኅሣሥ ፮ ቀን ጠዋት ከ፲፪ ሰዓት ቀደም ብሎ ኰተቤ በር መድረሱ ተሰማ። በዚያ አቅጣጫ፣ ጦር ወደ አዲስ አበባ እንደሚመጣ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ቀደም ብለው የያዙት ግምት ስለነበር፤ በሩን ይዞ ሁኔታውን የሚከታተል አንድ የሻምበል ጦር ተመድቦ ነበር። ይኸው ምድብ ሻምበል ጦር የደብረ ብርሃኑ ጦር ማልዶ መምጣቱን ለክብር ዘበኛ ፪ኛ ብርጌድ ጥብቅ አዛዥ ለሻለቃ ተፈራ በላይ አደረሰ። ሻለቃ ተፈራም ለቃኚው ሻምበል የበኩላቸውን መመሪያ ከሰጡ በኋላ ስለመጣው ጦር ጄኔራል መንግሥቱን አሳውቀው የውሳኔ ትእዛዝ ለመቀበል ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ይመጣሉ። የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ባለሁበት፤ እዚያ ደርሰው ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር የሚከተለውን ተነጋገሩ።

> ከደብረ ብርሃን ጦር ይንቀሳቀሳል የሚል ጥርጣሬ ቀድሞውኑ ስለነበረን፤ ረቡዕ ዕለት አንድ ቃኚ ሻምበል ልኬ፣ ይኸው አጣሪ ሻምበል ሐሙስ ጧት በ፲፪ ሰዓት ከደብረ ብርሃን ጦር መምጣቱን መልእክት አስተላለፈልኝ። እኔም ባለበት ቦታ እንዲያቆመው ትእዛዝ ሰጠሁ። ግንባር ቀደም ሆኖ የመጣው አንድ ሻምበል ጦር ታግዶ ቆሟል። በቀላሉ ትጥቅ ማስፈታት እንችላለን። ዋናውንም ጦር እንዲሁ።[1]

ሲሉ ለጄኔራል መንግሥቱ ሪፖርት አቀረቡ።

ጄኔራል መንግሥቱም "በጭራሽ! በጭራሽ! ተፈራ አይደረግም" ብለው ተቆጡ። ቀጠል አድርገው፣ "የአዛዡን ስም ታውቀዋለህ?" ብለው ጠየቋቸው። "አላውቀውም" አሉ። "እንግዲያውስ ይህን ማስታወሻ ወስደህ ስጥ" ብለው የሚከተለውን መልእክት የያዘ ማስታወሻ ሰጡዋቸው። "ከደብረ ብርሃን የመጣኸው፣ እዚያ ያሉትን ወታደሮች የምታዝ መኮንን፣ ፈቃድህ ቢሆን የእንቅስቃሴውን ሁኔታ ልግለጽልህ። ይኸውም በእኛ እና በእናንተ መካከል ምንም ቅሬታ እንደማይኖር አረጋግጥልሃለሁ" የሚል ነበር። ሻለቃ ተፈራም "ይህን የእርስዎን መልእክት ተቀብለው የማይፈፅሙና ወደ ተጠራንበት እንሔዳለን ቢሉ ምን ላድርግ?" በማለት ሲጠይቋቸው፤ "አንመጣም ካሉህ ወደታዘዙበት እንሔዳለን ልቀቃቸው" አሏቸው። ይህንን ስሰማ፤ ወታደርም ባልሆን ነገረ ሥራዬ የወታደር ስለሆነ እንዲህ ያለውን

---

[1] ሻለቃ ተፈራ የሰጡትን ቃል ለዝርዝር መረጃው ብወሰድም በአካልም በስፍራው ተገኝቼ ያዳመጥኩት ነበር። ይህንን ለመመልከት የቻልኩት እኔ ከብዙ የክብር ዘበኛና የሕዝብ ጸጥታ ጥበቃ መምሪያ መኮንኖች ጋር በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ አድሬ ስለነበረ ነው።

አጋጣሚ በቸልታ ማሳለፍ ቅር አሰኘኝ። ውሳኔውን አልወደድኩትም፤ እንደ እኔ ውሳኔውን ያልወደዱ ሌሎች መኮንኖችም ነበሩ።

ጄኔራሉ ትዕዛዙን እንደሰጡ እኔም ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ ካሉበት ክፍል ተጠርቼ ስገባ፤ "ከሻለቃ መላኩ በቀለና ከሻለቃ ተፈራ በላይ ጋር ወደ ኮተቤ ሔዳችሁ ከደብረ ብርሃን የመጣውን ጦር አግባብታችሁ ወደመጣበት እንዲመለስ አድርጉ" የሚል ትዕዛዝ ተሰጠኝ። ከፎቁ ወርደን ከመኪና ልንገባ ስንል፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ ከፎቁ በመስኮት ብቅ ብለው ሁለቱ መኮንኖች ወደ ታዘዙበት እንዲሔዱ ነገሩዋቸው። እኔን ግን እንድመለስ አዘዙኝ። ወደፎቁ ተመልሼ እነሱ ወዳሉበት ስገባም "የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የመሐንዲስና የሕንፃ ኮሌጅ፣ እንዲሁም የማሠልጠኛ ተቋማት ተማሪዎች በአጠቃላይም ምሑራኑ አወንታዊ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ይጠበቅ ነበር። እስካሁን እንቅስቃሴ የለም። ተቆጥበው የሚታዩት ምናልባት ስለለውጡ መንፈስ በቂ ማብራሪያ ካለመስጠቱ ወይም ለውጡን በመጠራጠር ሊሆን ይችላል። ከዚህ ግምት በመነሣት ረቡዕ ታኅሣሥ ፯ ቀን ማታ ወደ ፫ ሰዓት ገደማ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የማታ ተማሪ የሆነው የሻለቃ አዲስ ዓለም ጽጌ የሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ ባልደረባ ከሆኑት ከአቶ መስፍን ወልደ ሚካኤልና አቶ ኤፍሬም ፀሐይ ጋር ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ሔደው ስለለውጡ እንቅስቃሴ በመግለጽና በመንቀሳቀስ ለለውጡ ድጋፍ እንዲሰጡ ለማግባባት ተልከው ነበር። እነሱም መልእክቱን አድርሰው ተማሪዎቹም፣ በአፋጣኝ ድጋፍ እንደሚያደርጉ ቃል ሰጥተዋቸው ተመልሰው ይኸንኑ ሪፖርት ማድረጋቸውን ገለጹልኝና

> መሐንዲስ እና ሕንፃ ኮሌጅ እስካሁን የሔደ ሰው የለም። ስለዚህ፣ አንተ ወደሾላ ከምትሔድ ወደ መሐንዲስና ሕንፃ ኮሌጅ ሒደህ ስለለውጡ ቅስቀሳ አድርግ"። ልዑል አልጋ ወራሽ ከእኛ ጋር መሆናቸውን ገልጸህ፣ ጦር ሠራዊቱ ባላወቀው ነገር በተቃዋሚነት እንዲነሣ ስለተደረገ፤ ደም መፋሰስ እንዳይደርስ ተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሔደው፣ ጦር ሠራዊቱን የሚመሩትን ጄኔራሎች አቋም እንዲያስለውጡ አነጋግራቸው

ተብዬ ከመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ (በኋላ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ፪ኛ ተከሣሽ ከነበረው) ጋር ወደ መሐንዲስና ሕንፃ ኮሌጅ እንድንሔድ ታዘዝን።

በታዘዙት መሠረት ሁለቱ መኮንኖች[2] የደብረ ብርሃን ጦር ወደታገደበት ወደ ኮተቤ ሔደው፤ ከጄኔራል መንግሥቱ የተላከውን ማስታወሻ ለኃላፊው የሻምበል ደበሼ ለተባለ መኮንን ሰጡት። መኮንኑም መልእክቱን ተመልክቶ፣ "እናንተም እዚህ የቆማችሁት ታዛችሁ ነው። እኛም የተጠራነው ከአዛዣችን ክፍለ ጦር ነው። ስለዚህ፣ ከአለቆቻችን ትዕዛዝ እስከምናገኝ ወደመጣንበት እንመለሳለን" ስላሉ ለቀቋቸው። ከዚያም አንድ

[2] በኋላ ሻለቃ ተፈራ በላይና ሻለቃ መላኩ በቀለ እንደነገሩኝ፤ (የሻለቃ ተፈራ በላይ አሁን በሕመም ከቤት ውለዋል።)

ኪሎ ሜትር ያህል አፈግፍገው ብትንትን በማለት ወደ መጡበት ሳይሆን፣ ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር አመሩ።

እኔና የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ከጧቱ አንድ ሰዓት ገደማ መሐንዲስ ኮሌጅ እንደደረስን፤ ከኮሌጁ ግቢ ያገኘናቸው ተማሪዎች ጓደኞቻቸውን ከመኝታ ቤታቸው በመጥራት በአንድ ቦታ እንዲሰበሰቡልንና ስለተፈጠረው እንቅስቃሴ መግለጫ እንድንሰጣቸው ብለን ጠየቅናቸው። ተማሪዎቹም ትክክለኛውን ነገር ለማወቅ ጓጉተው ስለነበር፤ "አሁን የቁርስ ሰዓት ስለደረሰ ተማሪው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በሙሉ ይመጣል። እዚያው ላይ ልትገልጹ ትችላላችሁ" ብለው መለሱልንና ወደየመኝታ ቤቶቻቸው ሔደው ተማሪዎችን ቀስቅሰው አመጧቸው።

እኔ ንግግሬን ስጀምር ያነሣሁት የአዲሱ መንግሥት መጠሪያ ስም "ሕዝባዊ መንግሥት" መባሉንና ፕሬዝዳንቱ "ልዑል አልጋወራሽ" እንደሆኑ ነው። በመሬት ድልድል ረገድ "የአገራችን የመሬት ይዞታ ገደብ ኖሮት፣ የአንድ ሰው የከተማ ቦታ ይዞታ ከ፫ ሺህ ካሬ ሜትር እንዳይበልጥ ገደብ ይደረጋል" አልኩ። በዚያን ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥቱና ቤተሰቦቻቸው፣ መኳንንትና ወይዛዝርት በገጠር ባለ ብዙ ሺህ ጋሻ መሬት ባለቤትና በከተማ የባለ ብዙ መቶ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ባለርሥቶች ስለነበሩ፤ በከተማና በገጠር የሚታየው የመሬት ድልድል ልዩነት ተወግዶ፤ ለገበሬው በቂ መሬት ከማልሚያ ጋር እንደሚሰጥ በማብራራት ተናገርኩ። ስለዚህ ይኸን በመቃወም የተሰለፉት የጦር ሠራዊት ጄኔራሎች ደም እንዲፋሰስ ከማድረጋቸው በፊት፣ ጉዳዩ በሰላም እንዲያልቅ ተማሪዎች በሰላማዊ ሰልፍ መጠየቅ እንደሚኖርባቸው ቀሰቀስኩ። ከዚህ በኋላ ብዙ ጥያቄዎችና መልሶች ተካሔዱ።

በመጨረሻም እኔና የመቶ አለቃ ድጋፍ ተድላ ወደ ሕንፃ ኮሌጅ ለመሔድ ስንጣደፍ፤ እነሱ ቀድመው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች መልእክት ደርሷቸው ነው መሰል አስፈላጊውን ለማድረግ ተሰልፈው ሜክሲኮ አደባባይ አጠገብ በሚገኘው በመሐንዲስ ኮሌጅና በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ሲያልፉ ዓየን። በዚህ መኸል የምሕንድስና ኮሌጅ ተማሪዎች ከመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ጋር ተገናኝተው ትክክለኛውን አቋም ካወቁ በኋላ፣ የደም መፋሰስ እንዳይደርስ በበኩላቸው አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ ሁኔታውን አጣርተው የሚመጡ አራት ተማሪዎች መርጠው ሰጡን። ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች በእኔ መኪና ይዘን ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ አድርሰን ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር አገናኘናቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተመርጠው የተላኩ አራት ሌሎች ተማሪዎችም ቀደም ብለው ደርሰው ነበርና እኛ ካመጣናቸው ተማሪዎች ጋር ተደባልቀው ጄኔራል መንግሥቱ ስለሰውጡ ገልጸውላቸው፤ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ውይይቱን ቀጠሉ።

የውይይቱ ፍሬ ሐሳብ ደም መፋሰሱን ማስቀረት ስለሚቻልበት ሁኔታ ነበር። ከየኮሌጁ የመጡት ተማሪዎችም የተለያዩ ጥያቄዎች አቀረቡ። ዋናዎቹም "የጦር

ሠራዊት በበኩሉ ክብር ዘበኛም በበኩሉ ለግጭት እየተዘጋጃችሁ ነው። የየበኩላችሁ ስሜት የየራሳችሁ ነው። ይሁን እንጂ፣ ተኩስ በከፈታችሁ ጊዜ በመኻሉ በሰላማዊ ሕዝብ ላይ አደጋ ስለሚደርስ፣ እርስዎ ምን ማድረግ ነው የሚፈልጉት?" እና "በሰላማዊ ሕዝብ ላይ አደጋ እንዲደርስ ይፈልጋሉ?" የሚሉ ነበሩ። ጄኔራል መንግሥቱም "አንድም ሰው ቢሞት ደስ አይለኝም። የእኔ ዐላማ ሰው እንዲሞት አይደለም" አሏቸው። ጄኔራል መንግሥቱ ይህን መልስ ሲሰጧቸው፤ ተማሪዎቹ "እርግጠኛ ነዎት?" ሲሉ መልሰው ጠየቋቸው። "አዎ!" አሏቸው። ተማሪዎቹ ይህን ከጄኔራል መንግሥቱ እንዳረጋገጡ፣ "በጦር ሠራዊት በኩል የምናነጋግረው ማንን ነው?" ብለው ጠየቁ። "ጄኔራል መርዕድንና ጄኔራል ከበደን ነው" ብለው አሏቸው። "እነዚህ ጄኔራሎች የት ነው የሚገኙት?" ሲሉ ተማሪዎቹ ጠየቁ። "አንደኛ ክፍለ ጦር" ሲሉ መለሱላቸው።

በመጨረሻ ጄኔራሉ ለውጡ በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ እፈልጋለሁ። ወደዳችሁም ጠላችሁም የወደፊቷን ኢትዮጵያ አስተዳደር የምትሸከሙ እናንተ ናችሁ። ይህም የምታምኑበትና የምትቆሙለት ዐላማ ስለሆነ ሰላማዊ ሰልፍ አድርጉ። ሕዝቡን ለማስረዳትም ሞክሩ። እነሆ ዐላማው ተገልጾላችኋል። እኔን ያነሣሣኝ በአስተዳደር የሚፈጸመው በደል፣ በተለይም በፍርድ ላይ ያለው ችግር ነው። አንድ ባለ ጉዳይ በይግባኝ ከጠቅላይ ግዛት መጥቶ በአገሪቱ ያሉትን አራት እና አምስት የፍትሕ መስጫ እርከኖች አዳርሶ የመጨረሻውን ፍትሕ ለማግኘት ብዙ ዓመታት በአዲስ አበባ ተጉላልቶና ቤተሰቡም ተበትኖ እንደወጣ በመቅረቱ፤ ይህን ግፍና በደል ከሕዝብ ትከሻ ለማውረድ ነው። ከዚህ በኋላ እናንተ የመሰላችሁን አድርጉ። ብለው ምርጫውን ለተማሪዎቹ ተዉ።

ተማሪዎቹ ተመልሰው የሰሙትን መግለጫ ለጓደኞቻቸው ስለገለጹላቸው የሦስቱ ኮሌጆች ተማሪዎች ተሰባስበው በከፍተኛ ስሜት በመጨፈርና፣ መዝሙሮችን በመዘመር ለለውጡ ድጋፋቸውን በመስጠት ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር አምርተው፤ የለውጡ ጅምር የአንድ ሰው ደም ሳይፈስ በሰላማዊ መንገድ እንዲያልቅ በማለት ለጦር ሠራዊቱ ከፍተኛ መኮንኖች በማሳሰብ አቋማቸውን ለማስለወጥ ከክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ወጡ።

ተማሪዎቹ ለሰልፍ ከመውጣታቸው በፊት ግን የሚበትኑትን ወረቀት ለማርቀቅና ለማባዛት ማባዣ ማሽን ብልሽት አጋጥሟቸው ጥቂት ዘገዩ። እንደ አጋጣሚ እኔ (የዚህ ታሪክ ጸሐፊ) በቦታው ስለደረስኩ፤ ላስተካክለው እችል ይሆናል ብዬ ወደ ማባዣ ክፍሉ ልንገባ ስንል፣ የዩንቨርስቲ ኮሌጁ የንብረት ክፍል ኃላፊ የነበሩት አቶ አሰፋ ተክለ ሥላሴ ለተማሪዎቹ በማሰብ "ተዉ እናንተ ልጆች አርፋችሁ ብታዩ ይሻላችኋል። በኋላ እኔ የለሁበትም" የሚል ምክር በመስጠት በማንገራገር አወኩን። እኛ ግን ተጋፍተን ማባዣ ክፍሉ ገባን። የማባዣ መሣሪያው ብልሽት ቀላል ስለነበር፤ አስተካክዬላቸው በተዘጋጀው እስቴንስል የሚፈለገውን ያህል በወረቀት

ተባዝቶ እንዳበቃ መፈክራቸውን ይዘው እየዘመሩ ከግቢ ወጡ። መዝሙሩም ከዚህ ቀጥሎ የሠፈረው ነበር።

*ታሪክ ያለህ ያገሬ ሰው*
*ታሪክ ያለህ ያገሬ ሰው*
*ተነሣ ! ተነሣ !*
*ሰውነትህን አትርሳ።*
*ባርነትህን ደምስሰው*
*ነጻነትህን ዛሬ አድሰው*
*ሰውነትህን አትርሳ።*
*ክብርህ መብትህ ሊጠበቅ ነው*
*ደስታ ሕይወትን ልታገኝ ነው*
*ተነሣ ! ተነሣ !*
*ሰውነትህን አትርሳ።*

የሚል ሲሆን፤ መዝሙሩን እየዘመሩ መውጣት ሲጀምሩ፤ እኔም ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ተመልሼ ተማሪዎቹ በሰልፍ መውጣታቸውን ለመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ገለጽኩ። የሦስቱ ኮሌጅ ተማሪዎች ለሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ፣ ከተለማመዱት መዝሙር በተጨማሪ ለሕዝብ የተበተነው በራሪ ወረቀት ይዘትም ቀስቃሽ ነበር።

## በኢትዮጵያ ያላችሁ አባቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ሆይ

አገራችን ኢትዮጵያ በታሪክ፣ በባህል፣ በቦታ ስፋትና በሀብት ከማንም አገር የማታንስ መሆኗን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። ነገር ግን ዕድልና መብት አጥተን በፍርሃት ተውጠን ውስጣችን እንደ ጧፍ እየነደደና እየተቃጠለ ዝም ብለን ሥቃያችንን ተሸክመን የሌላውን አገር ስናደንቅ እንገኛለን። ስለ ውድ አገራችን ብልፅግና፣ ስለ ውድ አገራችን መሻሻል፣ ስለ ውድ አገራችን በሥልጣኔ ጉዳና መጓዝ ያለን ምኞትና መልካም ሐሳብ ሁሉ፣ በልባችን በየዕለቱ በማውጣትና በማውረድ ይህንኑ ምኞታችንን መልካም ሐሳባችንን ተመርኩዘን "ይህ ይሁን" ባለማለታችን እስከ አሁን ድረስ ከዚህ ደረስን። ከዚህም በላይ፣ መማር እንዳለብን ስንገነዘብ የምንማረውም አገራችን ደሀው ሰው በለፋው፤ ጥሮ ግሮ እየተቆራመደ ባፈራው ንጹሕ ሀብት መሆኑን እየተረዳን ነው። ነገር ግን፤ በፍርሃት ታስረን ችግሩ የሚቃለልበት አንድም ዓይነት ዘዴ ልንፈጥርለት አልቻልንም ነበር። ዛሬ ግን፣ በዚሁ መሠረት አሁን በተደረገው የአስተዳደር መለወጥ መንግሥቱ ለሕዝብ በሕዝብ የሚተዳደር ሲሆን ደስ ያሰኛል።

አገራችንን እጅግ እናፈቅራታለን፣ የምናፈቅራትም ከጥፋቷ ጋር ሲሆን፤ እስከ አሁን የነበረችበትን የችግርና የሥቃይ ሁኔታ በፍርሃት ምክንያት ሳናቃልልላት ቆየን። ነገር ግን፣ ማንኛውም ነገር በጊዜው

ስለሚፈፀም እኛም ጊዜውን ስንጠብቅ ለአገራችን መሻሻያ፣ ለሕዝባም ብልፅግና ይሆን ዘንድ ይሄው ዛሬ በማንኛውም ነገር አብረን ተባብረን ለጋራ ጥቅማችን ልንሠራ ቆርጠናል።

ከዚህ በላይ ከፍ ብለን በጠቀስነው መሠረት ለሚደረገው መሻሻል ዘወትር በሐሳብም ሆነ በሥራ ዝግጁዎች ነን። ኢትዮጵያ ነፃነቷንና መብቷን ከሦስት ሺህ ዘመናት በላይ ይዛ ሳትደፈር እስከ ዛሬ ደርሳለች። ነገር ግን፣ ይኸን ያህል ዘመን በነፃነት የቆየችው አገር ዛሬ አዲስ ዘመን የወለዳቸው አገሮችና ሕዝቦች ከኋላ ተነሥተው ወደ ኋላ ጥለዋት ስለሔዱ፣ ኢትዮጵያ ፊት የነበራት ክብርና የሥልጣኔ ቅርስ እየከሰመ ሔዷል። እኛ ይህን ለማወቅ የደረስነው በታሪክ ጥናትና የአሁኑን ዓለም ሁኔታ በትምህርት ተከታትለን ከተገነዘብነው በኋላ ነው።

ለኢትዮጵያ እርምጃና ግሥጋሴ ለሕዝባም ብልፅግና መሰናክል የሆነው በጥንቱ መንግሥት ውስጥ የነበረው የአስተዳደር ጉድለት መሆኑን እንገነዘባለን። በመሬት አደላደል (አከፋፈል) በኩል ነገሩን ስንመለከተው፣ ሀብታሙ ሁሉ በጠቅላላው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ጋሻ መሬት ይዞ፣ ሀገሬው የኢትዮጵያ ዜጋ በገባርነት የእኩል እያረሰ፤ ገሚሱ እርቦ እየሰፈረ፤ ገሚሱ ደግሞ ለሀብታሙም ለራሱም እያረሰ፣ በዚህ ላይ ለሀብታሙ ሀብት ማዳበሪያ ይሆን ዘንድ የሙያ እየዋለ በችግር ሲቆራመድ ይታያል። ከዚህ ከመሬት አደላደል ጋር ተያይዞ በመሬት ነገር ድሀው ለሙግት ወደ ከተማው እየመጣ፣ በፍርድ ጉድለት ምክንያት ስንቁን ጨርሶ መሬቱን ተነጥቆ በርሃብና በችግር ሲጉላላ ሁላችን ተመልክተናል። ይህ ከዚህ በላይ የገለጽነው በአጭሩ የባላገሩን ሰው ሁኔታ ሲገልጽ ፊታችንን ወደ ከተማ ሰው ያቀናን እንደሆን በገንዘብ አያያዝ በደመወዝ አከፋፈል በጠቅላላ በተንቀሳቃሽ ሀብቱ ላይ ያለውን ሸክምና ችግር ልንረዳው እንችላለን። በደመወዝ አከፋፈል በኩል ነገሩን ስንመለከተው በአንድ ወታደር ደመወዝና በአንድ ሚኒስትር ደመወዝ፣ ከልዩ ልዩ የሀብት ገቢ ጋር ተዳምሮ ያለው ልዩነት በጣም የተራራቀ ነው።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የአስተዳደር ጉድለቶች ሌላ የተከለከሉ መብቶች አሉ። ለምሳሌ ያህል እነዚህን እንመልከት፡-

- የንግግርና የጽሑፍ ነፃነት የለም።
- የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን መብት በአንድ ሰው እጅ ብቻ ነው።

ከዚህ በላይ ዘርዝረን የጠቀስናቸውን ጉድለቶችና ሳይዘረዘሩ የቀሩትን ጉድለቶች የሚያስወግድ፣ ኢትዮጵያ የምትሻሻልበትንና ሕዝባም የሚበለፅግበትን ጐዳና የሚከፍት ሰላማዊ ለውጥ ነው። ይህንን ሰላማዊ ለውጥ ሁላችን እንደምንደግፈው የታመነ ነው።

የሚል ነበር። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፣ የመሐንዲስና የሕንፃ ኮሌጅ ተማሪዎችና በተማሪዎቹ ሰልፍ ተቀስቅሶ የወጣው እጅግ በጣም ብዙ ሕዝብ፣ በዋና ዋና መንገዶች መፈክሮችን ይዞ መዝሙሮችን እየዘመረ ድምፁን በማስተጋባት ከላይ የሠፈረውን ይዘት ያለውን በራሪ ወረቀት በመንገድ እየበተነ ሲጓዝ፤ የክብር ዘበኛ

ፓትሮል ጂፖች መንገዶችን በመጠበቅ እየተመላለሱ ሲቃኙና የሰላማዊ ሰልፈኞችን ደህንነት ሲጠብቁ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች አዲስ ክስተት ሆኖ አረፈደ።

በዚሁ ዕለት ከላይ በተገለጸው አኳኋን፣ በአዲስ አበባ ከተማ የለውጡ ስሜት ተነሣሥቶ ሲያረፍድ፣ በመፈንቅለ መንግሥቱ ተቃዋሚዎች በኩልም በተቃራኒው የተከናወኑ ድርጊቶች ነበሩ።

## የፈጥኖ ደራሽ ጦር የአቋም ለውጥ

ረቡዕ ማታ የፈጥኖ ደራሽ አዛዥ፣ ኮሎኔል (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ታደሰ ብሩ ከኮሎኔል ከበደ ዋጋዬ (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል) ጋር ተገናኝተው ሲነጋገሩ፤ ተባብረዋቸው የነበሩትን የመፈንቅለ መንግሥቱን መሪዎች ትተው "እኔ የማውቀው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ነው" በማለት ከጦር ሠራዊቱ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ መሆናቸውን ለኮሎኔል ከበደ ዋጋዬ ስለገለጹ፤ ኮሎኔል ከበደም ይህን አቋም ለሜጀር ጄኔራል መርዕድ ነገሯቸው። ጄኔራል መርዕድም የኮሎኔል ታደሰ ብሩን አቋም ለማረጋገጥ "የምትይዘው ግንባር እንስጥህ ወይ?" የሚል መልእክት አስይዘው ኮሎኔል ከበደ ዋጋዬን ወደ ፈጥኖ ደራሽ ጦር ሠፈር መልሰው ላኩዋቸው። ኮሎኔል ታደሰም "በደስታ እቀበላለሁ" ሲሉ በመመለሳቸው፤ እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድ ከመፈንቅለ መንግሥቱ እጅ ፈልቅቀው ያወጡት፣ በኮሎኔል ታደሰ ብሩ የሚመራው የፈጥኖ ደራሽ ጦር የሚይዘውንና የሚያጠቃውን ሥፍራ ወስነው ለመስጠት በመቻላቸው፤ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ኃይል አንዱን ክንፍ ሰብረው የድሉን የመጀመሪያ የምሥራች እንዳገኙ አመኑ። በእርግጥ የዘውድ ጠባቂው ወገን ድል የፈጥኖ ደራሹን ጦር ተባባሪነት ማግኘቱ ብቻ ሳይሆን፤ በጦር ታክቲክ ሥልጠናው ከክብር ዘበኛ ጋር የሚቀራረብ ስለሆነ፣ የጦር ሠራዊቱን ደካማ ጐን የሚያካክስ በመሆኑ ጭምር ነበር።[3]

ቀጥሎም፣ ሐሙስ ከንጋቱ ጀምሮ የጦር ሠራዊቱን የማደራጀት ተግባር በማፋጠን፣ ከዚህ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች ከየጦር ክፍሉ ተቀንሰው የነበሩት ሁሉ፣ በገዛ ፈቃዳቸው እየመጡ መሣሪያ ጠይቀውና ጠመንጃ አውጥተው በየክፍል አለቆቻቸው አማካይነት እንዲሰለፉ ተደረገ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት ከደብረ ብርሃን እንዲመጣ የተጠራው ጦር በጧት የካ ላይ ታግዶ በጄኔራል መንግሥቱ ትእዛዝ ሲለቀቅ፤ ያፈገፈገ መስሎ በሌላ አቅጣጫ አንደኛ ክፍለ ጦር አጠገብ መድፈኛ ግቢ ስለደረሰ፤ እሱንም የመከላከያ ቦታ ሲያስይዙ አረፈዱ።

በመፈንቅለ መንግሥቱ አራማጆች በኩል በመጀመሪያ ጧት ከሦስት ሰዓት በኋላ ደግሞ፣ ልዑል ራስ እምሩ በሽምግልናው በኩል ምን መደረግ እንዳለበት ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ተወያይተው ከፍተኛ ተደማጭነት የነበራቸውን፣ የልዑል አልጋ ወራሽ የቅርብ አሽከር ካፒቴን ኃይሉ ተክለ ማርያምን ከጥብቅ አደራ ጋር

[3] ይህንን፣ የጦር ሠራዊቱ መፈንቅለ መንግሥቱ የማክሸፍ ሥራ ለማደራጀት ካሳየው ብልጠት ማረጋገጥ ይቻላል።

ማስታወሻ አስይዘው እነ ሜጀር ጄኔራል መርዕድን ወደ ሽምግልናው ለማግባባት ላኩ።[4] በመቀጠል ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ሔደው "ነገሩ እየከፋ ሔዷል። ስለዚህ ከብፁዕ አባታችን ጋር ተነጋግሬ ከእኛም በኩል ተመካክሬ ስለ ፀጥታው አስፈላጊውን መፈፀም ይኖርብኛል" አሏቸው። እርሳቸውም "እሺ" ብለው ጄኔራል መንግሥቱን አስጠርተው ገለጹላቸው። ጄኔራሉም በበኩላቸው ፈቃደኛ ሆነው አውቶሞቢል እንዲቀርብላቸው አደረጉ። ስለጉዳዩ ልዑል ራስ እምሩ እንደገለጹት «ምንም አላወከኝም። ወዲያው ወደ ብፁዕ አባታችን ግቢ ሔድኩ። በሩ ተዘግቶ ግቢው ጭር ብሏል። ሰው አላገኘንም። በዚህን ጊዜ አብረውኝ የሔዱት ክብር ዘበኞች "እንመለስ" ስላሉኝ ተመለስኩ። እንደተመለስኩ ካፒቴን ኃይሉ ጠዋት የሔደ በስምንት ሰዓት ተመልሶ መጣ።››[5] ልዑል ራስ እምሩ እንዳሉት፣ ካፒቴን ኃይሉ በጧት ለሽምግልና ተልከው ከሔዱ በኋላ ሳይመለሱ የዋሉበት ምክንያት በትክክል አይታወቅም። እንደሚገመተው ግን፣ እነጄኔራል መርዕድ ካፒቴንን ወዲያው እንደደረሱ ተቀብለው ለማነጋገር ጊዜ ሊያገኙ ባለመቻላቸው ይመስላል። እነጄኔራል መርዕድ በዚሁ ዕለት ተደራራቢና አጣዳፊ በሆኑ ተግባሮች ከመያዛቸው በተጨማሪ በተላከላቸው የሽምግልና ድርድር በመጠቀሙ በኩልም የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ከነበራቸው ፍላጐትና ጥረት የተለየ አመለካከትና አዝማሚያ ያላቸው መሆኑም ግምት ውስጥ ሊያገባ ይችላል።

የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች በሽምግልና የመጠቀምን አስፈላጊነት ያጠነከሩት የአንድ ሰው ደም ሳይፈስ ለውጡ የተሳካ እንዲሆን በሚል አስተሳሰብ ነበር። ይህ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎችን ፍላጐትና ምኞት ዘውድ ጠባቂዎች እንደ ድክመት የወሰዱት ብቻ ሳይሆን፤ የተጀመረውን ለውጥ ለማክሸፍ የመደራጃ ጊዜ ማግኛ ዘዴ ስለሆነ እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ እንዲቀጥል አድርገው ከቆዩ በኋላ፣ አቅማቸው ሲጠናከር ሽምግልናውን ትኩረት ነፍገውታል። በዝግጅት ደረጃ ግን ረቡዕ ዕለት ፍጥነት በተሞላበት ሁኔታ የጀመሯቸውን ዝግጅቶች በዚሁ ዕለትም ማጠናቀቅና ሁኔታውን ማረጋገጥ ስለነበረባቸው፤ በተከታታይ የወሰዷቸው ዐበይት እርምጃዎች ለስኬታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እነርሱም ከጅማ፣ ከነገሌ ቦረና፣ ከጐንደር፣ ከሐረርና ከሌሎችም ቦታዎች በአየር ኃይል አውሮፕላኖች፣ በባቡርና በመኪና ተጓጉዞ በመምጣት የደረሰውን ጦር ሁሉ እንደ ደብረ ብርሃን ጦር በተመደበለት የመከላከያ ቦታ መግባቱንና የቀረውም በተመሳሳይ ሁኔታ ሊደርስ መቻሉን ያረጋግጡ ነበር።

የክብር ዘበኛን ጦር ሁኔታ ከራሳቸው ጦር አቋም ጋር በማነጻጸር፣ መፈንቅለ መንግሥቱ በተጀመረ ፵፰ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ተደራጅተው የማጥቃት ዘመቻ ለመጀመር የሚያስችላቸውን የዕዝ ሰንሰለቱን በተሟላ ሁኔታ አዋቅረው ነበር። በዚህ በዕዝ ሰንሰለት

---

[4] መጀመሪያ በፈጥኖ ደራሽ ጦር ተይዘው ከነበሩት ከሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤና ከሻምበል ይልማ በላቸው በኋላ ደግሞ አቃቂ ወህኒ ቤት ከገባን ከቀኛዝማች ተፈሪ ተክለ ማርያም የኮሎኔል ከበደ ዋጋዬ ሚስት ዘመድ እንደሰማሁት፤

[5] ልዑል ራስ እምሩ ለፍርድ ቤት ከሰጡት ቃል፤

ውስጥ፣ ከጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ አዛዥነት እስከ ፖለቲካና መንፈሳዊ ኃይል ሰጭዎች ድረስ በተረጋጋ ሁኔታ ተፈላጊ ኃላፊዎችን ለመመደብ ችለው ነበር።

በዚህ ጊዜ፣ ጄኔራል መርዕድ መንገሻ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ መኮንን ሲሆኑ፤ ጄኔራል ከበደ ገብሬ እንደዚሁ የምድር ጦር አዛዥ ሆነው ተመደቡ። የውጊያ መምሪያውም በሁለት ተከፍሎ እንዲቋቋም ተደረገ። እነዚህ ጄኔራሎች የውጊያ ኃላፊ ስትራቴጂስቶች ከመሆናቸው በላይ በተጨማሪ በውስጣቸው የተለያዩ የዘመቻ መኮንኖች፣ የመረጃና የፀጥታ፣ የፐርሶኔልና የሎጅስቲክስ ኃላፊዎች ተመደቡ። የስትራቴጂ መምሪያዎችም ተቋቋሙ። በዚሁ መሠረት ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ከበደ የውጊያው ኃላፊ ስትራቴጂስት ሆኑ።



ኮሎኔል ኃይሌ ባይከዳኝ

በአጠቃላይ የዘመቻውን ስምሪት አስመልክቶ የኮሎኔል ጃግማ የውጊያ ሪፖርት ዝርዝር መዋቅሩን ያሳያል። በሪፖርቱ መሠረት፦ የስትራቴጂክ መምሪያዎች ተቋቁመዋል። አባላቱም፦

፩ ኮሎኔል ኃይሌ ባይከዳኝ (በኋላ ሜ/ጄ) የዘመቻ መኮንን
፪ ኮሎኔል አበበ ገመዳ (በኋላ ሜ/ጄ) መረጃና ፀጥታ
፫ ኮሎኔል በለጠ አበበ (በኋላ ሜ/ጄ) ፐርሶኔል
፬ ኮሎኔል ከበደ ወርቁ ሎጂስቲክስ

**"የመንፈስ" ኃይልና የውጊያ አማካሪዎች**

| | |
|---|---|
| ፩ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ | የሃይማኖት መሪ |
| ፪ ብርጋዴር ጄኔራል ኢሣይያስ ገብረሥላሴ | የውጊያ ረዳት |
| ፫ ብርጋዴር ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ | የውጊያ ረዳት |
| ፬ ብርጋዴር ጄኔራል ዋቅጅራ ሰርዳ | የውጊያ ረዳት |
| ፭ ብርጋዴር ጄኔራል ያዕቆብ ገብረ ልዑል | የውጊያ ረዳት |

**የፖለቲካ ኃላፊዎች**

| | |
|---|---|
| ፩ ልዑል ደጃዝማች አሥራተ ካሣ | የፖለቲካ ረዳት |
| ፪ ደጃዝማች መንገሻ ወልደጊዮርጊስ | የፖለቲካ ረዳት |
| ፫ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ | የፖለቲካ ረዳት |
| ፬ ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል | የፖለቲካ ረዳት |
| ፭ ፊታውራሪ ወርቅነህ ወልደ አማኑኤል | የፖለቲካ ረዳት |




ኮሎኔል ኃይሌ ባይከዳኝ

| | |
|---|---|
| ፮ የሻለቃ አሰፋ ለማ | የውጊያና የፖለቲካ ረዳትና |
| ፯ አቶ ዳንኤል አበበ (በኋላ ደጃዝማች) | የውጊያና የፖለቲካ ረዳት ናቸው |

**የአዲስ አበባ የተዋጊው ብርጌድ ምድብ**

| | |
|---|---|
| ፩ ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ (በኋላ ሌ/ጀኔራል) | የተዋጊው ጦር አዝማች |
| ፪ ኮሎኔል ይልማ ሺበሺ (በኋላ ሜ/ ጀኔራል) | የተዋጊው ጦር ም/አዝማች |
| ፫ የሻለቃ ይልማ ዓለሙ | የዘመቻ መኮንን |
| ፬ የሻለቃ ወልደ ገብርኤል ወልደ መስቀል | ፐርሶኔል |
| ፭ የሻለቃ አበበ አላጌ | ሎጅስቲክስ |
| ፮ የሻምበል ወርቅነህ በላቸው | መረጃ |
| ፯ የሻምበል መረሳ ባህለቤ | ረ/ፐርሶኔል |
| ፰ የሻምበል ከበደ የኋላዬ | ረ/ሎጂስቲክናመረጃ |
| ፱ የመ/አ ተመስገን ገብረ ሥላሴ | ረ/ሎጂስቲክ |
| ፲ የሻምበል ደጀኔ ተሰማ | 4.2 ሞርታር አዛዥ |
| ፲፩ የመ/አ ዘገየ ሰንበት | 4.2 ሞርታር ተኩስ መምሪያ |
| ፲፪ ም/የመቶ አለቃ ተከሰተ ዐባይ | ማጓጓዣ አዛዥ |
| ፲፫ ሻምበል ባሕሩ ገሠሠ | የቃኚ ሻምበል አዛዥ[6] |


ሖሙስ ጧት በተደረገው በዚህ ድልድል ውስጥ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር አብረው እንዲመደቡ የተደረጉት ቢኖሩም፤ በመፈንቅለ መንግሥቱ አራማጆችና በተጻራሪ ኃይሎች ባለመግባባት፣ ያልተፈለገ ግጭት እንዳይነሣና ደም እንዳይፈስ ለመሸምገል ረቡዕ ዕለት ወዲያ ወዲህ በማለት ሲመላለሱ የነበሩት፣ ደጃዝማች ከበደ ተሰማና ጄኔራል ኢሣይያስ ገብረሥላሴም ይገኙበት ነበር:: ደጃዝማች ከበደ የሽምግልና ተግባር ይዘው አንድ ጊዜ አንደኛ ክፍለ ጦር፣ አንድ ጊዜ ደግሞ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ በመመላለስ ለማግባባት ሞክረዋል:: ጄኔራል ኢሣይያስም ከዚሁ የተለየ ሚና እንዳልነበራቸው ለፍርድ ቤቱ[7] ከሰጡት ቃል ለመገንዘብ እንችላለን:: ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ያን ያህል ጊዜ በክብር ዘበኛ



*ጃገማ ኬሎ በሻለቃ ማዕረግ*

[6] *የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ የውጊያ ሪፖርት*

[7] *ብ/ጄኔራል ኢሣይያስ ለፍርድ ቤት የሰጡት ምስክርነት ቃል*



ጃገማ ኬሎ በሻለቃ ማዕረግ

ጠቅላይ መምሪያና ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር በመመላለስ ባለሥልጣኖችን ሲያነጋግሩ፤ የግርግሩ ዕላማ ግልጽ ሳይሆንላቸው ቀርቶ ሳይሆን፣ ጄኔራል መንግሥቱ እንደተመኘ ት ሁሉ ያለ አንዳች ደም መፋሰስ ለውጡ እንዲካሔድ መደገፍ በመፈለጋቸው እንደሆነ ይገመታል:: የጄኔራል ኢሣይያስ ወልደ ሥላሴም አቋም ከዚሁ የተለየ እንዳልነበረ ቢገመትም፤ ሁለቱም በሰጡት ቃል ግን የወቅቱን አስተሳሰባቸውን በይፋ አላወጡትም:: ለምሳሌ ደጃዝማች ከበደ በራሳቸው በኩል የነበረውን እምነትም ሆነ ጥረት ስለሽምግልናው የመጨረሻ ሁኔታ ጭምር የገለጹት፤

> በመጨረሻ ከጄኔራል መርዕድ ጋር ተገናኘቼ "እባካችሁ ተሸማገሉ:: ነገሩ በሰላም ቢያልቅ ይሻላል" ብዬ ጠየቅሁት:: ጄኔራል መርዕድ፣ "መንግሥቱ ንዋይ የጃንሆይን መንግሥት አፍርሶ ሌላ መንግሥት አቋቋምኩ እያለ ምኑን ተሸማገልነው" በማለት የመንግሥት ለውጥ የተደረገበትን ዐዋጅ ቴፕ ከፍቶ አሰማኝና "እንግዲህ ምን ይላሉ?" አለኝ:: እኔም ነገሩ እስከዚህማ ከደረሰ እዚህ ካላችሁት እንደ አንዳችሁ ሁኜ የሚያስፈልገውን ማደራጀት ነው የሚኖርብኝ አልኩትና ጉዳዩን አንድ በአንድ ተነጋግረን ወደ ሥራ ተሰማራን::

በሚል ነው እንጂ በሰላማዊ መንገድ እስከሆነ ድረስ የሙከራውን መሳካት ይሹ እንደነበረ አይጠቅስም::

ደጃዝማች ከበደ ለሽምግልና ላይ ታች ሲሉ የነበረው መፈንቅለ መንግሥቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈጸም ከነበራቸው ብርቱ ፍላጐት አንጻር እንጂ አሁን ለኅትመት የተዘጋጀው የሕይወት ታሪካቸው ማስታወሻ ረቂቅ ላይ፣ የመፈንቅለ መንግሥት ጥንስስ መኖሩን ከጥቂት ቀናት በፊት ያውቁ እንደነበር ጠቁመዋል::[8] ደጃዝማች ከበደ ለፍርድ ቤት በምስክርነት የሰጡት ቃል ግን ሽምግልናውን ትተው የወሰዱትን አቋምና መፈንቅለ መንግሥቱን ለማክሸፍ የተሰማሩበትን የመንፈስ ኃይል ለጭነት ሥራ ያስገነዝባል::

እንሽመግላለን ብለው አንድ ግዜ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንደኛ ክፍለ ጦር በመሄድ ከላይ ከታች በማለት ሲደክሙ የነበሩት፣ እነዚህ ሁለት የታወቁ ሰዎች የኃይል ሚዛኑ ወደየት እያዘነበለ እንደሔደና የማሸነፊያው ካርድ፣ ወደነጄኔራል መርዕድ እጅ እየገባ መሆኑን ተረዱ:: ከዚያ በኋላ በከፋፍለህ ግዛው ፍልስፍና ሊቅ የሆነው ማኪያቬሊ "ዘ ፕሪንስ" በተባለ መጽሐፉ እንደገለጸው፣ "ልታሸንፋቸው ካልቻልክ ከነሱ ጋር ሁን" ያለውን ፈሊጥ ተቀብለው ከእነ ጄኔራል መርዕድ ጋር ወገኑ:: እንደውም ስለ ጉዳዩ አንድ በአንድ ተነጋግረው ከፈፀሙ በኋላ በፕሮፓጋንዳ አራማጅነት ምድብ ተሰማሩ ማለት ነው::

የአዲስ አበባ ከተማ በሰላማዊ ሰልፈኛው ተሟሙቃ በምትታይበት ሐሙስ እረፋድ ላይ የዘውዳዊ አስተዳደር ደጋፊዎች በአንደኛ ክፍለ ጦር ተሰብስበው፣ ከላይ

---

[8] በአሜሪካ በልጃቸው በአቶ ካሣ ከበደ እጅ የሚገኝ ረቂቅ

የተዘረዘሩትን ተግባሮች በማከናወንና ከጠቅላይ ጦር አዛዥ እስከ መንፈሳዊ ኃይል ሰጭነት ድረስ የዕዝ ሰንሰለታቸውን አዋቅረው በመሿሿም ላይ እንዳሉ፤ በመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች እጅ ያለው የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የዐዋጅ መግለጫ ማሰማት ጀመረ:: የሬዲዮ ጣቢያው እንደ ረቡዕ ዕለት ሁሉ መጀመሪያ አዲስ ሕዝባዊ መንግሥት መቋቋሙን አሰምቶ፣

፩ኛ. ልዑል አልጋ ወራሽ ለተቋቋመው አዲስ ሕዝባዊ መንግሥት የበላይ መሪ መሆናቸውን፣

፪ኛ. ልዑል ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

፫ኛ. ሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ የጦር ኃይሎች ኤታ ማዦር ሹም ሆነው መሾማቸውን፤ በማርሽ እያጀበ በመግለጽ የመንግሥት ለውጡ በሰላማዊ መንገድ መከናወኑን አበሠረ:: አያይዞም "የልዑል ራስ እምሩን ማንነት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: እርሳቸውን ማስተዋወቅ አያስፈልግም:: ራስ እምሩ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚወዱ ለዕድገቷ የሚጥሩ ታላቅ ሰው ናቸው:: ስለዚህ፣ ሁላችንም ተባብረን ለአመራራቸው ድጋፍ በመስጠት ኢትዮጵያን እናራምዳት" እያለ ሬዲዮኑ የዐዋጅ መግለጫውን እየደጋገመ ሲያሰማ ቆየ::

፬ኛ ከቀኑ ፩ ሰዓት ከ፲ ደቂቃ ሲሆን ቀጣይ ዐዋጅ ተነገረ:: ይኸውም ስለሽረት ዐዋጅና ለወታደር ደመወዝ መጨመሩን የሚያበስር ዜና ነበር:: የሽረት ዐዋጁ የተመለከታቸው ሜጀር ጄኔራል መርዕድንና ሜጀር ጄኔራል ከበደን መሆኑን ይገልጻል፤ አቀራረቡም ሁለቱን ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ልዑል አልጋ ወራሽ ቤተ መንግሥት ድረስ ጠርተው፣ ኢትዮጵያን ወደ ዕድገት ሊመራ የሚችል ሕዝባዊ መንግሥት በማቋቋሙ ዐላማ ጦሩ ሳይከፋፈልና የእርስ በእርስ ግጭት ሳይፈጠር፣ ለውጡ በሰላም እንዲጠናቀቅ ትብብር እንዲያደርጉ መልእክተኞች ተልከ ለማግባባት ተሞክሮ እንደነበር፤ ሁለቱ መኮንኖች ግን አንተባበርም በማለታቸው መሻራቸውን የሚገልጽ ነው:: ለወታደር የተደረገውን የደሞዝ ጭማሪ የሚያበስረው ዜና ደግሞ ጭማሬው ከተራ ወታደር እስከ ሻምበል ባሻ ድረስ፣ የመነሻ ደመወዝ ብር አርባ፣ ከም/መቶ አለቃ እስከ ሻለቃ በሚያገኘው ደሞዝ ላይ ብር ሃምሳ ጭማሪ መፍቀዱን አስረዳ:: ከዚህ በተጨማሪ አዲስ የግብር ጭማሪ እንዲቀርና ቦታ የሌለው ወታደር ባዶ ቦታ እየፈለገ ቤት እንዲሠራ መብት መጉናፀፉ ተገለጸ::

ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. እስከ እኩለ ቀን ድረስ፣ በመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች የተወሰዱት እነዚህን የመሳሰሉ ተከታታይ የለውጥ መግለጫ ዐዋጆችና የተማሪዎች የድጋፍ ሰልፍ የዘውድ ጠባቂውን ወገን በጣም እያሳሰበው መጣ:: የሜጀር ጄኔራል መርዕድና የሜጀር ጄኔራል ከበደ ተሽረዋል መባልና፣ በተለይም የወታደር ደመወዝ መጨመር ከመፈንቅለ መንግሥቱ በተቃራኒ የተያዘውን ዐላማ ያከሽፋል ብሎ በመሥጋት፣ የአጸፋ ፕሮፓጋንዳ የያዙ በራሪ ወረቀቶችን በፍጥነት

በአዲስ አበባ ከተማ መበተን የጭንቀቱ ነጸብራቅ ሆነ። ይህንንም ያቀላጠፈላቸው የአየር ኃይል ምክትል አዛዡ ኮሎኔል አሰፋ አየነ፣ ረቡዕ ታኅሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከጄኔራል መርዕድ ጋር በሬዲዮ ቴሌፎን ተገናኝተው፣ የአየር ኃይሉ ከጦር ሠራዊቱ ጋር በመሰለፍ የዐፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሕልውና ለመጠበቅ መቆሙን ማረጋገጣቸው ነው። ጄኔራል መርዕድ አሥመራ ከሚገኙት ከንጉሠ ነገሥቱ የፌዴራል መንግሥቱ ተጠሪ ከሜጀር ጄኔራል ዐቢይ ጋር በሬዲዮ ተገናኝተው፤ የቃኘው ሬዲዮ ጣቢያን ጠይቀው ሊጠቀሙ እንደሚችሉ በዚያው ሬዲዮ ጣቢያ ከጃንሆይ ጋርም መገናኘት እንደሚቻል ሲነጋገሩ ጄኔራል ዐቢይ መገናኘቱን መጀመራቸውን አበሠሩላቸው።

ከዚህ በኋላ ኮሎኔል አሰፋ የአየር ኃይል የመገናኛ ዋና ክፍል ኃላፊውን የሻምበል (ኋላ ሻለቃ) ጠለለ ቸርነትን ታኅሣሥ ፯ ቀን አሥመራ ሄዶ ከሜጀር ጄኔራል ዐቢይ ጋር በመገናኘት፣ በፓትርያርኩ ስም ተዘጋጅቶ በአውሮፕላን የሚበተን ወረቀት ባስቸኳይ እዚያ ታትሞ (አዲስ አበባ ማሳተም ስለማይቻል) አዲስ አበባ በአውሮፕላን ለመበተን እንዲችል የጄኔራል ዐቢይን ትብብር እንዲጠይቅ ላኩት። አብዛኞቹ የአየር ኃይል ቦምብ ጣይና ማጓጓዣ አውሮፕላኖች የነበሩት አሥመራ ስለነበረ፤ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ቀደም ብሎ ቢጠየቅም፤ አልተፈቀደም ነበር። ምክንያቱም ለነጄኔራል ዐቢይ አየር ኃይሉ ከማን ጋር እንደሆነ ግልጽ ስላልነበረና ኮሎኔል አሰፋ አየነንም ይጠረጥሩዋቸው ስለነበር ነው። አሁን የኮሎኔሉ ከዘውድ ጠባቂው ወገን ጋር ማበር ስለተረጋገጠላቸው ‹‹እሺ ይሔዱ›› ብለው ፈቀዱ።

በሌላ ጎኑ ደግሞ ተማሪዎች ለውጡን ደግፈው በከተማው ዋና ዋና ክፍሎች ተዘዋውረው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ሲያመሩ፤ በባቡር ጣቢያ አጠገብ ዛሬ ብሔራዊ የኢንሹራንስ ኮርፖሬሽን ሕንፃ ከተሠራበት ፊት ለፊት ካለው መስቀለኛ መንገድ ላይ ደረሱ። ያን ጊዜ እኔም ለመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ሪፖርት አድርጌ ተመልሼ ከተማሪዎቹ ሰልፍ ተቀላቀልኩ። በቁጥር ፳ የሚሆኑ የጦር ሠራዊት ወታደሮች ጠመንጃ ወድረው መትረየስ ጠምደው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር የሚወስደውን መንገድ በመዝጋት የሚጓዘውን ሰልፈኛ አገዱት። እነዚህን ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር የሚወስደውን መንገድ ዘግተው የያዙትን ወታደሮች ሰልፈኛው ጥሶ ለማለፍ ሙከራ ቢያደርግ ውጤቱ እልቂትን የሚያስከትል ሆኖ እየታየ ሳለ፤ ሦስት የክብር ዘበኛ ማክ መኪናዎች በፍጥነት በመምጣት መንገድ ዘግተው ይዘው የነበሩትን ወታደሮች መንገዱን አስለቀቋቸው። ሰልፈኛውም ጉዞውን ወደ አሰበው ቦታ ለመቀጠል ተነሣሣ። እኔም መኪኖቹ መንገዱን ሲያስከፍቱ ከተማሪዎቹ አንዱ የነበረውን አቶ ዮሐንስ ክፍለን በኋላ (የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የፕሮቶኮል ሹም) እንሒድ ስለው፤ ከተማሪዎቹ ጋር ሰልፍ ውስጥ የነበረው መምህር ጋሼ መስፍን (በኋላ ፕሮፌሰር) ወታደሮቹ አውሬነት ይታይባቸዋል "ሳቤጆች" ናቸው። ሊተኩሱ ይችላሉና አይሆንም ተመለሱ ብሎ መቆጣቱን ነገረኝ። ሰልፈኛውም እንደተመከረው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር ለመሔድ ጀምሮት የነበረውን ጉዞ ለውጦ ወደ

ራስ ሆቴል አቅጣጫ ዞረ። ከዚያም ተማሪዎቹ ሰልፉን ሲያካሒዱ አርፍደው ሁሉም ወደየራሳቸው ግቢ ጉዞ ጀመሩ።

ከዚህ በኋላ ደግሞ የአየር ኃይሉ እንቅስቃሴ ቀጠለ። በፓትርያርኩ ስም ተዘጋጅቶ የሚበተነው በራሪ ወረቀት በአስቸኳይ ታትሞ ለሻለቃ ጠለለ ከተሰጠ በኋላ እግረ መንገዳቸውን መቀሌ፣ ደሴና አዲስ አበባ በተኑ። ትንሽ ቆየት ብሎ ፓይለቶቹ የክብር ዘበኛን ዋና መሥሪያ ቤትና አካባቢውን ብቻ ደበደቡ። አደባደቡ ግን ፓይለቶቹ ትዕዛዙን ከልብ የተቀበሉት እንደማይመስል ያሳይ ነበር። ምክንያቱም አጠቃላይ ሁኔታው ዕልቂት ሳናስከትል ከሚለው የአዛዡ ትዕዛዝ በላይ ፓይለቶቹ አነጣጥረው ጉዳት ለማድረስ ሳይሆን፤ ትዕዛዙን ለመፈፀም ያህል ያደረጉት የግብር ይውጣ ይመስል ነበር። በድብደባው ወቅት እኔ ቤተሰቤን ከመኖሪያዬ ከራስ ደስታ ሆስፒታል ጀርባ አንሥቼ ጉዳቱ ይቀላል ብዬ ወዳልኩበት ወደ ቀበና ወደ አቶ ዳኘው ወልደ ሥላሴ (በኋላ አምባሳደር) ቤት ይዤ ተጓዝኩ። እመንገድ ላይ በልዑል ሣኅለ ሥላሴ ግቢ አጠገብ በጽሕፈት ሚኒስቴር በስድስት ኪሎ አድርጌ ስሔድ በጃንሜዳና በክብር ዘበኛ መኮንኖች መኖሪያ መሐል ስደርስ አንድ አውሮፕላን በራሳችን ላይ የመትረየስ ጥይት አዝንቦብን አለፈ።

የአየር ኃይል አውሮፕላን በክብር ዘበኛ ጦር ሠፈርና በከተማው የበተነው በራሪ ወረቀት መልዕክት ፍሬ ነገር፤ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሕልውና የተጠበቀ መሆኑንና የወታደር መነሻ ደሞዝ ብር ሃምሳ እንደሚሆን የሚገልጽ፤ ረፋዱ ላይ ከሥልጣን ተወግደዋል የተባሉትን ሁለት ጄኔራሎች ፊርማ የያዘ ነበር። እንዲሁም፣ ንጉሡን የከዳ ውጉዝ ይሁን የሚል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን የውግዘት ቃልም ይዞ ነበር።

በዚህ ዓይነት ሁለቱ ተጻራሪ የጦር ክፍሎች በየበኩላቸው በመካረር ለፍልሚያ ተዘጋጁ። በመሆኑም፣ እነ ጄኔራል መርዕድና ለዘውዳዊው አገዛዝ ሕልውና መቀጠል በግንባር ቀደምትነት የተሰለፉት የጦር ሠራዊት ከፍተኛ መኮንኖች የክብር ዘበኛ ጦር የሚገኝበትን ሁኔታ፣ ቦታ አያያዙን፣ አሰላለፉን፣ በአጠቃላይ ጥንካሬውንና ድክመቱን በመገምገም ያወጡትን የማጥቃት የውጊያ ፕላንና ስልት አፀደቁ። ተባባሪ ሆኖ ለተገኘው ለአየር ኃይልም የውጊያ ትእዛዝ በቴሌግራም አስተላለፉ። የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ለመፈንቅለ መንግሥቱ ድል ማስጨበጫ ይሆናል ብለው ተስፋ የጣሉበት ኃይል ግን ሁለት ያልተሟሉ ብርጌዶች ጦር ነበሩ። የዘውዳዊ አስተዳደር ደጋፊ ክፍል የጦር አዝማች የነበሩት ኮሌኔል ጃገማ ኬሎ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኋላ ለበላይ አዛዣቸው ባቀረቡት ጠቅላላ የውጊያ ዘገባም ይህንኑ አረጋግጠዋል። ዝርዝሩም

> ለጥበቃ:- ሁለት ያልተሟላ ሻምበል ጦር ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥትን፣ የልዑል ሣኅለ ሥላሴንና የልዑል መኮንን ግቢ፤ አንድ ያልተሟላ ሻምበል ፫ኛ ሻለቃ ሠፈርንና የክብር ዘበኛ መሥሪያ ቤትን፤ አንድ የመቶ ጦር የፀጥታ መሥሪያ ቤትንና የውሀ ክፍልን፣ አንድ ሌላ የመቶ ጦር ደግሞ፣ የፕሮፓጋንዳን (የማስታወቂያ) ጽህፈት ቤትን፣ ከዚህ

በኋላ ደግሞ ኃይሉ እንቅስቃሴ ቀጠለ። ምክንያቱም ክብር ዘበኛ ፈረሰኛ ክፍል የክብር ዘበኛ መድፈኛ ግቢ፣ ከባድ አጻፍኔ ክፍል ደጃዝማች መሸሻ ሠፈርን፣ ጊዮርጊስ አካባቢንና ታች ግቢን፤ አንድ ጓድ ከፖሊስ ጋር በመሆን ባንክን፤ አንድ የመቶ ጦር የፖስታ ሚኒስቴርንና የቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤትን፤ አንድ ያልተሟላ ሻምበል የክብር ዘበኛ ጦር ከፖሊስ ጋር ሆኖ በከተማው እየተዘዋወረ ሕግ እንዲያስከብር፣ አንድ የመቶ ደግሞ የግርማዊት እቴጌን ቪላና አካባቢ፣ አንድ ያልተሟላ ሻምበል ፫ኛ ሻለቃ ሠፈርንና የክብር ዘበኛ ሐኪም ቤት፤ አንድ ያልተሟላ ሻምበል በጆማ በር ያለውን ቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤት፣ አንድ ሌላ ያልተሟላ ሻምበል ደግሞ በናዝሬት በር የሚገኘውን መስመር፤ አንድ ጓድ ቀ.ኃ.ሥ አውሮፕላን ማረፊያ (አሮጌውን) እንዲጠብቅ አሰማርቷል[9]

የሚል ነው።

የክብር ዘበኛ ያወጣው የዘመቻ ግዳጅ

፩. አንደኛ ብርጌድ ለጥበቃ አሰማርቶ ከተረፈው ኃይል ላይ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ተደርቦለት፣ ከጠቅላይ ሠፈሩ ከአራዳ ጊዮርጊስ ተነሥቶ በሱማሌ ተራ በተክለ ሃይማኖት ቁልቁል ወርዶ በገነት ሆቴል ያደርግና ወደ ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በማቅናት አንደኛ ክፍለ ጦርን ከጀርባ አጥቅቶ መያዝ ነበር።[10] ይህንኑ ለማሣካት ሐሙስ አራት ሰዓት ገደማ ጄኔራል መንግሥቱና ጄኔራል ጽጌ ዲቡ ተገናኝተው ምናልባት ከጦር ሠራዊቱ ጋር ግጭት ቢፈጠር የፈጥኖ ደራሽ ጦርን ከክብር ዘበኛ ጦር ጋር የጥምር ውጊያ እንዲያደርግ ከፈጥኖ ደራሽ ሹማምንት ጋር ለመነጋገር የሻምበል ይልማ በላቸውን ከአንድ የፖሊስ ሻምበል ጋር አገናኝተው ይህንኑ መልእክት እንዲነግሩ ወደ ኮልፌ ፈጥኖ ደራሽ ጦር ሠፈር ላኩ። በር ላይ ሲደርሱ ዘቡ በሩን ዘግቶ አላስገባም አላቸው። ከዚያ የዘብ ኃላፊው መጥቶ ካነጋገራቸው በኋላ ተመለሱ ብሎ በማንገራገር በቁጥጥር ሥር ለማዋል ካሰበ በኋላ በሉ ዝም ብላችሁ ተመልሳችሁ ሒዱ ብሎ ሰደዳቸው። ወዲያው ሁለቱ መኮንኖች ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ሂደው ሁኔታውን መጀመሪያ ላዘዙዋቸው ጄኔራሎች ገለጹ። ጄኔራል ጽጌ የሻምበል በኋላ የሻለቃ ገድሉ ኃይሉ የተባለውን የፖሊስ መኮንን ከሻምበል ይልማ ጋር አያይዘው የመጀመሪያውን መልእክት አሲይዘው ወደ ፈጥኖ ደራሽ በድጋሚ ላኩዋቸው። ያ ዘብ አሁንም ተመለሱ እያለ ሲያንገራግር የዘብ ኃላፊው መጣና በቁጥጥር ሥር አዋላቸው።

በማግሥቱ ዐርብ ሻምበል ይልማንና አንደኛ ብርጌድን ያዘመተው የሻለቃ ተፈራ ወልደ ትንሣኤንና አብሮት የነበረውን አንድ ጓድ ጦር ፈጥኖ ደራሽ በቁጥጥር ሥር አቆይቷቸው ስለነበር እነሱንም ወደ ጦር ሠራዊት ፖሊስ መምሪያ ግቢ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ወደ ደቡብ ምሥራቅ አሁን ቶታል ሦስት

[9] የኮሎኔል ጃግማ ኬሎ ሪፖርት፤

[10] በዚህ ግዳጅ ውስጥ የተሳተፈው ሻምበል ይልማ እንደነገረኝ፤

ቁጥር ማዞሪያ አጠገብ ወስደው አስረከቧቸው። ቅዳሜ እነሱን ይጠብቁ የነበሩት የሚሊተሪ ፖሊስ አባሎች በሁሉም ላይ ጠመንጃ በመወደር "እናንተ ከሀዲዎች! ደግሞ እናንተ ምን ሆንን ብላችሁ ነው በንጉሡ ላይ ያመፃችሁት?" "ሁላችሁም ዋጋችሁን ታገኛላችሁ" እያሉ ሲዝቱባቸው፣ በአጋጣሚ ሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ በተኩሱ ጉዳት የደረሰባቸውን ወታደራዊ ክፍሎች እየዞሩ ይጐበኙ ነበርና ወታደር ፖሊስ ግቢ ሲገቡ በተያዙት የክብር ዘበኛ ጦር አባሎች ላይ የተደቀነውን ዓይተው "ምንድን ነው? ምን ልታደርጉ ነው" ብለው ሲጠይቁ፣ "ልንረሽናቸው ነው" ብለው መለሱላቸው። "አይ፡ አይደለም! ብዙ የሚጠብቃቸው ነገር አለ። እንዳትነኳቸው" ብለው ሔዱና ወዲያው ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር (በኋላ አራተኛ) እንዲላኩ በማድረግ ከሞት ተረፉ።

፪. የአንደኛ ክፍለ ጦር መያዝ እንደተረጋገጠ፣ አንድ ያልተሟላ ሻምበል ጦር ወዲያው ወደ ደብረ ዘይት ወርዶ የአየር ኃይልን እንዲይዝ፣

፫. አውሮፕላን ማረፊያ (አሮጌውን) እንዲቆጣጠር፣ ይህም ሁለተኛ ብርጌድ ከጥበቃ ከተረፈው ኃይል ላይ የሸዋ ፖሊስ ተደርቦለት ከጠቅላይ ሠፈሩ ከክብር ዘበኛ መኮንኖች ሠፈር ተነስቶ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን በቀኙ አድርጎ ወርዶ በጥይት ቤትና በታላቁ ቤተ መንግሥት መሐል ዘልቆ ከወጣ በኋላ ጦሩን ከሁለት በመክፈል አንዱ በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥትና በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስትያን መሐል በማለፍ የራስ ብሩን ቤት በጋሻው[11] ትቶ ወደላይ በመዝለቅ አንደኛ ክፍለ ጦርንና የመድፈኛ ክፍልን መያዝ፣ ሌላው ክፍል፣ የራስ ብሩን ቤት ወደ ቀኝ እየተወ በድንጋይ መፍለጫ በኩል አልፎ አንደኛ ክፍለ ጦርን ከምሥራቅና ከደቡብ በኩል አጥቅቶ መያዝ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የታንከኛ፣ የብረት ለበስና የፈረሰኛ ክፍል ጠቅላይ ሠፈሩን ፈረሰኛ ሠፈር አድርጐ አንዱ ክፍል በቸርችል ጐዳና ቁልቁል በመውረድ፣ ሁለተኛው ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ይመጣና ወደ ፖሊስ ጋራጅ በመውረድ፣ ሦስተኛው ክፍል በታላቁ ቤተ መንግሥት በኩል ወርዶ በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት አድርጐ በሁለቱ ፍል ውሃዎች መሐል የእንጨት ድልድዩን ተሻግሮ በማለፍ፣ ሦስቱም በጣምራ መከላከያን ከበው፣ አጥቅተው ከያዙ በኋላ፣ ወደ ብሔራዊ ትያትር አቅጣጫ በመዝለቅ ከሁለቱ ብርጌድ መካከል ድጋፍ ለጠየቀና ለሚያስፈልገው መርዳት የሚል ነበር።

በሁለቱ ተፋላሚ ቡድኖች መካከል ዝግጅቱ በዚህ መልኩ እየተጠናቀቀ ሲመጣ፣ የሽምግልናው መጨረሻ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ ግልጽ እየሆነ ሔደ። ጄኔራል መንግሥቱ የለውጡ አቋራጭ ጐዳና የኃይል እርምጃ መሆኑን የሚያውቁ ቢሆንም፣ በተቻለ መጠን ሰላማዊው መንገድ ዕድል እንዲያገኝ ብርቱ ፍላጐትና ጠንካራ አቋም ነበራቸው። ሆኖም፣ የሽምግልናው ጥረት እስከምን ደረጃ መቀጠል እንደነበረበትና ከለውጡ ዐላማ አንጻር ሊያስገኝ የሚችለው ፍሬያማ ውጤት መኖር

[11] ጋሻው የሚለው ጋሻ በሚያዝበት በግራው ለማለት ነው። ግራ የሚለው ቃል አሉታዊ ትርጉም አለው።

አለመኖር በቅድሚያ[12] በጋራ የተጤነ እንዳልነበረ ግልጽ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል ጄኔራል መንግሥቱ በሌላ በኩል ደግሞ በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁና በገርማሜ ንዋይ መካከል በስትራቴጂም ይሁን በታክቲክ መገጣጠም አልነበረም፡፡ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና አቶ ገርማሜ የሽምግልናው ሙከራ ጊዜ እየወሰደ በሔደ ቁጥር የሚያመጣው ውጤት አደጋ ከመሆን ሊያልፍ እንደማይችል አስጠንቅቀው ነበር፡፡ ጄኔራል መንግሥቱ ደግሞ እንቅፋቶችን በኃይል ለማስወገድ መነሣቱ የተጠላውን የደም መፋሰስ ያስከትላል የሚል ሥጋት ነበራቸው፡፡ ስለዚህ በሽምግልናው በኩል መግባባት ተፈጥሮ አገሪቱን ወደ ተሻለ የዕድገት ደረጃ የሚያራምድና ፈር የሚያሲዝ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ለማሳመን በሚደረጉ ጥረቶች ልዩነቶች ሊታረቁ ይችላሉ የሚል ፅኑ አቋም በመያዝ፤ ሁኔታዎቹ ተባብሰው እስከተደቀኑበት ጊዜ ድረስ አልተቀበሉትም ነበር፡፡

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አደጋውን አስቀድሞ ከመገንዘቡ የተነሣ ቁጭት ላይ ወድቆ እንደነበር ያጫወተኝ የሻለቃ መላኩ በቀለ ትውስታ ሁኔታውን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

> ደጃዝማች ከበደ ከጄኔራል መንግሥቱ ጋር ሲነጋገሩ ደረስኩ፡፡ እኔ እነሱ ከሚነጋገሩበት ቦታ አልፌ ወደ ወታደሮቹ ሔድኩና "እነማን አሉ?" ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ ወታደሮቹም፣ "ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እዚያ አሉ አሉኝ"፡፡ ሔድኩና እሱ ከሚገኝበት ክፍል ገብቼ "ወርቅነህ ምን ሆነሃል?" ብዬ ጠየኩት፡፡ (ያንድ ኮርስ መኮንኖችና አብሮ አደጎች ናቸው)፤ "አትጠይቀኝ" አለኝ በቁጣ፣ "ምነው ወርቅነህ ንገረኝ እንጂ!" አልኩት፡፡ "የማውቀው ነገር የለም! አትጠይቀኝ እኮ ነው የምልህ!" አለኝ፡፡ አሁንም "እንዴ! ኧረ ባክህ! የሆነውን ብትነግረኝ ምንድን ነው?" አልኩት፡፡ አሁንም ተቆጣኝና "አበላሽተውታል! ከዚህ ሌላ የምነግርህ የለም" አለ፡፡ በቃ ይህ ነበር የእርሱ ቃል፡፡[13]

ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በተጨማሪ የክብር ዘበኛ መኮንኖችም ከመሪ ውጭ መሆናቸው እስከሚሰማቸው ድረስ ፍፃሜው እያሳሰባቸው መደረግ የሚገባውን አስፈላጊ እንቅስቃሴ ለመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ከማሳሰብና ከመምከር አልተቆጠቡም ነበር፡፡ ለምሳሌ የሻለቃ ተፈራ በላይ "ተጨማሪ የጦር ሠራዊት ከያቅጣጫው በመምጣት ላይ ነው፡፡ መዘዋወርም ጀምሯል፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁኔታው ከሚያሠጋ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ በበኩላችን የተዘጋጀ ጦር ስለአለን እርምጃ መውሰድ ይኖርብናል" ብለው እንዳሳሰቡ ይናገራሉ፡፡ ይህን የመሰለ ማሳሰቢያ በክብር ዘበኛ መኮንኖች በተሰነዘረ ቁጥር ጄኔራል መንግሥቱ "እናንተ የሚያገባችሁ ነገር የለም፡፡ አልጋ ወራሽ "አይሆንም" ብለዋል፡፡ እርምጃ ለመውሰድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች ወደ እናንተ ይመጣሉ፡፡ ስለዚህ በዚያው በቦታችሁ ሆናችሁ የሚሰጣችሁን ትእዛዝ ተጠባበቁ" የሚል ትእዛዝ ብቻ ደጋግመው

---

[12] እኔ በቅድሚያ ባላውቀውም በሒደት የታየው እንደዚያ እንደሆነ ነው፡፡

[13] ሻለቃ መላኩ በቀለ

ይሰጡ ነበር። ይህም በራሱ ያስከተለው ቅሬታ ነበር። ስለዚሁ ቅሬታ ያጫወቱኝ ሻለቃ ተፈራ በላይ ሁኔታውን እንዲህ ያስታውሱታል።

> "በየቦታችሁ ሆናችሁ ትእዛዝ ጠብቁ። የሚያገባችሁ ነገር የለም!" የሚል መልስ ተደጋግሞ ከተሰጠን በኋላ፣ መኮንኖች ሁሉ ተከፋን። እንኳን መንግሥት ግልበጣን ያህል ነገር፣ አንድን የጦር ክፍል ለመቆጣጠር እንኳ ሳይዘጋጅበት መድረስ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የጦር ሠራዊቱ ሳይዘጋጅ መድረስ እየተቻለ፣ አይሆንም ሲባል በእውነቱ ከመሪ ውጭ እንደሆን ተሰማን"

ይላሉ። ስለዚህ እንደየሻለቃ ተፈራ በላይ ብዙዎቹ የክብር ዘበኛ መኮንኖች "ቁመን በማየትና ጊዜ በመስጠት በራሣችን ላይ እሳት ልናነድ እና ልንቀደም ነው…።" እያሉ መብሰልሰል ብቻ ነበር።

ይህ ዓይነቱ ግራ መጋባት የተፈጠረው፣ በመኮንኖች ስነልቦና ብቻ ሳይሆን፤ በጠቅላላ የነገሩን ልክ ሳያውቅ ማክሰኞ ዘብ ገብቶ ውሎ ያደረውና፣ ረቡዕ ዕለት ጃንሜዳ ክተት ተብሎ በገባው በክብር ዘበኛ ጦር ሁሉ ነበር። ሠራዊቱ አንድ ላይ ተሰብስቦ፣ የተሰበሰበበትን ምክንያት ከሹክሹክታ በቀር ጉዳዩን በውል ሳይረዳ እስከ ረቡዕ ማታ ረሃብ፣ ውሀ ጥም፣ ፀሐይና ብርድ እየተፈራረቀበት ቆይቶ፤ ዳቦና ሰርዲን የተሰጠው ወደ ዘጠኝ ተኩል አካባቢ ነበረ። ሐሙስም እንዲሁ ውሎ የተሰጠው ዳቦና ሰርዲን በመሆኑ፤ ድካሙ ተባብሶበታል።

በዘውድ ጠባቂው ወገን የነበረው ግምት በአገር ውስጥ የክብር ዘበኛን ጦር የሚቋቋም ምንም ኃይል የለም የሚል ነበረ። ነገር ግን የፓትርያርኩ ውግዘት ቃል በራሪ ወረቀት ከቀኑ ስምንት ሰዓት የክብር ዘበኛ ሠራዊት ባለበት ሁሉ በአውሮፕላን ተበትኖ ሠራዊቱ ደርሶት ሲያነበው እንደተገመተው ሁሉም የሥነ-ልቡና ውድቀት አጋጥሞት አንገቱን ደፋ፤ አዘነ። እንኳን ለመዋጋት ባለበት ተረጋግቶ መቆም አቃተው፤ አስጠላው። ውግዘቱ ሠራዊቱን ከመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ስለለየው የመፈንቅለ መንግሥቱን ኃይል ክንፉን የተመታ አሞራ አደረገው። የተበተነው ወረቀት መልእክት ይዘትም የሚከተለው ነበር።

የተላከው ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ መሆኑን ገልጸ:-



ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ

> ለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ልጆቼ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ:: ትላንት ታኅሣሥ ፬ ቀን ከምሽቱ በ፬ ሰዓት፣ ንጉሠ ነገሥታችንን፣ ንጉሣዊ ቤተሰብን በእምነት እንዲጠብቁ አደራ የተቀበሉት የክብር ዘበኞች በጥቂት መኮንኖች በተመሠረተ ዐድማ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆኑ የክብር ዘበኞች ጋር እምነታቸውን አጉድለው ቃል ኪዳናቸውን አፍርሰው በአገራቸው ላይ የክህደት ሥራ ፈጽመዋል:: እነዚህ እምነታቸውን ያፈረሱት ጥቂት ክፍሎች ንጉሠ ነገሥታቸው ለኢትዮጵያ ወዳጅ ለማትረፍ በውጭ አገር በጉብኝት ላይ ሳሉ፣ ንጉሣዊ ቤተሰቦችንና አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን በኃይል ወስደው በማስገደድ፣ ፫ ሺህ ዘመን ጸንቶ የኖረውን መንግሥት "ለውጠናል" በማለት ከቀኑ ከ፯ ሰዓት ጀምሮ ዐዋጅ አስነግረዋል:: ያላወቀውን ለማሣሣት የጦር ሠራዊት፣ የአየር ኃይልና ፖሊስ የተስማሙበት ጉዳይ በማስመሰል፣ የክህደት ሥራቸውን ለመጀመር እንዲያስችላቸው የሬድዮ ጣቢያውን ቀደም ብለው ይዘዋል:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለ ሙያ ንጉሠ ነገሥቱን የሚወድ የሚያፈቅር የተደረገለትን ውለታ ሁሉ የሚያውቅ በሃይማኖቱ የጸና፣ በወሬ የማይፈታ ታማኝ የሆነ ታላቅ ሕዝብ ነው:: የጦር ሠራዊቱ ለንጉሠ ነገሥቱና ለሀገሩ ፍጹም ታማኝ መሆኑን በመካከሉ ተገኝቼ አረጋግጬ አውቄያለሁ:: የጦር ሠራዊት፣ የአየር ኃይልና ፖሊስ በፍጹም ከአድማው ውጭ ናቸው:: ስለዚህ በሃይማኖታችሁና በቃል ኪዳናችሁ ፀንታችሁ እንድትገኙ፣ ንጉሠ ነገሥታችሁን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ብቻ በታማኝነት እንድታገለግሉ አደራ እያልኩ፣ ከሃዲ የሆኑትን ጥቂት ወንበዴዎች አትስሙአቸው:: እንዳትከተሉዋቸውም በተሰጠኝ ሥልጣን አውግዤአችኋለሁ

የሚል ነበር::

ሻለቃ ጠለለ ቸርነት ይህን በፓትሪያርኩ ስም ተዘጋጅቶ የተበተነውን የውግዘት ቃል በራሪ ወረቀት አሥመራ አሳትመው ይዘው በአውሮኘላን ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ በእግረ መንገድ መቀሌ፣ ደሴና አዲስ አበባ ካደረጉት ብተና በተጨማሪ የሻምበል (በኋላ ኮሎኔል) ዳጨው አድማሱ “ሲ-፭” በተባለ አውሮፐላን የክብር ዘበኛ ጦር ባለበትና በአዲስ አበባ ከተማ መበተናቸው ይታወቃል::



ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ወፓትርያርክ
ዘኢትዮጵያ

ይህ በእንዲህ እያለ እነ ጄኔራል መርዕድ የአየር ኃይል በክብር ዘበኛ ተቋማት ላይ የቦምብና የመትረየስ ድብደባ እንዲያካሒድ በሬዲዮ ያስተላለፉት የውጊያ ትእዛዝ ተጠልፎ ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ እንደደረሰው፤ ወዲያው ለጄኔራል መንግሥቱ ያሳውቃል:: ሆኖም የአየር ኃይሉ ክፍል ከወረቀት መበተን ሌላ በተባለው ሰዓት ወታደራዊ የማጥቃት ሥራ እስከ ቀኑ አሥር ሰዓት ድረስ አላካሔደም:: ጄኔራል መንግሥቱ ተጠልፎ የመጣውን የማጥቂያ ትእዛዝ እንደሰሙ፤ ስለውሳኔው ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንና ለልዑል ራስ እምሩ ለማሳወቅና የበኩላቸውን የአፀፋ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ለማስረዳት ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሔዱ:: በዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገው ልዑል ራስ እምሩ እስከዚሁ ሰዓት ድረስ ለሽምግልናው መሳካት ወደ እነጄኔራል መርዕድ ከጧቱ ፫ ሰዓት ተኩል የላኩዋቸው፣ የካፒቴን ኃይሉን መልስ በጉጉት ሲጠባበቁ ነበር:: ካፒቴን ኃይሉ ከጧት ጀምሮ በ፩ኛ ክፍለ ጦር በእነጄኔራል መርዕድ መንገሻ መሰብሰቢያ አዳራሽ ኮሪዶር ሲጉላሉ ውለው በመጨረሻ ጨርሶ ተስፋ የሚያስቆርጥ መልስ ይዘው ጄኔራል መንግሥቱ ይፈልጓቸው በነበረበት ጊዜ ነበር የተመለሱት:: ያመጡት መልስም "የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሕልውና አናውቅም እየተባለና፣ ሚኒስትሮችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ታሥረው ምን ዓይነት ውይይት ነው ሊካሔድ የሚችለው?። በመጀመሪያ እነዚህ ሁኔታዎች ካልተነሡ መወያየት አይቻልም!። "የሚል ሲሆን ብፁዕ ወቅድስ አቡነ ባስልዮስም "አንድ ጊዜ የውግዘት ቃል ወረቀቱን በትኛለሁ፣ ሌላ የማደርገው ነገር አይኖርም" ማለታቸውን የሚያረዳ ነበር::

ጄኔራል መንግሥቱም ይህ ከሆነ የማጥቃት ትእዛዝ እንደሚሰጡ ለልዑል ራስ እምሩ ተናግረው ሊሔዱ ሲሉ፤ ራስ እምሩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን ባስቸኳይ አግኝተው ስለ ጉዳዩ ለማነጋገር መፈለጋቸውን ስለገለጹላቸው፤ ጄኔራል መንግሥቱ በፈቃደኝነት በአልባሌ መኪና ሸኝተው ወደ ጠቅላይ መምሪያ ተመለሱ:: ከዚሁ ጋር አብሮ መነሣት ያለበት ሌላው ሁኔታ፣ ጄኔራል መርዕድ ስለሽምግልናው በመጨረሻ ሰዓት የተናገሩት ቃል ነበር::

> ተኩስ ሊከፈት እኩል ሰዓት እስቲቀረው ድረስ ግንኙነታችን አልተቋረጠም:: በዚሁ ጊዜ በልዑል አልጋ ወራሽ ስም ወደ እኛ ዘንድ መልእክተኛ እንደተመላለሰ ነበር:: ከዚህም በቀር፣ በመጨረሻው ሰዓት ከልዑል ራስ እምሩ የተላከ መልእክት ነው ተብሎ መጥቶ ነበር:: ይኸውም "አገሪቱን ከጥፋት ሕዝብን ከደም መፋሰስ ለማዳን እንዲቻል ጄኔራል መርዕድ መንገሻና ጄኔራል ከበደ ገብሬ በፍጥነት መጥተው ከእኔ ጋር እንዲነጋገሩ" የሚል ነበር:: ይህን ሐሳብ በፍጹም የማንቀበለውና የማይከጀል ድርጊት ነው በማለት ተቃወምነው::
>
> ነገር ግን በተላከው መልእክት ውስጥ "ሠራዊቱን ደም ከመፋሰስ ለማዳን" የሚለው አንቀጽ ታላቅ ጉዳይ በመሆኑ፣ አንድ ሰው ወደ ልዑል ራስ እምሩ ዘንድ ሔዶ እንዲነጋገር ወሰነን፣ ሻለቃ አሰፋ ለማን ላክነው:: ሻለቃ አሰፋ ለማም አሜሪካን ኤምባሲ ሔዶ፣ ልዑል ራስ እምሩን ሳያገኝ ከአቶ ገርማሜ ጋር ተነጋግሮ አንድ መልእክት፣ ይዞ ተመለሰ:: ያመጣው


መልእክት "ቢቻል ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ከበደ ሁለታችሁም፣ ያለበለዚያም ከሁለት አንዳችሁ መጥታችሁ በጉዳዩ ላይ እንመካከርበት:: ይህ ደግሞ የማይቻል መስሎ ቢታያችሁ፣ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መኖሪያ ወይም በከተማ ውስጥ ለሁለታችንም አማካይ በሆነ ሥፍራ ተገናኝተን እንነጋገር" የሚል ነበር::

ይህንና ይህንን የመሳሰለ የመልእክት መለዋወጥና ውዝግብ ከተደረገ በኋላ፣ በበኩላችን ለመጨረሻ ጊዜ በላክነው ደብዳቤ ውስጥ "ሕዝብን ከደም መፋሰስ ለማዳን የሚቻለው መሣሪያችሁን በቀጥታ ያስረከባችሁ እንደሆነ ነው" በማለት ቁርጥ ሐሳባችንን ገለጽንላቸውና መልእክት መለዋወጡን ዘጋን::

እንደ ጄኔራል መርዕድ አገላለጽ ከሆነ፣ በካፒቴን ኃይሉ የተላከው ደብዳቤ ከሻለቃ አሰፋ ለማ ወደ አሜሪካን ኤምባሲ መሄድ በኋላ መሆኑ ነው:: ጄኔራል መንግሥቱ ራስ እምሩን ወደ ፓትርያርኩ ግቢ ባልባሌ መኪና ከሰደዱ በኋላ የክብር ዘበኛ ተዋጊ ክፍሎች አዛዦችና የፖሊስ እንዲሁም የፀጥታ ኃላፊዎች ተሰብስበው አገኟቸው:: እነሱም:- ሻለቃ ቃለክርስቶስ ዐባይ፣ ሻለቃ ተፈራ በላይ፣ ሻለቃ ተፈራ ወ/ትንሣኤ፣ ሻለቃ ጌታቸው አፈወርቅ፣ ሻለቃ ጸጋዬ ጣሰው፣ ሻለቃ ዮሐንስ ምስክር፣ ኮሎኔል አስፋው አንዳርጌ፣ ኮሎኔል ታደሰ ብሩ (የፈጥኖ ደራሽ ጦር አዛዥ)ና ሻለቃ ኃይለ ማርያም ሌንጮ ሲሆኑ፤ ከነዚህ መኮንኖች በተጨማሪም ገርማሜ ንዋይና አቶ ገርማሜ ወንድ አፍራሽ (የሁለት አውላሎ አውራጃ ገዥ) አብረው ነበሩ::



የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ



የሻለቃ ተፈራ ወ/ትንሣኤ



የሻለቃ ጌታቸው አፈወርቅ




የሻለቃ ተፈራ በላይ



የሻለቃ መላኩ በቀለ

የሻለቃ ንጋቱ ተሊላ



የሻለቃ ኃይለማርያም ሌንጮ

ጄኔራል መንግሥቱ እነዚህን የክብር ዘበኛ መኮንኖችና ሌሎችንም በመሰብሰብ ጄኔራል መርዕድ ወደ አየር ኃይል ያስተላለፉትን ቴሌግራም ኮሎኔል ወርቅነህ እንዲያነብላቸው አደረጉ የሚሉት ሻለቃ ቃለ ክርሥቶስ፤ የተከተለውን ሁኔታ ሲያብራሩ፤

> ቴሌግራሙ «፰ ሰዓት ተኩል የክብር ዘበኛን ጠቅላይ መምሪያ፣ የ፫ኛ ሻለቃን ሰፈር የመድፈኛ ሰፈር በአውሮፕላን እንዲደበደብ» የሚያዝ ነበር። ጀኔራል መንግሥቱም ይህ የቴሌግራም ቃል በኮሎኔል ወርቅነህ ተነበ እንዳበቃ የውጊያ ትእዛዝ ሰጡ። በንግራቸውም የነጀኔራል መርዕድ የውጊያ ትእዛዝ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን፤ እኔ ግን አሩብ ሰዓት አሳልፌ ለ፱ ሰዓት አሩብ ጉዳይ፣ መድፈኛ መድፍ እንዲተኩስ አዝዣለሁ። አሩብ ሰዓት ማስተላለፌም ለግጭቱ ቀዳሚ እንዳልሆን ብዬ ነው። እዚያ እንዳለሁ አንድ መኮንን መጥቶ፣ ልዑል ራስ እምሩ «አባታችንን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስን አላገኘኋቸውም። ስለዚህ እኔ ተመልሼ ከቦታዬ እገኛለሁ» ብለውሃል ብሎ ነገረኝ፤

ይላሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን፣ ጀኔራል መንግሥቱ የውጊያ አቅጣጫና ስልትን አስመልክቶ በሰጡት መመሪያ ኮሎኔል ወርቅነህ አልስማማ በማለቱ ጭቅጭቅ ስለተነሣ፤ ሁለቱ በግል ተነጋግረው እስኪግባቡ ድረስ፣ የውጊያ ትእዛዝ ይቀበሉ የነበሩት መኮንኖች ለጥቂት ደቂቃዎች ከክፍሉ እንዲወጡ ተጠይቀው ወጥተው እንደነበር እና ሁለቱ ሲስማሙ ተመልሰው መግባታቸውንም የዘመቻው መኮንን የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ይገልጻሉ።

የሁለተኛ ብርጌድ ጦር አዝማች የነበሩት የሻለቃ ተፈራ በላይ ደግሞ ስለሁኔታው

> በአስቸኳይ ወደ ክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ተጠራን። በመጨረሻ የውጊያ ትእዛዝ ተሰጠን። ከእኛ ጋር የሸዋ ፖሊስ አዛዥ ኮሎኔል ቀልቤሳ ቤካ (በኋላ ብርጋዴር ጀኔራል) እና ኮሎኔል ጋሻው ከበደ (በኋላ ብርጋዴር ጀኔራል የአዲስ አበባ ከተማ ፓሊስ አዛዥ) ነበሩ። የተሰጠን ትዕዛዝ አጭር ነበር። እሱም (መድፈኛ መድፍ እንዲተኩስና ማጥቃት እንዲቀጥል በተቻለ መጠን ለማስፈራራት ወደ ላይ ተኩሱ የሚል ርኅራኄ የተቀላቀለበት ሳይፈለግ የተሰጠ የውጊያ ትእዛዝ ነበር።

በማለት ይገልጻሉ።

ከዚህ በኋላ፣ ተሰብስበው ለነበሩት መኮንኖች ስለተሰጠው ትእዛዝ በየበኩላቸው ስለሚከናወነው ተግባር በግልጽ ገብቷቸው እንደሆን ወይም ያልገባው ካለ እንዲጠይቅ በሰጡት ዕድል፣ የክብር ዘበኛ ጦር አዝማች የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ ሐሳብ አቅርበው ነበር። ሐሣቡም፣ "ተቃዋሚው ሠራዊት ቦታ ቦታ ይዟል፤ የኛ መድፍ መተኮስ መጣንልህ ለምንለው ሕዝብ መጣንብህ ማለት ይሆናል። ስለዚህ የማጥቃቱን ውጊያ በእግረኛ እንቅስቃሴ ማከናወን የሚሻል ይመስለኛል" የሚል አስተያየት ነበር። ሆኖም፣ ይህን በሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ የቀረበውን ሐሳብ ጀኔራል መንግሥቱ አልተቀበሉትም። ጀኔራሉ እንዲሆን የፈለጉትን "ለዘማቹ ጦር ወደ ሰው ከመተኮሳችሁ በፊት በድምፅ ማጉያ ከእናንተ ጋር እንዲተባበሩ ለማግባባት ሞክሩ፤ በተቻለ መጠን በመጀመሪያ ለማስፈራራት ወደ ላይ ተኩሱ፤ ወደ ሰው አትተኩሱ" በማለት አዘዙ። "ሲተኩሱብን ምን እናድርግ?" የሚል ጥያቄ ሲነሣ ደግሞ፤ "ሲተኩሱባችሁማ ምን

ማድረግ ትችላላችሁ?" የሚል ነበር:: ጄኔራል ጽጌ ዲቡም የውጊያ ትእዛዝ ይቀበሉ ለነበሩ መኮንኖች "በማጥቃት ጊዜ ሰው ተመትቶ ሲወድቅ እሱን ለማንሣት ብላችሁ ጊዜ እንዳታጠፉ፤ በፍጥነት አልፋችሁ ወደ ግባችሁ መገሥገሥ ነው:: የወደቀ የሚያነሣ የተለየ የተዘጋጀ ክፍል አለ" ብለው አደፋፈሩ::

በመፈንቅለ መንግሥት ሞካሪዎቹ ኃይሎች በኩል፤ እንዲህ ሲደረግ በዘውድ ጠባቂው ወገኖች ለዚህ ማፍረሻ የጄኔራል መርዕድና የጄኔራል ከበደ ፊርማ የሰፈረበት ቀጥሎ የቀረበው በራሪ ወረቀት በአውሮፕላን በአዲስ አበባ ከተማ ተበተነ::

### ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጠቅላይ የጦር ኃይሎች ኤታ ማጆር ሹም የተሰጠ መግለጫ

ታኅሣሥ ፬ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ከምሽቱ ፬ ሰዓት ጀምሮ፣ ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ የክብር ዘበኞች በተለይ የተጣለባቸውን እምነትና አደራ አጉድለው፣ የወታደር ቃል ኪዳናቸውን አፍርሰው፣ የንጉሠ ነገሥቱን ቤተሰብ በኃይል ደፍረው፣ ልዑል አልጋ ወራሽን በማስገደድ በዐዋጅ ስም በሬዲዮ የተነገረውን ሰምታችሁታል::

በዚህ ዐዋጅ ነው በተባለው ቃልና በርሱም ላይ በተሰጠው ሐተታ በዐድማው ውስጥ የጦር ኃይሎች ሁሉ የሚገኙበት በማስመሰል ተነግሯል:: ይህ ግን በፍጹም ሐሰት ነው:: የጦር ሠራዊት፣ የአየርና የባሕር ኃይል ሙሉ በሆነ ኅብረትና አንድነት የክህደት ሥራ የፈጸሙትን ወንጀለኞች ለመቃወምና፣ ጨርሶ ለመደምሰስ ታጥቀው መሣሪያቸውን አንስተዋል:: እነዚህ የጦር ኃይሎች ከጠቅላይ አዛዣቸው ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተሰጣቸውን ትእዛዝና ግዳጅ ከማክበርና ከማስከበር ከቶ አያጓድሉም:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለሚወዱት ሕዝባቸውና ለአገራቸው ለኢትዮጵያ የሰጡትን አገልግሎትና የፈፀሙትን ሙያ ሕዝባቸው ሁሉ እናውቅላቸዋለን:: ይህንንም መላው ዓለም ያውቅላቸዋል:: አሁንም በዚህ ሕዝባቸውን በማገልገል ተግባር ላይ ይገኛሉ::

### የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

የጦር ኃይሎች ቃል ኪዳን ለገባንላቸው ለታላቁ ንጉሠ ነገሥታችን ዙፋንና መንግሥቱን በክብር ለመጠበቅ አገራችንን በታማኝነት ለማገልገል ቆርጠናል:: ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደር የማይገኝለት አገልግሎት እንደሰጡህ ዐውቀህ፣ ክብርህን ነፃነትህን ፍቅርህን የላኩላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በያለህበት ፀጥታህን አክብረህ በመካከልህ ለመገኘት በጉዞ ላይ ያሉትን ንጉሠ ነገሥትህን በክብር ለመቀበል ተዘጋጅ::

የክብር ዘበኛና ፖሊስ ለንጉሠ ነገሥታችሁ ተገዥ፣ ለአገራችሁም አገልጋዮች መሆናችሁ የታወቀ ስለሆነ፣ ቁጥራቸው በጣም ጥቂት በሆኑ ወንጀለኞች መኮንኖቻችሁ እንዳትታለሉ:: ለ፫ ሺህ ዘመን በዓለም ታሪክ በክብር የታወቅነውን ሰዎች አባቶቻችሁ የኢትዮጵያን ታላቅነት ሳታሳንሱ በሃይማኖታችሁና በወታደር ቃል ኪዳናችሁ ፀንታችሁ ለትልቁ የኢትዮጵያ

አገልጋይ፣ ለግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የታማኝነታችሁን ማረጋገጫ የወንጀለኞቹን እጅ እየያዛችሁ ከወንድሞቻችሁ ከጦር ኃይሎች ተቀላቀሉ።

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!*

በሞት ጥላ ሥር ወድቃ የነበረችውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዐላማ መልሰው፣ ከፋሽስት ጭቆና ቀንበር አውጥተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እየመሩ፣ የድህነትን ቀንበር ለማቅለል ሌት ተቀን የሚደክሙትን ንጉሠ ነገሥትህን፤ ጥቂት ወንበዴዎች በድንቁርና መንፈስ ተመርተው አገሪቱን ለመከፋፈልና ሕዝቡን ለማዋጋት ስለተነሡ እነዚህን ዐመፀኞች በሽማግሌ በባልቴቶችና በሕፃናት ላይ አደጋ ከማድረሳቸው በፊት ከታማኙ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሠራዊትና ሰላማዊ ሰው ጋር በመተባበር ፈጥናችሁ አጥፏቸው።

ለኢትዮጵያ ብልፅግናና ለሕዝባቸው እድገት ለአገሪቱ መሻሻያ መንገድ ለመፈለግ በልዩ ልዩ አገሮች ለጉብኝት ወደ ውጭ አገር ሔደው የነበሩት ገናናው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተመልሰው ኢትዮጵያ ገብተዋል።

ስለዚህ፣ የጊዜውን ሁኔታ በመመልከት ለወንጀለኞች ጊዜ መስጠት አስፈላጊ መስሎ ስላልታየ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የምድር ጦርና የአየር ኃይል በህብረት ግዳጃቸውን እነሆ ጀምረው አሁን በማጥቃት ላይ የገኛሉ።

የሚል ነበር።

ምንም እንኳን የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች የዘውድ ጠባቂው ወገን የአየር ድብደባ እንደሚያደርግ መረጃው የደረሳቸው ቢሆንም ወዲያው ድብደባው አለመጀመሩን ጠቁሜአለሁ። አጀማመሩም በዚያን ጊዜ የአየር ኃይሉ የሕዝብ ግንኙነትና የፕሮፖጋንዳ ኃላፊ የነበረው የሻለቃ ሰይፉ ኃይለ ሥላሴ እንደነገረኝ የአሜሪካ ተራድኦና ማሠልጠኛ ተቋም "MAAG" የአየር ክፍሉ ኃላፊ ኮሎኔል ራምሲስ በጊዜው ኤፍ ፹፮ ጄት አብራሪ የነበረውን፣ የመቶ አለቃ ደብሩ ድንበሩንና ቦምብ ጣይና መትረየስ ተኳሽ አውሮፕላን አብራሪ የነበረውን የመቶ አለቃ አበበ ወርዶፋን "ሒዱና የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያን ደብድቡ" ብሎ ገፍቶ ወደ አውሮፕላን ለማስገባት ሲሞክር፤ የመቶ አለቃ አበበ ወርዶፋ "ወገኖቼን በአውሮፕላን አልደበድብም። የሚመጣውን እቀበላለሁ" በማለቱ በእሥር እንዲቆይ ተደርጓል። የመቶ አለቃ ደብሩ ድንበሩ ደግሞ ትእዛዙን ተቀብሎ በሮ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያንና ሌሎቹንም ክፍሎች ደብድቦ ተመለሰ። የአየር ኃይል ጓደኞቹም "እንዴት አደረክ?" ብለው ሲጠይቁት "የወንድሜን ቢሮ ደብድቤ መጣሁ" አለ። የሻለቃ ክፍሌ ድንበሩን ማለቱ ነው።

እስከዚህ ሰዓት ድረስ ፊታውራሪ አሉላ በቀለ (በኋላ ደጃዝማች)፣ ልጅ ዳንኤል አበበ (በኋላ ደጃዝማች) አየር ኃይል የውጊያ ዕዝ መደብ ላይ ሆነው የኮሎኔል አሰፋ እየነን እንቅስቃሴ መከታተላቸውን አላቆሙም ነበር። ሁኔታቸው አዝማሚያው ካላማረ ኮሎኔል አሰፋን ከመምታት የማይመለሱ መሆናቸውን ያሳይ ነበር።

ኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ደግሞ ሐሙስ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ጠላት በ፰ ሰዓት ያጠቃል የሚል ወሬ በ፯ ሰዓት ስለመሰማቱ፤ የጦር ሠራዊት ማዘዣ ስፍራ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በጠላት መሣሪያ የታለመበት "የተመዘገበ" በመሆኑና የማዘዣው ሥፍራ ከአንደኛ ክፍል ጦር ጠቅላይ ሠፈር አንድ ኪሎ ሜትር ርቆ ስለመቋቋሙ እንዲሁም ማናቸውም ተንቀሳቃሽ መኪናና አስፈላጊ መሣሪያዎች ቦታ እንዲይዙ እንደተደረገና ስለጠቅላላ ውጊያው ለበላይ ባቀረቡት ሪፖርት ገልጸዋል፡፡ "በሽምግልናው ጥረት ደም መፋሰሱ ቀርቶ ለውጡ በሰላማዊ መንገድ ሊያልቅ ይችላል" ተብሎ በመፈንቅለ መንግሥት መሪዎች በኩል ተጥሎበት የነበረው ተስፋ ከስሞ፤ ሁለቱ ተፎካካሪዎች በየበኩላቸው ለፍልሚያው ስላወጡት የውጊያ ስልትም እንደዚሁ በኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት ላይ ሠፍሯል፡፡ ሪፖርቱ እንደሚገልጸው እነጄኔራል መርዕድ ኃይላቸውን በማረጋገጥ የማጥቃት እርምጃ ለመውሰድ ሲወስኑ፤ ጦሩም ከየአገሩ ረዳት ጦር እንደሚመጣለት በመተማመን በታንክና በመድፍ የበላይነት፣ እንዲሁም የአየር እርዳታ ማግኘቱን ስለተረዳ ሥጋት አላደረበትም፡፡ ቁርጥ ሐሳቡም ከውጭ ጦር እስኪመጣለት ድረስ ባለው ጦር መከላከልና መልሶ ማጥቃት ነበር፡፡ በአንጻሩ የመፈንቅለ መንግሥቱ ጦር በሁለት ጉዶሎ ብርጌድ በመንፈስ ኃይልና ብርታት በመደገፍ የጦር ሠራዊትን ለማጥቃት ኃይሉን በየሥፍራው ከፋፍሎ ልዩ ልዩ ቦታዎችን በማስጠበቅ፣ አንደኛ ክፍለ ጦርን አጥቅቶ ከያዘ በኋላ፣ አንድ የሻምበል ጦር ወደ ደብረ ዘይት ሐረር ሜዳ ሔዶ የአየር ኃይልን ሠፈር መያዝ ነበር፡፡[14]

## የተኩሱ መጀመር

በእነ ጄኔራል መንግሥቱ በኩል፣ መጀመሪያ የሚመታው የክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ መሆኑን በማወቅ፤ የማጥቂያ ውጊያ ለ፱ ሰዓት ሩብ ጉዳይ እንዲጀመር ትእዛዝ ከተሰጠ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፤ የክብር ዘበኛ የትእዛዝ መስጫ መምሪያ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ተዛወረ፡፡ የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ እንደገቡ፣ የመድፍ ተኩስ ከአንደኛ ክፍለ ጦር ተጀመረ፡፡ ይህም የሆነው የኮሌጅ ተማሪዎች ከተማውን በሰላማዊ ሰልፍ ሲዞሩ ቆይተው ወደ ግቢያቸው መግባት ሲጀምሩ ነበር፡፡ ለክብር ዘበኛ ጠቅላይ መመሪያ እና ለሦስተኛ ሻለቃ ሠፈር ተብሎ በጦር ሠራዊቱ መድፈኛ ክፍል የተተኮሰው የመድፍ ጥይት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ (ከነበረው ሕንፃ) ቅጥር ግቢ አቅራቢያ፣ ዛሬ የቱሪስት ሆቴል ሕንፃ በተሠራበት ቦታ ላይ በነበረ አንድ ትልቅ ጠጅ ቤት ላይ ወድቆ፣ ጉዳት በማድረሱ ተማሪዎቹ ተሯሩጠው በየመጠለያው ገቡ፡፡ የመፈንቅለ መንግሥቱ የፕሮፓጋንዳ ክፍል ወዲያው በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ "የጦር ሠራዊት በሰላማዊ ሰልፍ ላይ የነበሩትን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና መንገደኛውን ሕዝብ በመድፍ ጥይት ጨረሳቸው" ሲል አሰማ፡፡

---

14 የኮሎኔል ጃገማ ኬሎ ሪፖርት

በክብር ዘበኛ በኩልም ውጊያውን ለመጀመር እንቅስቃሴ ተጀመረ። በዘመቻው ዕቅድ መሠረት መጀመሪያ የመድፍ ጥይት ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር መተኮስ ነበረበት። የመጀመሪያው የመድፍ ጥይት ወደ አንደኛ ክፍል ጦር መተኮስ ከመጀመሩ በፊት፣ በከተማ ውስጥ በመድፍ ተኩስ ስለመጠቀሙ አስፈላጊነት ቅሬታ ተፈጥሮ ነበር። ስለሁኔታው ሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ እንዲህ ይላሉ።

> የክብር ዘበኛ ሠራዊት የኦፕሬሽን ኃላፊ፣ ሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይ (በኋላ የትግራይ ክፍለ አገር አስተዳዳሪ) ‹አንደኛ ክፍለ ጦርን በመድፍ ምታ› የሚል ትእዛዝ ሰጡኝ። ‹ምን ይመስልሃል?› በማለት ጠየቀኝ። እኔም፣ ‹የጄኔቫ ኮንቬንሽን ለእኔም ለአንተም ሀ..ሁአችን ነው። እናውቀዋለን። የከተማ ውስጥ ውጊያ በቀላል መሣሪያ እንጂ፣ በከባድ መሣሪያ አይካሔድም፤ ክልክል ነው› አልኩት። ይህን ካልኩት በኋላ ቀጥዬ፣ ‹ባታስተኩስ ደግሞ አንተን ሊገድሉህ ይችላሉ። ምንም አማራጭ የለም፣ አስተኩስ› አልኩት። ከዚህ በኋላ፣ ለክብር ዘበኛ መድፈኛ አዛዥ፣ ለሻለቃ ጸጋዬ ጣሰው ትእዛዝ ሰጠ። አንደኛ የመድፈኛ ሻምበል በታላቁ ቤተ መንግሥት፣ ሁለተኛ የመድፈኛ ሻምበል ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ጀርባ በደጀንነት እንዲጠብቅ ተደረገ። ወደ ጦር ሠራዊት መድፈኛ ሠፈርና ወደ አንደኛ ክፍለ ጦር የሚተኮስ አሥራ ሁለት (፲፪) የመድፍ ጥይቶች ተዘጋጁ። አንድ የሃምሳ አለቃ፣ በ"ኤፍ.ዲ.ሲ" የተኩስ መምራት ሙያ የሠለጠነ፣ በአንደኛ ክፍለ ጦር በባቡር ሃዲዱ አጠገብ ሆኖ፣ በሬዲዮ መገናኛ የመለኪያ የማዕዘን ጉን እንዲገልጽ ታዘዘ። በትእዛዙ መሠረት ከአስተኳሹ መልስ እንደተገኘ፣ በመጀመሪያ የተተኮሰው የመድፍ ጥይት እነጄኔራል መርዕድ አሉበት ተብሎ ይገመት ከነበረው ቤት ጐን የነበረውን ቤት መታው። ሁለተኛው ጥይት እንደዚሁ የመጀመሪያው ጥይት ካረፈበት ቦታ ጥቂት አለፍ ብሎ እዚያው ግቢው ውስጥ ወደቀ። ከእነዚህ ፪ ጥይቶች በኋላ የተተኮሰ የመድፍ ጥይት አልነበረም። ሆኖም ለውጤት አራት አምስት ያህል የመድፍ ተኩሶች መቀጠል ሲገባቸው ቆመ።[15]

ስለተኩሱ መቆም የተሰጠው ምክንያት ብዙ ነው። አንዱ የክብር ዘበኛ መድፈኞች ያመፁው ማን መሆኑን ከተበተነው ወረቀት ካወቁ በኋላ፣ "በወገኖቻችን ላይ መድፍ አንተኩስም፤ በጦር ሠራዊቱ ላይ ጉዳት ማድረስ አንፈልግም፤ የከተማውን ሕዝብም አናሸብርም" በማለት ተኩስ አቆሙ የሚል ነው። ሌላው ደግሞ፣ ተኩሱ እንዳይቀጥል ለመድፈኛ አዛዡ ትእዛዝ ተሰጥቷል ተብሎ መነገሩ ነው። የዘመቻ መኮንኑ የሻለቃ ቃለ ክርስቶስም እሳቸው ተኩሱ እንዲቀጥል ትእዛዝ ብሰጥም፤ የበታች ሹማምንት "አንተኩስም" በማለት ትእዛዝ አልፈፅምም ከማለታቸው ባሻገር፤ የመድፉን ቃታ አውልቀው እስከመጣል እንደደረሱ ሻለቃ ጸጋዬ ጣሰው የነገሩኝ ነው ብለው ገልጸውልኛል።[16] ለክብር ዘበኛ መድፎች ተኩስ እንዳይቀጥል ትዕዛዝ

---

[15] ሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ

[16] ሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ ይሄን የነገሩኝ በ፲፱፻፹፮ ሲሆን፤ ሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ዐባይም በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. የገለጹልኝ ይሄንኑ ነው።

ተሰጥቷል የሚለው ጥርጣሬ ግን ትክክል ይመስላል። ምክንያቱም የመኮንኖቹ የቅጣት ደረጃ ሲታይ ተኩስ ያቆመ አካል እንዳለ የሚያመለክት ነበርና።

ነገሩ እንዲህ ነው። ከመፈንቅለ መንግሥቱ ክሽፈት በኋላ የተወሰኑ የክብር ዘበኛ መኮንኖችና እኔም የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ወደ ቤተ መንግሥት ተወስደን ስለ እንቅስቃሴው የምታውቁትንና የሠራችሁትን ለጃንሆይ ግለጹ እየተባለ ተጠይቀን ሁሉም የራሱን ግንዛቤና የሠራውን ገልጾ ሲጨርስ እንደየሥራችሁ የፍርድ ውሳኔ ታገኛላችሁ እየተባልን ተመለስን። የሻለቃ ቃለ ክርስቶስ ግን ለክስ ሳይደርሱ በነፃ እንዲለቀቁ ተብሎ ነበረ። የሻለቃ ቃለ ክርስቶስም ይህ ለሞራሌና ለቤተሰቤ ታሪክ መልካም አይሆንም ስላሉ፤ እንግዲያው ዝቅተኛ ቅጣት ባገኙት ጓደኞቼ ልክ ይወሰንለት ተብለው በሦስት ዓመት ግዞት ናዝሬት እንዲቀመጡ ተደርጓል። እሳቸው ያዘመቷቸው ዘማቾች ግን ከፍተኛው ፲፩ ዓመት ዝቅተኛው ፯ ዓመት እሥራት ተፈርዶባቸዋል። የክብር ዘበኛ ሠራዊትም በዚህ ያጉተመትም ነበር። እኔ በዚህ መፈንቅለ መንግሥት እንቅስቃሴ ላይ መጽሐፍ ልጽፍ እንዳሰብኩ ገልጨላቸው፤ ስለመድፍ ተኩሱ አቋቋም ትክክለኛ መግለጫ እንዲሰጡኝ ሻለቃ ቃለ ክርስቶን ደጋግሜ ጠይቄአቸው ነበር። ደጋግመው የነገሩኝ መልሳቸውም ከላይ የተገለጸው ብቻ እንደሆነ ነው።

ይህ የክብር ዘበኛ መድፍ ጥይቶች ምት በዘውድ ጠባቂው ኃይል ላይ ከፍተኛ መደናገጥ አስከትሎ ነበር። ስለዚህ ይህ ድንቅ የመድፍ ዒላማ ተኩስ መቀጠል ሲገባው መቋረጡ ደባ እንደተሠራ አመልካች ነው። የክብር ዘበኛ ዒላማ ምት በጣም ጥሩ ስለነበር፤ እነጄኔራል መርዕድ "ከመካከላችን ዒላማ የሚመራና የሚያስተኩስ ሰው አለ?" በማለት ጥርጣሬ ውስጥ እስኪገቡና እስኪጨቃጨቁ አድርጓቸው ነበር።[17] ምናልባት ሻለቃ ቃለ ክርስቶስ የመድፍ ተኩስ መቋረጥ ነገር ሲነሳ ደስ የማይላቸው ለዚህ ይሆናል።

[17] የሻለቃ ክፍሌ ድንበሩ፤